# የአካል ጉዳተኛ
# ልጅዎን
# ቀጣይ ሕይወትን አስተማማኝ ማድረግ

**ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ወደ ጎልማሶች አገልግሎት**
**የሚደረግ ሽግግር መምሪያ**
**ለአካል ጉዳተኛ ጎልማሶች**
**በአሌክሳንድሪያ፣ አርሊንግተን፣**
**ፌርፋክስ እና ፎልስ ቸርች ውስጥ ለሚገኙ**

The Arc Northern Virginia

Transition POINTS — Providing Opportunities, Information, Networking and Transition Support

**ለ The Arc of Northern Virginia**
**Transition POINTS Program የተዘጋጀ**

**ኦክቶበር 2019**

ይህ መምሪያ በ The Arc of Northern Virginia’s Transition POINTS ሃላፊነት ስር የአእምሮ አካል ጉዳተኛ ልጆች ላላቸው ወላጆች ከተዘጋጁት ስድስት መምሪያዎች መካከል አንዱ ነው። Transition POINTS ቁልፍ በሆነ የሕይወት ውሳኔ ነጥቦች ላይ ያተኩራል፡ የበሽታ ምርመራ ውጤት ማግኘትና አካል ጉዳተኛ የሆነ ልጅ ወደ ቅድመ እርምጃ ፕሮገራም እንዲገባ ማድረግ፤ ትምህርት መጀመር፤ ከት/ቤት ስርዓት ውጭ ሽግግር ማድረግ፤ የስራ ቅጥር ማግኘት፤ ከተንከባካቢው ቤት ውጭ የመኖሪያ ቦታ ማግኘት፤ እና ከአካል ጉዳተኝነት ጋር ማርጀት።

የዚህ መምሪያ የሕትመት ቅጂ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ይዘጋጃል። መረጃዎች ሲለዋወጡ፣ የዘመነ መረጃንና ግብዓቶችን ከሪሶርስ ቤተ መጻሕፍት በቀጣዩ ድረ ገጻችን ላይ ማግኘት ይችላሉ www.thearcofnova.org

ይህ መምሪያና በስፓኒሽ፣ ቬትናምኛ፣ ቻይንኛ፣ አረብኛ እና ኮሪያኛ በተከታታይ የተዘጋጁ የ Transition POINTS መምሪያዎች ትርጉሞችን ከቀጣዩ ድረ ገጽ ማውረድ ይቻላል፡ https://thearcofnova.org/programs/transition/። የትርጉም ስራዎችን ለማሰራት የተቻለው ከ Virginia Board for People with Disabilities (ቨርጂኒያ የአካል ጉዳተኞች ቦርድ) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ምክንያት ነው። ከ Rotary Club of Alexandria ተጨማሪ ድጋፍ ተገኝቷል። ይህ መምሪያ ወደ አማርኛ ቋንቋ እንዲተረጎም ያስቻለው ከ Alexandria Fund for Human Services የተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው።

እባክዎ ማናቸውንም አስተያየቶች ወይም ተጨማሪ ነጥቦች ለ Diane Monnig፣ TransitionManager፣ The Arc of Northern Virginia፣ Transition POINTS፣ 2755 Hartland Road, Suite 200, Falls Church, VA  22043 (703)208-1119 ext 118 dmonnig@thearcofnova.org ይላኩ።

የቅጂ መብት © 2019 The Arc of Northern Virginia

**የገጽ ማውጫ**

**የ Transition POINTS መግቢያ**

**ቀጣይ ሕይወትን አስተማማኝ ማድረግ፡ መግቢያ** ....................1

**የተግባር መዘርዝር ለወላጆች** ....................5

**ስለ ምን ማሰብ እንደሚገባ**

ድሕረ ሞት የሐብትና የጥቅማ ጥቅም ማስተላለፍ ዝግጅት....................7
የኮሌጅ ትምህርት፣ የስራ ቅጥር እና የእንክብካቤ መስጫ አገልግሎቶች....................11
መዝናኛ....................14
የትራንስፖርት አገልግሎት....................15
የመኖሪያ ቤት አማራጮች....................16

**ቅጥያዎች**

#1 ጥሩ መረጃዎችን መያዝ ....................17
#2 የጤና ኢንሹራንስ ማረጋገጥ ....................18
#3 ለጥቅማ ጥቅሞች ማመልከት፡ የማሕበራዊ ዋስትና አካል ጉዳተኝነት ፕሮግራሞች.................... 19
#4 ለጥቅማ ጥቅሞች ማመልከት፡ የ Medicaid መሻሪያ ፕሮግራሞች ....................22
#5 ድሕረ ሞት የሐብት ማስተላለፊያ እና የልዩ ፍላጎቶች ትረስት ማቋቋም ....................24
#6 የውሳኔ አሰጣጥ ድጋፎች እና የሕግ ባለስልጣን አማራጮች....................26
#7 ት/ቤት ተኮር የሽግግር አገልግሎቶች ጋር መስራት።....................30
#8 የኢንተርንሺፕ ፕሮግራም እና የሽግግር ድጋፎችን መዳሰስ....................33
#9 የኮሌጅ ትምህርት ግብዓቶችና የትምህርት ድጋፎችን መዳሰስ....................35
#10 ለስራ ቅጥር መዘጋጀትና ከ DARS ጋር መስራት ....................38
#11 ለስራ ቅጥር እና ለእንክብካቤ አገልግሎቶች ከ CSB እና ESOs ጋር መስራት ....................45
#12 ዘና ማለት ....................52
#13 አካባቢን መቃኘት....................57
#14 ለራስ መሟገት .................... 54
#15 የቤት አማራጮችን መዳሰስ....................58

ምስጋና ....................62

**በእነዚህ ሁሉ አርእስት ላይ ተጨማሪ ግብዓቶችን ለማግኘት፣ የ The Arc of Northern Virginia's**

- የእውነታ ቅጾችና ናሙናዎች የግብዓት ቤተ መጻሕፍትን ድረ ገጽ ይጎብኙ https://thearcofnova.org/programs-services/library/
- የጠበቆች፣ ቴራፒስቶች፣ የመዝናኛ እና ተጨማሪ የግንኙነት መረጃን የአድራሻ ማውጫ ከዚህ ያገኛሉ፡ https://thearcofnova.org/directory/
- የ Special Needs Trust ድረ ገጽ https://thearcofnovatrust.org/ SNT እና ABLE ለሚመለከት መረጃ
- የተለያዩ የሕይወት ዕቅድ ማውጫ መሳሪያዎች ላይ ያሉ አርእስትን የተመለከቱ ምዝግብ ውይይቶችን የያዘ የ YouTube ቻናል https://www.youtube.com/user/VideosatTheArcofNoVA

## መግቢያ

የአእምሮና የዕድገት አካል ጉዳት (ID/DD) ዕድሜ ልክ የሚቆይ በመሆኑ ID/DD ላለበት ወዳጅ ዘመድ እንክብካቤ ማደረግ የዕድሜ ልክ ሃላፊነት ነው ማለት ነው። እነዚህ የአካል ጉዳቶች ባላቸው ተፈጥሮ ምክንያት፣ ተንከባካቢዎች በወዳጆቻቸው የሕይወት ምዕራፍ ውስጥ እጅግ ወሳኝና ብዙውን ጊዜም በጣም አስቸጋሪ ውሳኔዎችን መወሰን አለባቸው - ወዴትኛው ት/ቤት እንደሚገባ ወይም እንደምትገባ፣ ትምህርታቸውን ሲጨርሱ ምን እንደሚያደርጉ፣ ለመዝናናት ምን እንደሚያደርጉ፣ የት እንደሚኖሩ፣ እና ተንከባካቢው ከዚህ በኋላ ከእነርሱ ጋር በማይሆንበት ወቅት የፋይናንስ ደህንነታቸውን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻል የመሳሰሉትን።

ተንከባካቢዎች ለወዳጆቻቸው የተሻሉ ምርጫዎችን ለማድረግ ቢፈልጉም፣ ብዙዎቹ ግን ይህን ለማድረግ የሚያስፈልግ ግብዓት እንደሌላቸው ጥናቶች አሳይተዋል። The Arc ያካሄደው ሃገር አቀፍ የዳሰሳ ጥናት የአእምሮ አካል ጉዳት ያለባቸውን ወዳጆቻቸውን ለማገዝ የሚጥሩ በርካታ ቤተሰቦች እንዳሉ አረጋግጧል፡

- ጥናቱ ከተደረገባቸው ቤተሰቦች መካከል 80 በመቶ የሚሆኑት ለሚያስፈልገው እንክብካቤ የሚሆን በቂ ገንዘብ የሌላቸው ሲሆን ወደ ግማሽ የሚጠጉት ደግሞ ማስተናገድ ከሚችሉት በላይ ተጨማሪ የእንክብካቤ ሃላፊነቶች እንዳሉባቸው ገልጸዋል
- 85 በመቶ የሚሆኑት ቤተሰቦች ID/DD ያለበት ጎልማሳ የቤተሰባቸው አባል የሙሉ ጊዜ ወይም የትርፍ ሰዓት ስራ እንደማይሰሩ ገልጸዋል
- 62 በመቶ የሚሆኑት ቤተሰቦች ዘላቂ የሆነ የእንክብካቤ ዕቅድ የላቸውም
- 75 በመቶ የሚሆኑት ለወዳጆቻቸው ድሕረ ት/ቤት እንክብካቤ፣ የማህበረሰብ አገልግሎቶች ወይም የክረምት ወቅት እንቅስቃሴዎችን ማግኘት አልቻሉም
- 59 በመቶዎቹ የቤት አማራጮችን በተመለከተ ጥሩ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ በቂ መረጃ እንደሌላቸው ገልጸዋል
- 65 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ለቀጣይ ሕይወት ዕቅድ ለማውጣት በቂ ድጋፍ እንደሌላቸው ገልጸዋል።[1]

### ስለ Transition POINTS

ቤተሰቦች ልጃቸው በሚያድግበት ጊዜ ለሚያሳልፏቸው መጠነ ሰፊ ውሳኔዎች የሚጠቀሙበት ተጨባጭ እና እርምጃ ሊወሰድበት የሚችል መረጃ ያስፈልጋቸዋል። ይህን መረጃ ማቅረብ ደግሞ የ The Arc of Northern Virginia's Transition POINTS ፕሮገራም ተልዕኮ ነው (ዕድሎችን መፍጠር፣ የመረጃ፣ የትስስርና የሽግግር ድጋፍ መስጠት)።

Transition POINTS የአእምሮ አካል ጉዳተኛ በሆነ ግለሰብ የሕይወት ዘመን ውስጥ ስድስት ቁልፍ የውሳኔ ነጥቦች ላይ ያተኩራል፡

1. የበሽታ ምርመራ ውጤት መቀበልና ልጅ ወደ ቅድመ እርምጃ ፕሮግራም እንዲገባ ማድረግ፤
2. ትምህርት መጀመርና ወደ ልዩ ትምህርት ስርዓት መግባት፤
3. ከት/ቤት ስርዓት በመውጣት ወደ ጎልማሶች አገልግሎት መሸጋገር፤
4. ወደ ስራ ዓለም መግባት፤
5. ቤት ማግኘት፤ እና
6. ከአካል ጉዳት ጋር ማርጀት።

ለእያንዳንዱ የመሸጋገሪያ ነጥብ፣ ማቴሪያሎችን በሕትመትና በዲጂታል ቅርጸት፣ ኦንላይን የመረጃ ግብዓቶች፣ ወርክሾፖችና የኢንተርኔት ውይይቶችን እናቀርባለን።

በዚህ መምሪያ ውስጥ የሚገኘው መረጃ የአእምሮ እና ዕድገት አካል ጉዳት ያለባቸው ሁሉም ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው ላይ ተፈጻሚነት ቢኖራቸውም፣ ግብዓቶችን ለማግኘት አብዛኛው የግንኙነት አድራሻ ግን ለ Northern Virginia አካባቢ የታሰበ ነው። ለአካባቢዎ ማህበረሰበ የተዘጋጁ ግብዓቶችን ለመዳሰስ፣ በክልልዎ የሚገኝ Community Services Board (CSB፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ቦርድ) ያነጋግሩ። የአካባቢዎን CSB ለማግኘት የ DBHDS (Department of Behavioral Health and Developmental Services) ድረ ገጽን http://www.dbhds.virginia.gov/community-services-boards-csbsor ይጎብኙ። CSB የአእምሮ ጤና ችግር፣ የአእምሮና የዕድገት አካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ወጪያቸው በመንግስት ወደሚሸፈኑ አገልግሎቶች ስርዓት የመግቢያ በር ነው። በተጨማሪም፣ የ The Arc of Virginia ድረ ገጽን www.thearcofva.org በመጎብኘት በማህበረሰብዎ ውስጥ የሚገኘውን የ Arc ቅርንጫፍ ማግኘት ይችላሉ። በአካባቢዎ የሚገኘውን የአካባቢውን Department of Aging and Rehabilitative Services ለማግኘት፣ ቀጣዩን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡ https://www.vadars.org/offices.aspx።

### ለእርስዎ ለወላጅ የሚደረግ እገዛ

ወላጆች በእነዚህ ወሳኝ የሕይወት ደረጃዎች ላይ ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚኖርባቸውን ወሳኝ ጉዳዮች ለመዳሰስ ስድስት መምሪያዎችን ጽፈናል። መምሪያዎቹ የተዘጋጁት ዕድሎችን ለመለየት፣ አማራጮችን ለመመዘንና ውሳኔዎችን በሚገባ ለማስተናገድ ነው። የተግባር መዘርዝሮች፣ የጊዜ ሰሌዳዎች፣ ወርክሺቶችና ወደ ሌሎች ግብዓቶች የሚወስዱ ማስፈንጠሪያዎችም በተቻለ መጠን እንዲካተቱ ተደርጓል። እያንዳንዱ ሰነድም ወላጆችና ተዛማጅ ልምድና ብቃት ያላቸው ፕሮፌሽናሎች ባቀፈ ግብረ ሃይል ተገምግሟል። እባክዎ በቀጣዩ ድረ ገጾችን ላይ የሚገኘውን የ Transition POINTS ገጽ በመጎብኘት www.thearcofnova.org፣ እንደዚሁም የግብዓት ቤተ-መጽሓፍታችንን https://thearcofnova.org/programs-services/library/ በመጎብኘት ተጨማሪ አጋዥ ሰነዶችና ናሙናዎችን ማግኘት ይችላሉ።

The Arc of Northern Virginia መረጃ ሰጪ የሕይወት ዕቅድ አወጣጥና የወደፊት ዕቅድ አወጣጥ ቪድዮዎች ላይብረሪ እና YouTube ላይ የኢንተርኔት ውይይቶች ያሉት ሲሆን ይህንንም በቀጣዩ አድራሻ ያገኛሉ፡ https://www.youtube.com/user/VideosatTheArcofNoVA።

ምንም እንኳን እያንዳንዱ መምሪያ ከአንድ የሕይወት ምዕራፍ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚሸፍን ቢሆንም፣ እያንዳንዱ መምሪያ ወላጆችና ተንከባካቢዎች ወዳጆቻቸው ዕድሜያቸው 2፣ 22 ወይም 62 ዓመት ቢሆንም ማወቅ የሚያስፈልጋቸውን መረጃ ይደግማል፡ የወዳጅዎን የወደፊት ፋይናንስ እንዴት እንደሚጠብቁ፣ ለጥቅማ ጥቅሞች እንዴት እንደሚያመለክቱና እገዛ ለማግኘት ወዴት መሄድ እንዳለብዎት።

[1] Anderson, L.L., Larson, S.A., & Wuorio, A. (2011). 2010 FINDS National Survey Technical Report Family Caregiver Survey. Minneapolis: University of Minnesota, Research and Training Center on Community Living.

***መብቶችዎና ኃላፊነቶችዎ***

*ይህ የሕግ ሰነድ ባለመሆኑ እርስዎም ሆኑ ልጅዎ በሕጉ መሰረት ያሏችሁን መብቶችና ኃላፊነቶች አይዘረዝርም። በዚህ ሰነድ ውስጥ የቀረቡትን መረጃዎች ትክክለኛነት ለማጣራት የተቻለው ጥረት ሁሉ ተደርጓል፤ ነገር ግን የፕሮግራም ደንቦች፣ ቀነ ገደቦችና የግንኙነት አድራሻን የመሳሰሉ ጉዳዮች ሊቀየሩ እንደሚችሉ እባክዎ ይወቁ።*

*ወደ ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚደረጉ ማስተላለፎች ለመረጃ መስጠት ዓላማ ብቻ በመሆናቸው ለእነርሱ አገልግሎት ድጋፍ መስጠታችንን አያመለክትም። እባክዎ ማናቸውንም አስተያየቶች ወደ* Diane Monnig, The Arc of Northern Virginia, Transition POINTS, 2755 Hartland Road, Suite 200, Falls Church, VA 22043 dmonnig@thearcofnova.org *ይላኩ።*

## የአካል ጉዳተኛ ልጅዎን ቀጣይ ሕይወት አስተማማኝ ማድረግ

የአካል ጉዳተኛ ልጅ ወላጅ በመሆንዎ፣ ልጅዎ በቀኑ ውስጥ ያለውን አብዛኛውን ጊዜውን እንዴት ማሳለፍ እንዳለበት እርስዎና የት/ቤቱ ስርዓት የጋራ ኃላፊነት አለባችሁ። ሊሆን የሚችለው ሁኔታ ልጅዎ የሚኖረው ከእርስዎ ጋር ነው፣ ወደ ት/ቤት ይሄዳል፣ እና ምናልባትም በት/ቤት ስርዓት ስፖንሰር በተደረገ ወይም ሌሎች አቻዎቹ በሚሳተፉባቸው ተግባራት ውስጥ ይሳተፋል። ይሁን እንጂ፣ ልጅዎ ከት/ቤት ስርዓቱ አንዴ ከወጣ ከጎልማሶች አገልግሎት ኤጀንሲዎች አገልግሎት ለማግኘት የብቁነት መስፈርት ሊያሟላና የገንዘብ ድጋፍም ሊገኝ ይገባል። በብቁነት ላይ የተመሰረተ የመንግስት ትምህርት እና የጎልማሶች አገልግሎትን የማግኘት መብት መካከል ያለው ልዩነት ግራ አጋቢ ሊሆን ይችላል። ታዳጊ ጎልማሳ፣ ወላጆችና ቤተሰቡ የወደፊት ሕይወትን ግልጽ በማድረግና በማሰስ ረገድ የመሪነቱን ሚና መጫወት አለባቸው። ይህ ማለት በስራ ቅጥር፣ ትርጉም ያለው የእንክብካቤ አገልግሎት፣ መዝናኛና የቤት አገልግሎትን በመሳሰሉ መስኮች አገልግሎቶችን መመርመርና ለዚሁ መሟገት ማለት ነው። በተጨማሪም፣ ለልጅዎ ዘላቂ የፋይናንስ ዋስትና ሁኔታዎችን ማመቻቸትም ማለት ነው።

በ VCU ውስጥ የሚገኘው The Center on Transition Innovations በቀጣዩ ድረ ገጽ የመሸጋገሪያ ዕቅድ አወጣጥ ላይ ለወላጆች መረጃ ይሰጣል [www.centerontransition.org](http://www.centerontransition.org)።

1. ***ለልጅዎ ያልተገደበ ፍቅር ያሳዩ፣ በእርሱ ወይም በእርሷ ላይ እምነት ያሳድሩ፣ ማበረታቻ ይስጡት፣ ታላቅ ሕልም ያልሙ!*** *እርስዎ የልጅዎ ታላቅ ተሟጋች ነዎት። በዚህ አስደሳች ጊዜ ውስጥ ወላጆች በሚችሉት መጠን ድጋፍና ፍቅር ስጧቸው።*
2. ***የተማሪ ድምፅ እንዲሰማ ይታገሉ።*** *ተማሪውን የሚመለከት ጭውውት በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ የተማሪው ድምፅ መካተት አለበት።*
3. ***በሽግግር ሒደቱ ውስጥ የተማሪውን ተሳትፎ ያሳድጉ።*** *አካል ጉዳተኛ ለሆነ ታዳጊ ጎልማሳ በራስ የመወሰን አቅምን ለማሳደግ ታላቁ መንገድ በ IEP ሒደት አማካይነት ነው።*
4. ***ግብዓቶችን በማፈላለግ የቤት ስራዎን ይስሩ።*** *በሽግግር ሒደቱ ወቅት በቀላሉ በስሜት ሊዋጡ ይችላሉ። የተሻሉ አማራጮችና አሰራሮችን ማፈላለግ ለልጅዎ ለመሟገት ጠንካራ መሳሪያ ይሆንዎታል።*
5. ***አእምሮዎን ክፍት አድርገው ሰፋ ያለ አስተሳሰብ ይኑርዎት።*** *ከዚህ በፊት በጭራሽ ስላልተሰራ ብቻ ሊሰራ አይችልም ማለት አይደለም። ሽግግርን በሚመለከት ሃሳብ ላይ መወያየት ምንም ጉዳት አያስከትልም።*
6. ***ከጎልማሶች አገልግሎት ጋር ይተባበሩ።*** *የማህበረሰብ የጎልማሶች አገልግሎቶች ልጅዎ ከት/ቤት ስርዓት አንዴ ከለቀቀ በኋላ ጠቃሚ የሆነ ድጋፍና የፕሮግራም ዝግጅት ያቀርባሉ። የተለያዩ አገልግሎቶችን በተመለከተ መረጃ ማግኘትና ከአቅራቢዎች ጋር አስቀድሞ ግንኙነቶችን ማዳበር ወደ ጎልማሶች አገልግሎቶች የሚደረገውን ሽግግር ያቀለዋል።*
7. ***በሽግግሩ ዕቅድ አወጣጥ ሒደት ላይ የቤተሰብ ተሳትፎን ያሳድጉ።*** *ልጅዎ የ IEP ማዕከል እንዲሁም እርስዎ ልጅዎን በበለጠ ሁኔታ ያውቁታል! የቤተሰቡ ተሳትፎ በጨመረ ቁጥር የልጅዎ ድምፅም የበለጠ ይደመጣል።*

## በዚህ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ ጉዳዮች

አካል ጉዳተኛ ለሆነ ዕድሜው ከፍ ላለ ልጅ ውሳኔዎችን መወሰን የተወሳሰበ ነው። በዚህ ተግባር ላይ እንዲያግዝዎትም ይህ ሰነድ የሚከተሉትን ጉዳዮች ይመለከታል:

***አበይት የሆኑ የሕይወት ውሳኔዎችን ላይ ኃላፊነት ያለበት ማን እንደሆነ።*** *ወላጆች ለልጃቸው የበለጠ ነጻነት ለመስጠት የሚፈልጉ ሲሆን ይህም የልጁን ደህንነት ለማረጋገጥ ያስችላል። ሕጉ የአካል ጉዳተኛ ጎልማሳን ደህንነት ለማስጠበቅ የተለያዩ አማራጮችን የሚያስቀምጥ ሲሆን በዚህም ውስጥ የሞግዚትነት ውክልና ስልጣን እና የተቆጣጣሪነት ስልጣን ይገኝበታል።*

***ጎልማሳ ልጅዎ ለመንግስታዊ ድጋፍ ብቁ ስለመሆኑ።*** *አካል ጉዳተኛ የሆነ ጎልማሳ ከ18 ዓመት ዕድሜው ጀምሮ ከማሕበራዊ ዋስትና አስተዳደር ለሚሰጥ ወርሐዊ ገቢና ለ Medicaid ብቁ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ አካል ጉዳተኞችም ከመንግስት ገንዘብና ከ Medicaid አገልግሎቶች መሻሪያ ገንዘብ አጭርና ዘላቂ ጥቅማ ጥቅም ሊያገኙ ይችላሉ።*

***ምን ዓይነት ስራዎችና የእንክብካቤ አገልግሎቶች ስለመኖራቸው።*** *ለስራ ዕቅድ ማውጣት የሚጀምረው አንድ ልጅ የት/ቤት ስርዓቱን ከመልቀቁ በፊት ሆኖ ሙያዊ ምዘናዎችና (በሃሳብ ደረጃ) የተወሰኑ የበጎ ፈቃድ ስራ ልምድ ያስፈልገዋል። ልጅዎ ለጎልማሶች አገልግሎት ብቁ ሆኖ ከተገኘ፣ የአካባቢ አስተዳደሮች ሙያዊ ምዘና፣ እንደዚሁም ስራ ለማግኘት፣ ለመሰልጠንና ድጋፍ ለማግኘት ሊያግዙ ይችላሉ።*

***የትኞቹ የመዝናኛ ተግባራት የተሻሉ ስለመሆናቸው።*** *የመዝናኛ ተግባራት ሰዎችን ጤናማ አድርጎ ለማቆየትና ማህበራዊ መተንፈሻ እንዲያገኙ ለማስቻል ጠቃሚ ናቸው። የአካባቢ መንግስታትና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ቡድኖች አካል ጉዳት ላለባቸው ወጣት ጎልማሶች የመዝናኛና የስፖርት ፕሮግራሞችን ያቀርባሉ።*

***ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንዴት እንደሚንቀሳቀስ።*** *በሶስቱም የአካባቢ መስተዳድሮች ለአካል ጉዳተኞች የትራንስፖርት ስልጠና ይሰጣል። በተጨማሪም፣ በአሌክሳንድሪያ፣ አርሊንግተን እና ፌርፋክስ ውስጥ የሚሰሩ የአካባቢው የትራንስፖርት ድርጅቶች (አውቶብስ፣ የምድር ውስጥ ባቡርና ታክሲን ጨምሮ) ምቾትን ለመጨመርና የትራንስፖርት ወጪን ለመቀነስ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ያቀርባሉ።*

***የት እንደሚኖሩ።*** *ይህ ምናልባትም ወላጆች ሊያውቁት የማይቻላቸው ትልቅ ጉዳይ ሊሆን ይችላል - ልጃቸው የት እንደሚኖር። አንድ አካል ጉዳተኛ የሆነ ጎልማሳ ልጅ የት ለመኖር እንደሚችልና እንደሚፈልግ ለመወሰን ታሳቢ የሚያደርጋቸው ደህንነት፣ ተገኝነትና ምቾት ናቸው። የቤት አማራጮችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ቀጣዩን የ Arc of Northern Virginia መምሪያ ይመልከቱ፡ ለአካል ጉዳተኞች የሚሆን ቤት ማግኘት*
[https://thearcofnova.org/programs/transition/finding-home-adults-disabilities/](https://thearcofnova.org/programs/transition/finding-home-adults-disabilities/)

ልጅዎ ዕድሜው 22 ዓመት እስከሚሞላው ድረስ ትምህርቱን ባያጠናቅቅም እንኳን፣ ዕድሜው 18 ዓመት ሲሞላው መወሰድ ያለባቸው በርካታ እርምጃዎች አሉ። አሁኑኑ መወሰድ ያለባቸውን ውሳኔዎች ለማየት "የወላጆች የተግባር መዘርዝር" ውስጥ በተቻለ ፍጥነት የሚል ምልክት የተደረገባቸውን ተግባራት ይመልከቱ።

**ለራሳቸው እንዴት እንደሚሟገቱ።** የሽግግር ዕቅድ አወጣጥ ውጤት ላይ ከተማሪው የበለጠ ፍላጎት ያለው ሰው የለም። ተማሪው ንቁ መሆን አለበት፣ የሽግግር ቡድኑ ተሳታፊ አባልና የሁሉም ተግባራት ማዕከል መሆን አለበት። ለራስ መሟገት ክህሎቶች ውስጥ የመጀመሪያው ደረጃ የግል እውቀትን ማሳደግ ነው። ስለ አንድ ሰው ማንነት ማወቅ የትምህርት ዘይቤን፣ ጥንካሬና ድክመትን፣ ፍላጎትና ምርጫን መለየትን ያካትታል።

**ቀጣይ ሕይወትን አስተማማኝ ማድረግ፡ የወላጆች የተግባር መዘርዝር**

| በዕድሜ የሚወሰዱ እርምጃዎች | ንብረት/ ሕጋዊ | የኮሌጅ ትምህርት | ስራ/የቀን ድጋፍ | መዝናኛ | ትራንስፖርት | ቤት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **በተቻለ ፍጥነት** | | | | | | |
| ለአበይት ሰነዶች ፋይል ያዘጋጁ | x | | | | | |
| ኑዛዜ ያዘጋጁ | x | | | | | |
| የልዩ ፍላጎቶች ትረስት ያቋቋሙ | x | | | | | |
| አካል ጉዳት ያለበት **ልጅ** ለተጨማሪ የዋስትና ገቢ ብቁ መሆኑን ይወስኑ | x | | | | | |
| ግለሰቡ ለ Medicaid መሻሪያዎች ብቁ መሆኑን ይፈትሹ። የተጠባባቂዎች ዝርዝር ውስጥ ይግቡ። | ምናል | ባት | ረዥም | የተጠባባቂ ዎች | ዝርዝር | |
| **ዕድሜ ከ12-14 ዓመት** | | | | | | |
| የልጅዎን የተፈጥሮ ችሎታ፣ ሙያዊና የመዝናኛ ፍላጎቶች መዝግበው ይያዙ | | | x | x | | |
| ስለ ልጅዎ ፍላጎቶች ከአካባቢው የቴራፒ መዝናኛ መምሪያ ጋር ይወያዩበት | | | | x | | |
| **ዕድሜ ከ14-16 ዓመት** | | | | | | |
| የሽግግር ግቦችን በ IEP፣ እንደዚሁም በትራንስፖርት፣ በኮሌጅ እና ራስን ችሎ በመኖር ውስጥ ያካትቱ፤ በ DARS በሚዘጋጁ የቅድመ ስራ ቅጥር ስልጠና አገልግሎቶች ውስጥ ይሳተፉ | | x | x | x | x | |
| የሕዝብ ትራንዚት የሚጠቀሙ ከሆነ፣ የሜትሮ ዝቅተኛ ክፍያ መለያ ቁጥር ወይም የ MetroAccess ካርዶችን ያግኙ | | | | | x | |
| ከት/ቤት እና CSB ጋር በመሆን የጎልማሳ አገልግሎቶችን ብቁነት ይፈትሹ፤ የማመልከቻ እና የመረጃ መልቀቂያ ቅጾችን ይሙሉ | | | x | | | x |
| **ዕድሜ ከ16-18 ዓመት** | | | | | | |
| ወደ ኮሌጅ የሚገባ ከሆነ፣ ኮሌጆችን ይፈትሹና ካምፓሶችን ይጎብኙ፤ ከአካል ጉዳተኞች ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች ጋር ይገናኙ። | | x | | | | |
| የስራ ቅጥር እና/ወይም ትርጉም ያለው የእንክብካቤ አገልግሎቶን በተመለከተ መረጃ ያሰባስቡ፤ በውድድር ላይ የተመሰረተ የስራ ቅጥር ከሆነ ግቡ ከ DARS ኬዝ ያስከፍቱ | ብቁ | መሆን | ማለት | x<br>የ DARS | አገልግሎቶች ን ለማግኘት | ዋስትና አይደለም |
| አግባብነት ባለው የአካባቢ ኤጀንሲ (CSB) በኩል ለ**ጎልማሶች** አገልግሎት ብቁ መሆንን ይወስኑ | | | x | | | x |
| **ዕድሜ 17 ዓመት (ወይም ከት/ቤት ከመልቀቃቸው 12-18 ወራት በፊት)** | | | | | | |
| ወደ ኮሌጅ ለሚገቡ፣ አስፈላጊ ፈተናዎችን ይውሰዱ፤ ቃለ መጠይቆችንና ጉብኝቶችን ያመቻቹ። የአካል ጉዳተኞች አገልግሎት ቢሮን በማነጋገር ለካምፓስ ውስጥ አገልግሎቶች ብቁ መሆኑን ይወስኑ። | | x | | | | |
| የቅጥር/የእንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን አፈላልገው ቃለ መጠይቅ ያድርጉ | | | x | | | |

**ቀጣይ ሕይወትን አስተማማኝ ማድረግ፡ የወላጆች የተግባር መዘርዝር**

| በዕድሜ የሚወሰድ እርምጃ | ሐብት/ ሕጋዊ | የኮሌጅ ትምህርት | ስራ/የቀን ድጋፍ | መዝናኛ | ትራንስፖርት | መኖርያ ቤት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **የከፍተኛ ትምህርት በልግ ወቅት** | | | | | | |
| ለኮሌጅ ትምህርት ማመልከት | | x | | | | |
| **ከ17 ዓመት በታች፤ ከ6 ወራት በታች በፊት ያልሆነ** | | | | | | |
| የተደገፈ የውሳኔ አሰጣጥ፣ የትምህርትና የጤና እንክብካቤ ወይም የሞግዚትነት የውክልና ስልጣንን ጨምሮ የውሳኔ አሰጣጥ አማራጮችን ይፈትሹ። | x | | | | | |
| **የ18ኛ ዓመት ልደት በዓል ከመድረሱ 1 ወር በፊት** | | | | | | |
| ሞግዚትነት ለማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ፣ ለአዲስ ሕጋዊ ግንኙነት የመጨረሻ ሰነዶችን ለማዘጋጀት ከጠበቃ ጋር ይነጋገሩ። | x | | | | | |
| **በ18 ዓመት ዕድሜ** | | | | | | |
| ለተጨማሪ የዋስትና ገቢ (SSI) ያመልክቱ | x | | | | | |
| **በ18-22 ዓመት ዕድሜ** | | | | | | |
| ኑዛዜውን ወቅታዊ ያድርጉት። ለቤተሰብ ስለ ኑዛዜ፣ ትረስት፣ ሞግዚትነት፣ ወዘተ… ያሳወቁ። | x | | | | | |
| የጎልማሶች የመዝናኛና ማሕበራዊ አገልግሎቶችን ይፈትሹ | | | | x | | |
| የሕይወትና የስራ ታሪክ ያዘጋጁ፣ ሁኔታዊ ምዘናዎችን ያካሂዱ፣ ለስራ ቃለ መጠይቅ ይሂዱ | | | x | | | |
| ለ SSI አንዴ ተቀባይነት ካገኙ፣ ለ Medicaid ያመልክቱ። | x | | | | | |
| ስራ እየሰሩ ከሆነ፣ የስራ ገቢና የማሕበራዊ ዋስትና ጥቅማ ጥቅሞችን ስለማስተዳደር መረጃ ያግኙ። | x | | | | | |
| ቀደም ሲል ያላደረጉት ከሆነ፣ የ Medicaid መሻሪያዎችን ብቁነት በመወሰን ከ CSB ጋር ተነጋግረው የመነሻ መረጃዎችን ያግኙ። | x | | | | | |
| እስካሁን ካላደረጉት፣ የሜትሮ ቅናሽ ዋጋ የትራንዚት ፈርካርዶች/የመታወቂያ ካርድ ያግኙ፤ ለ Metro Access ያመልክቱ | | | | | x | |
| ለወደፊቱ ዕቅድ ሲያወጡ የቤት ግብዓቶችን ይፈትሹ | | | | | | x |
| **ዕድሜ ከ20-22** | | | | | | |
| ትምህርቱን ከማጠናቀቁ በፊት፣ ለስራ ቅጥር ወይም ለእንክብካቤ አገልግሎት የልጅዎን ፍላጎቶች በተሻለ ሁኔታ የሚያሟላ አገልግሎት ሰጪን ወስነው ይምረጡ | | | x | | | |
| የሕዝብ ትራንስፖርት ወይም ልዩ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ተጠቃሚነት በተመለከተ ይወስኑ። የጉዞ ስልጠናን ይዳስሱ። | | | | | x | |

**ድሕረ ሞት የሐብትና ንብረት ማስተላለፊያ ዕቅድ**

***ግብ፡*** *ጉልማሳ ልጅዎ ብቁ የሆነበትን የፌዴራልና የግዛት ጥቅማ ጥቅሞች ማግኘቱንና የወላጅ ሞት ወይም አካል ጉዳት ቢከሰት እንክብካቤ እንደሚደረግለት ማረጋገጥ።*

| ***እርምጃ መቼ እንደሚወሰድ*** | ***ምን መደረግ አለበት*** | ***ማገዝ የሚችለው ማነው*** |
|---|---|---|
| ***አጠቃላይ የፋይናንስ ዕቅድ አወጣጥ*** <br> ***በተቻለ ፍጥነት*** | እርስዎ ከሞቱ በኋላ ሐብቶችዎ እንዴትና ለማን እንደሚከፋፈሉ ፍላጎቶችዎ ይፈጸሙ ዘንድ **ኑዛዜ** ወሳኝ ነው። አካል ጉዳተኛ ልጅ ካለዎት፣ <br> ለመንግስት ጥቅማ ጥቅሞችና አገልግሎቶች ብቁነታቸውን ለማስጠበቅና በወንድምና እህት አማቾችና በቤተሰብ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ይፈልጋሉ። | ስለ ኑዛዜና ድሕረ ሞት የሐብት ክፍፍል በተመለከተ ዕድሜው ጠና ያለ የሕግ ጠበቃ ያነጋግሩ። የልዩ ፍላጎቶች ትረስት ተብሎ የሚጠራ ሌላ ሰነድ አካል ጉዳት ላለበት ልጅ መዘጋጀት አለበት (ከታች ተመልከት)። <br><br> አንዳንድ ቤተሰቦችም የፋይናንስ ፕላነር ማማከር ጠቃሚ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ። |
| ***የልዩ ፍላጎቶች ትረስት*** <br> ***በተቻለ ፍጥነት*** | አካል ጉዳተኛ ሰው ለፌዴራል ጥቅማ ጥቅሞች ፕሮግራሞች ያለው ብቁነት እንደተጠበቀ ሆኖ ያልተገደበ ሐብት በትረስት ውስጥ እንዲቀመጥለት የሚያስችለው የልዩ ፍላጎቶች ትረስት ያቋቁሙ። <br><br> SNT በማቋቋም አንድ ሰው፣ ወላጅ፣ አሳዳጊ ወይም ፍ/ቤት ወይም አያት አካል ጉዳት ያለበትን ሰው ሐብቶች በማስተላለፍ ለፌዴራል ጥቅማ ጥቅሞች እንዲያመለክት ወይም እነዚህን ጥቅማ ጥቅሞች ጠብቆ ለማቆየት እንዲችል ያድርጉ። | የልዩ ፍላጎቶች ትረስትን በተመለከተ ጠቅላላ መረጃ ለማግኘት፣ ቀጣዩን የ Special Needs Trust Alliance ድረ ገጽን ይጎብኙ፡ [https://www.specialneedsalliance.org/](https://www.specialneedsalliance.org/) <br><br> The Arc of Northern Virginia ለቤተሰቦችና አካል ጉደተኛ ሰው ገንዘቡን መቆጠብና ኢንቨስት ለማድረግ የሚያስችለው ተመጣጣኝ መንገድ በመፍጠር የግለሰቡን ሕይወት ለማሳደግ የሚያስችል የልዩ ፍላጎቶች ትረስት ፕሮግራም ያቀርባል። ተጨማሪ መረጃ ከቀጣዩ ድረ ገጽ ያገኛሉ [www.thearcofnovatrust.org](http://www.thearcofnovatrust.org) <br><br> የ The Arc of Northern Virginia የትረስት ፕሮግራምን የማይጠቀሙ ከሆነ፣ የልዩ ፍላጎቶች ትረስትን ስለመጻፍ በአረጋውያን እንክብካቤ ሕግ ስፔሻላይዝ ያደረገ ጠበቃና የልዩ ፍላጎቶች ትረስትን ያነጋግሩ። *እነዚህን ሰነዶች ማዘጋጀት የሚችሉት ሁሉም ጠበቆች አይደሉም።* የ The Arc of Northern Virginia ኦንላይን አቅራቢን ዳይሬክተሪ [https://thearcofnova.org/directory/](https://thearcofnova.org/directory/) ይመልከቱ |
| ***የፍላጎት መግለጫ ደብዳቤ*** <br> ***በተቻለ ፍጥነት*** | ይህ ሰነድ የልጅዎን ሕይወት፣ እንደዚሁም ለወደፊት ሕይወቱ ያለዎትን ምኞት የተመለከቱ ዝርዝር መረጃዎችን ያቀርባል። ሕጋዊ አስገዳጅነት ባይኖረውም፣ የልጅን እንክብካቤ ሊረከቡ ለሚችሉ አካላት ጠቀሜታው የጎላ ነው። | . |

**ድሕረ ሞት የሐብትና ንብረት ማስተላለፊያ ዕቅድ**

***ግብ፡*** *ጐልማሳ ልጅዎ ብቁ የሆነበትን የፌዴራልና የግዛት ጥቅማ ጥቅሞች ማግኘቱንና የወላጅ ሞት ወይም አካል ጉዳት ቢከሰት እንክብካቤ እንደሚደረግለት ማረጋገጥ።*

| ***መቼ እርምጃ ይወሰዳል*** | ***ምን መደረግ አለበት*** | ***ማገዝ የሚችለው ማነው*** |
|---|---|---|
| ***የተጨማሪ ዋስትና ገቢ (SSI)*** | | |
| አካል ጉዳት ላለበት **ልጅ** በተቻለ ፍጥነት የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች | የእርስዎ ***ልጅ* (ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች)** ለ SSI ብቁ ሊሆን እንደሚችል ይወስኑ።ልጁ የማሕበራዊ ዋስትና አስተዳደርን ጥብቅ የሆነ የአካል ጉዳተኝነት ትርጉም ማሟላትና ጥቂት ወይም ምንም የፋይናንስ ሐብት ያለው መሆን አለበት። *የወላጆች ሐብትና ገቢ ከግምት ውስጥ ይገባል።* | አብዛኛውን የማመልከቻ ቅጹን ለመሙላት ቀጣዩን ድረ ገጽ መጎብኘት ይችላሉ [http://www.socialsecurity.gov/pgm/ssi.htm](http://www.socialsecurity.gov/pgm/ssi.htm) በተጨማሪም ወደ 1-800-772-1213 ደውለው ከማሕበራዊ ዋስትና ተወካይ ጋር ቀጠሮ እንዲያዝልዎት በመጠየቅ ማመልከቻውን በስልክ ወይም በአካል መሙላት ይችላሉ። ለማመልከትና ጥቅማ ጥቅሞችን ለማስተዳደር አጠቃላይ ደንቦችን በተመለከተ እገዛ ካስፈለገዎት ይህን ይጎብኙ [http://www.vaaccses.org/wipa/](http://www.vaaccses.org/wipa/)። በ Northern VA ውስጥ የማህበረሰብ ስራ ማትጊያ አስተባባሪ የሆኑትን Marilyn Morrison, በ vaACCSES ስልክ ቁጥር 571-339-1305 [mmorrison@vaaccses.org](mailto:mmorrison@vaaccses.org) *ያነጋግሩ።* |
| በ18 ዓመት ዕድሜ ለአካል ጉዳተኛ ጎልማሳ የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች | አካል ጉዳተኛ ***ጎልማሳ*** ለ SSI ያለውን ብቁነት ይወስኑ። አካል ጉዳት ያለበት ጎልማሳ የስራ እንቅስቃሴ አካል ጉዳትንና የገቢ/ሐብት መስፈርቶችን (በራሳቸው ስም ከ $2,000 ያነሰ ሐብት መኖር) ማሟላት አለበት። *የወላጆች ገቢ እና ሐብቶች ከግምት ውስጥ አይገቡም*<br><br>ጎልማሳው ልጅዎ የአካል ጉዳተኝነትና የገቢ መስፈርቶችን ካሟላ ***ለ*** SSI ***ያመልክቱ።*** | ማመልከቻዎን ለመጀመር ቀጣዩን ድረ ገጽ ይጎብኙ [http://www.socialsecurity.gov/pgm/ssi.htm](http://www.socialsecurity.gov/pgm/ssi.htm) በተጨማሪም ወደ 1-800-772-1213 ደውለው ከማሕበራዊ ዋስትና ተወካይ ጋር ቀጠሮ እንዲያዝልዎት በመጠየቅ ማመልከቻውን በስልክ ወይም በአካል መሙላት ይችላሉ።<br><br>ማስታወሻ፡ ከማሕበራዊ ዋስትና ተወካይ ጋር ከመገናኘትዎ በፊት ቅጾቹን ለመሙላትና ደጋፊ ሰነዶችን ለማዘጋጀት ይሞክሩ።<br><br>ማስታወሻ፡ የማሕበራዊ ዋስትና ጥቅማ ጥቅሞችን የሚያገኘውን አካል ጉዳተኛ ልጅዎን የቤተሰቡ ቤት ውስጥ በመኖሩ ኪራይ እንዲያስከፍሉት ይመከራሉ፤ የሚጠየቀው የኪራይ ክፍያ አሁን ከሚያገኘው ከፍተኛው ጥቅማ ጥቅም ቢያንስ 30 በመቶ መሆን አለበት። ለዝርዝሩ የማሕበራዊ ዋስትና ደንቦችን ይመልከቱ። |
| አንዴ የማሕበራዊ ዋስትና ጥቅማ ጥቅሞች ከተቀበሉ | ተጠቃሚው ማንኛውንም ገቢውን ለማሕበራዊ ዋስትና ሪፖርት ማድረግ ያለበት ሲሆን፣ በዚህም ውስጥ ከስራ የሚገኝ ገቢ፣ የአንድ ግዜ ገቢ፣ የልጆች ድጋፍ ወይም ከትረስት የሚገኝ ክፍያን ይጨምራል። | |

**ድሕረ ሞት የሐብትና ንብረት ማስተላለፊያ ዕቅድ**
**ግብ፡** ጐልማሳ ልጅዎ ብቁ የሆነበትን የፌዴራልና የስቴት ጥቅማ ጥቅሞች ማግኘቱንና የወላጅ ሞት ወይም አካል ጉዳት ቢከሰት እንክብካቤ እንደሚደረግለት ማረጋገጥ።

| ***መቼ እርምጃ ይወሰዳል*** | ***ምን መደረግ አለበት*** | ***ማገዝ የሚችለው ማነው*** |
|---|---|---|
| ***የውሳኔ አሰጣጥ አማራጮች*** እና ***ሕጋዊ ስልጣንን*** ይፈትሹ<br>በ 17 ዓመት ዕድሜ ላይ | የሚደገፍ ውሳኔ አሰጣጥን እና የአካል ጉዳተኛ ጎልማሳን ውሳኔ አሰጣጥ የሚመሩ የተለያዩ ሕጋዊ ግንኙነቶችን ዓይነት ጥቅምና ጉዳት በተመለከተ መረጃ ያፈላልጉ። ያሉት አማራጮች ከተወካይ ተከፋይ እስከ ሞግዚትነትና የግልሰብ ተቆጣጣሪነት ይደርሳሉ። | የተደገፈ የውሳኔ አሰጣጥን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት፣ http://www.supporteddecisionmaking.org/። የተለያዩ የሕጋዊ ስልጣን አማራጮችን የተመለከቱ መረጃዎችና የውክልና ስልጣን ማስረጃ ናሙናዎችን ለማግኘት፣ የ Disability Law Center of Virginia ድረ ገጽን ይጎብኙ www.dlcv.org። የትምህርት የውክልና ስልጣን ናሙና እዚህ ይገኛል https://www.fcps.edu/sites/default/files/media/forms/se340.pdf |
| ከ17 ዓመት ከ6 ወር በፊት አይደለም | ሞግዚትነትን በቁምነገር እያሰቡበት ከሆነ፣ በአረጋውያን እንክብካቤ እና በአካል ጉደተኝነት ሕግ ላይ ልምድ ያለውን ጠበቃ ያነጋግሩ። | |
| ከ8ኛ ዓመት የልደት ቀን 1 ወር በፊት | ሞግዚነትን በጥብቅ እየተከታተሉ ከሆነ ጠበቃው የመጨረሻዎቹን ሰነዶች እንዲያዘጋጅ ያድርጉ። | በሞግዚትነቱ ጉዳይ ሲቀጥሉበት እንደሚፈልጉ ለመወሰን እንዲያግዝዎ፣ በመረጃ ቤተመጻሕፍታችንችን ውስጥ ቀጣዩን ይጎብኙ "Thinking About Guardianhip Checklist" https://thearcofnova.org/programs-services/library/<br><br>ከቨርጂኒያ የሞግዚትነት ማህበር መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ፡ www.vgavirginia.org።<br><br>በ The Arc of Northern Virginia የአገልግሎት አቅራቢዎች የአድራሻ ዝርዝር ውስጥ በኦንላይን የተዘረዘሩትን ጠበቆች እዚህ ይመልከቱ፡ https://thearcofnova.org/directory/ |
| ***የMedicaid የጤና ኢንሹራንስ***<br>በተቻለ ፍጥነት | *ልጅዎ ለ SSI ብቁ ከሆነ፣ ወዲያውኑ ለ Medicaid ብቁ ይሆናል።* ማመልከቻውን መሙላት ያስፈልግዎታል። | |
| ***የግል ጤና ኢንሹራንስ*** | የዕድሜ ልክ አካል ጉዳት ያለበት ሰው በወላጆቹ ኢንሹራንስ ውስጥ ላልተወሰነ ጊዜ መቆየት ይችላል። ለአዳዲስ የኢንሹራንስ ዕቅዶች፣<br>ዕድሜያቸው ከ19 ዓመት በታች ለሆናቸው ልጆች አካል ጉዳት አስቀድሞ ያለ ሁኔታ ተደርጎ አይቆጠርም። | www.dmas.virginia.gov ለጠቅላላ መረጃ። ይሁን እንጂ፣ በአካባቢዎ የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ በኩል ማመልከት አለብዎት፤ *ቀደም ሲል SSI ማግኘት የጀመሩ ከሆነ፣ የMedicaid አጭር ቅጽ እንዲሰጥዎ ይጠይቁ።*<br>***አሌክሳንድሪያ፡*** የሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት፣ (703)746-5700<br>***አርሊንግተን፡*** DHS/DD አገልግሎቶች፣ (703)228-1300<br>***ፌርፋክስ፡***የቤተሰብ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት፣ (703)324-7500 |

***ድሕረ ሞት የሐብትና ንብረት ማስተላለፊያ ዕቅድ***

***ግብ፡*** *ጐልማሳ ልጅዎ ብቁ የሆነበትን የፌዴራልና የስቴት ጥቅማ ጥቅሞች ማግኘቱንና የወላጅ ሞት ወይም አካል ጉዳት ቢከሰት እንክብካቤ እንደሚደረግለት ማረጋገጥ።*

| ***እርምጃ መቼ እንደሚወሰድ*** | ***ምን መደረግ አለበት*** | ***ማገዝ የሚችለው ማነው*** |
|---|---|---|
| ***የMedicaid መሻሪያ ፕሮግራሞች በተቻለ ፍጥነት****የተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ መግባት* | ID/DD ያለባቸው ሰዎች በ Medicaid መሻሪያ ፕሮግራሞች ስር ላሉ አገልግሎቶችም ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።<br><br>የቨርጂኒያ ግዛት የመሻሪያ ምድቦችን በገንዘብ የሚደግፍ ቢሆንም ይህ የገንዘብ ድጋፍ ግን በመላው ግዛቱ ውስጥ ያለውን ፍላጎት ለመሸፈን በቂ አይደለም። | የ The Arc of Northern Virginia ድረ ገጽን ይመልከቱ፡ https://thearcofnova.org/programs/waivers/all-about-waivers/<br>ለጠቅላላ መረጃ፣ http://mylifemycommunityvirginia.org/ ለ DD መሻሪያ ለማመልከት በካውንቲዎ የሚገኘውን Community Services Board ያነጋግሩ<br>የአሌክሳንድሪያ ከተማ CSB (703)746-3400<br>የአርሊንግተን DHS/DD አገልግሎቶች፡ (703)228-1700<br>የፌርፋክስ/ፎልስ ቸርች CSB/DD አገልግሎቶች፡ (703)-324-4400<br><br>ለ CCC Plus መሻሪያ የካውንቲዎን የማሕበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ ያነጋግሩ<br>አሌክሳንድሪያ ከተማ፡ (703)746-5700<br>አርሊንግተን ካውንቲ፡ (703)228-1350<br>ፌርፋክስ ካውንቲ፡ (703)324-7948 |
| ***የስራ ቅጥር/ትርጉም ያለው የእንክብካቤ ድጋፍ አገልግሎቶች በተቻለ ፍጥነት*** | ልጅዎ ለስራ ቅጥር ወይም ለእንክብካቤ አገልግሎቶች ብቁ መሆኑን የመወሰን ሒደቱን ከአካባቢዎ ይጀምሩ።<br><br>**ልጅዎ በአካባቢው Community Development Board የገንዘብ ድጋፍ እንዲደረግለት የዕድገት መዘግየት አካል ጉዳት እንዳለበት በምርመራ ሊረጋገጥና የትግበራ ደረጃ መስፈርቶችን ሊያሟላ ይገባል።**<br>የማመልከቻ ቅጽ መሙላት፣ የልጅዎን ስነ-ልቦናዊ ምርመራ ውጤት ማቅረብና DHS ማናቸውም አስፈላጊ የሕክምና/ስነ-ልቦናዊ መረጃዎችን እንዲያይ የሚፈቅድ ቅጽ መፈረም አለብዎት። | |

**የኮሌጅ ትምህርት፣ የስራ ቅጥርና የእንክብካቤ አገልግሎቶች**

**ግብ፡** ልጅዎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ አግባብነት ያለው የኮሌጅ ትምህርት፣ የስራ ዕድል፣ የበጎ ፈቃድ እና/ወይም የእንክብካቤ ተግባራትን እንዲያገኝ ማመቻቸት።

| ***መቼ እርምጃ እንደሚወሰድ*** | ***ምን መደረግ አለበት*** | ***ማገዝ የሚችለው ማነው*** |
|---|---|---|
| ***ሙያዊ ምዘና***<br><br>ዕድሜ ከ12-14 ዓመት | የልጅዎን ፍላጎቶችና ጥንካሬዎች፣ የስራ ዘመን ማፈላለጊያ ተግባራትና ክህሎቶችን መመዝገብ ይጀምሩ<br><br>የት/ቤት ተግባራት ልጅዎን ለስራ ቅጥር ዕድሎች ሊያዘጋጁ የሚችሉባቸውን መንገዶች ከመምህራን ጋር ሆነው ይወስኑ | ሙያዊ ምዘናዎች እና የስራ ቅጥር አገልግሎቶች ከምረቃ በፊት ሊመቻቹ ይችላሉ፤ ይህም ብቁ ከሆኑና የገንዘብ ድጋፍ ዝግጁ ሲሆን የሚደረግ ሆኖ በአካባቢዎ የት/ቤት ስርዓት፣ በ Community Services Board, እና/ወይም በ Virginia Dept. for Aging & Rehabilitative Services (DARS) አማካይነት የሚከናወን ነው። |
| ዕድሜ ከ14-16 ዓመት | IEPs የኮሌጅ ትምህርትና በ14 ዓመት ዕድሜ ራስን ችሎ የመኖር ግቦችን ማካተት አለባቸው | |
| ዕድሜ ከ16-22 ዓመት | ቀደም ሲል ካላደረጉት፣ አግባብነት ባለው የአካባቢ ኤጀንሲ በኩል ልጅዎ ለጎልማሶች አገልግሎት ብቁ መሆኑን ይወስኑ፤<br>በዚህም ውስጥ ከ Department of Aging & Rehabilitative Services (DARS) እና ከ CSB የሚገኝ ድጋፍ ይካተታል። የት/ቤት ሽግግር ተወካይዎ እና የ CSB የድጋፍ አስተባባሪ ይህን ሒደት ለመፈተሽ ሊያግዙዎት ይችላሉ። | DARS በት/ቤት ውስጥ የቅድመ ስራ ቅጥር የስልጠና አገልግሎቶችን የሚሰጥ ሲሆን አካል ጉዳተኛ ጎልማሶች ውድድር ባለበትና በተቀናጀ የስራ ቅጥር ውስጥ ለመስራት እንዲዘጋጁ የሚያስችል የአጭር ጊዜ ድጋፍ ሊያቀርብ ይችላል። ተማሪዎች የ DARS የብቁነት መስፈርት ማሟላት አለባቸው። ስለ DARS ተጨማሪ መረጃዎችን በቅጥያው ላይ ያገኛሉ። www.vadrs.org<br><br>ልጅዎ በሚማርበት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ያሉት የሽግግር ተወካይ የኮሌጅ ትምህርትና የስራ ቅጥር አማራጮችን በተመለከተ መረጃ ለመስጠት በቅድሚያ መጠየቅ ያለበት ሰው ነው። |

**የኮሌጅ ትምህርት፣ የስራ ቅጥርና የእንክብካቤ አገልግሎቶች**

**ግብ፡** *ልጅዎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ አግባብነት ያለው የኮሌጅ ትምህርት፣ የስራ ዕድል፣ የበጎ ፈቃድ እና/ወይም የእንክብካቤ ተግባራትን አንዲያገኝ ማመቻቸት።*

| **እርምጃ መቼ እንደሚወሰድ** | **ምን መደረግ አለበት** | **ሊያግዝ የሚችለው ማነው**<br>***የአርሊንግተን ት/ቤቶች የሽግግር አስተባባሪዎች***<br><br>Joy Haley, Yorktown HS<br>(703)228-2545 joy.haley@apsva.us<br><br>Christina Eagle, Arlington Career Center (703)228-5738<br>Christinaeagle@apsva.us<br><br>Thomas Sweet, Washington-Liberty<br>(703)228-6265<br>thomas.sweet@apsva.us<br><br>Jennifer DeCamp, Wakefield HS<br>703-228-6728<br>Jennifer.decamp@apsva.us<br><br>Joyce Kelly, Stratford Program<br>703-228-6450<br>joyce.kelly@apsva.us<br><br>Brian Stapleton, Contract Services<br>703-228-6360<br>Brian.stapleton@apsva.us<br><br>***የፌር ፋክስ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች***<br>**የስራ ዘመንና የሽግግር አገልግሎቶች**<br><br>Janelle Ellis, Coordinator (571)423-4150. ፌር ፋክስ በ29 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና ማዕከሎች ውስጥ የስራ ቅጥርና የሽግግር ተወካዮች አሉት። ስለእነዚህ አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ፡ https://www.fcps.edu/academics/academic-overview/special-education-instruction/career-and-transition-services |
|---|---|---|

**የኮሌጅ ትምህርት፣ የስራ ቅጥርና የእንክብካቤ አገልግሎቶች**

***ግብ፡*** ልጅዎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ አግባብነት ያለው የኮሌጅ ትምህርት፣ የስራ ዕድል፣ የበጎ ፈቃድ እና/ወይም የእንክብካቤ ተግባራትን እንዲያገኝ ማመቻቸት።

| ***እርምጃ መቼ እንደሚወሰድ*** | ***ምን መደረግ አለበት*** | ***ማገዝ የሚችለው ማነው*** |
|---|---|---|
| በ12-17 ዓመት ዕድሜ | የስራ ቅጥርና የእንክብካቤ አገልግሎቶችን ስለሚሰጡ ድርጅቶች መረጃ በጽሑፍና በኦንላይን ማቴሪያሎችና በመረጃ መስጫ ትርኢቶች አማካይነት ያፈላልጉ | ***የአገልግሎት አቅራቢ መረጃ ሰጪ ትርዒቶች።*** የአርሊንግተን እና ፌርፋክስ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች በበልግ ወቅት አመታዊ ትርዒቶችን ያዘጋጃሉ።<br><br>***የላቀ መሸጋገሪያ ቅዳሜ*** በ FCPS የሚስተናገድ ሆኖ በአንደኛና በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ የሚያተኩርና በክረምት ወቅት የሚካሄድ ነው። |
| በ17 ወይም 18 ዓመት ዕድሜ ላይ ት/ቤትን ከመልቀቅ በፊት | ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር ስብሰባዎችን ለማመቻቸት ሊያግዝዎ የሚችል የሽግግር ተወካይ ጋር ይገናኙ ወይም ራስዎ የሚገናኙበትን ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ<br><br>ልጅዎ ከመመረቁ በፊት የድጋፍ ፍላጎቶቹን በተሻለ ሁኔታ የሚያሟሉለትን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በመወሰን ብቁነቱንም ይወስኑ | ***ወደፊት ማስቀጠል።*** ድሕረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና የስራ ቅጥር አማራጮች። በየዓመቱ የሚካሄድና በፌርፋክስ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የሚስተናገድ ነው።<br><br>**Future Quest** (George Mason Univ.) ለአንደኛ ደረጃና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በየሁለት ዓመቱ የሚዘጋጅ የኮሌጅ/የስራ ዘመን የሚመለከት ዝግጅት ነው፤ ቀጣዩ ዝግጅት አክቶበር 2019 ላይ ይካሄዳል |
| ***የኮሌጅ አካዳሚያዊ አማራጮች*** | ልጅዎ የኮሌጅ ትምህርት ለመማር ፍላጎት ካለው፣ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ኮርሶችን እንዲወስዱ እና/ወይም ዲግሪ እንዲያገኙ የሚያግዙ በርካታ ፕሮግራሞች አሉ። | |
| ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከመልቀቅ 2 ዓመት በፊት | የኮሌጅ ፕሮግራሞችን አፈላልገው ከተማሪው ጋር ሆነው ጉብኝት በማድረግ ከአካል ጉዳት አገልግሎቶች ተወካይ ጋር በካምፓስ ውስጥ ይገናኙ።<br><br>አስፈላጊ ፈተናዎችን ይውሰዱ፤ ቃለ መጠይቆችና ተጨማሪ ጉብኝቶችን ያመቻቹ | በተጨማሪም፣ ለአካል ጉዳተኞች በድሕረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ያተኮረውን ኦንላይን clearinghouse የሆነውን the Heath Center በቀጣዩ ድረ ገጽ ይጎብኙ [www.heath.gwu.edu](http://www.heath.gwu.edu) ለሌሎች አማራጮች ይህን ይመልከቱ፡ [www.thinkcollege.net](http://www.thinkcollege.net) |
| የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመጀመሪያ ዓመት | | |
| የመጨረሻ ዓመት ወቅት | ለድሕረ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ወይም ፕሮግራሞች ያመልክቱ | የድሕረ ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን ከቅጥያው ላይ ይመልከቱ |

***መዝናኛ***

**ግብ፡** ልጅዎ በመዝናኛና ዘና በሚያደርጉ ተግባራት ውስጥ እንዲሳተፍ ለማስቻል።

**እርምጃ መቼ እንደሚወሰድ**

በ12 ዓመት ዕድሜ

ከ12 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ በልጁ ዕድሜ ሙሉ እንዳስፈላጊነቱ ይደጋገማል።

ከ18 ዓመት በላይ

ትምህርት ለመማር ዝግጁ ሲሆን

***ምን መደረግ አለበት***

የልጅዎን ፍላጎቶችና ጥንካሬዎች መመዝገብ ይጀምሩ።

ማናቸውንም አስፈላጊ የመስተንግዶ ቅጾች ይሙሉ፤ ይህ እንደየአካባቢው ይለያያል። እነዚህ በየዓመቱ የሚሻሻሉ ሆነው እስከ አዋቂነት ዕድሜ ድረስ ይቀጥላሉ።

የታዳጊ ጎልማሳዎ ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ ተግባራት የትኞቹ እንደሆኑ ለመወሰን በአካባቢዎ የሚገኘውን የቴራፒ መዝናኛ ቢሮ ያነጋግሩ ወይም ከመምህሩ/የኬዝ ተጠሪው ጋር ይነጋገሩ።

ለ TR/ለውርስ ፕሮግራሙ አዲስ ከሆኑ፣ የብቃት ማረጋገጫ ካለው የቴራፒ መዝናኛ ስፔሻሊስት (CTRS) ጋር መረጃ ለመለዋወጥ ይጠይቁ

ለቴራፒ መዝናኛ ቢሮው ደውለው ይመዝገቡ፤ አስፈላጊ ከሆነም መስተንግዶ ይጠይቁ።

የአካባቢዎ መስተዳድርም በአጠቃላይ የመዝናኛ (non-TR) መማሪያ ክፍሎች ወይም ካምፖች ውስጥ መስተንግዶን ሊያመቻች ይችላል። የማረፊያ አገልግሎት በቅድሚያ መጠየቅዎን እርግጠኛ ይሁኑ።

በርካታ የግል ድርጅቶች የራሳቸው የመረጃ መሰብሰቢያና የምዝና ሒደቶች አሏቸው። ነጻ ምዘና ወይም ቅበላ መኖሩን መጠየቅዎን እርግጠኛ ይሁኑ። ለፕሮግራሞች የማረፊያ አገልግሎት ሲጠይቁ፣ ለማቅረብ ፈቃደኛ የሆኑት እና/ወይም የሚችሉት የማረፊያ አገልግሎት የትኛው እንደሆነ ይጠይቁ።

***ማገዝ የሚችለው ማነው***

***አሌክሳንድሪያ***

Alexandria Recreation, Parks & Cultural Activities, Therapeutic

https://www.alexandriava.gov/recreation/info/default.aspx?id=45758

703-746-5422

***አርሊንግተን***

Department of Parks and Recreation Therapeutic Recreation Office

https://parks.arlingtonva.us/therapeutic-recreation/

703-228-4740

***ፌር ፋክስ***

Fairfax Therapeutic Recreation Services

https://www.fairfaxcounty.gov/neighborhood-community-services/therapeutic-recreation

703-324-5532

POAC (የኦቲስቲክ ልጆች ወላጆች) የመዝናኛ አገልግሎቶችን ዝርዝር ይይዛል። ይህን ይጎብኙ፡ https://poac-nova.org/wp-content/uploads/2018/02/Adapted-sports-and-rec-list-2018.pdf

የ FCPS የወላጆች መረጃ ማዕከል የካምፖችን ዝርዝር ይይዛል https://www.fcps.edu/node/31344

የመንግስትና የግል ድርጅቶች ለአካል ጉዳተኞች የስፖርት፣ ማሕበራዊና የቴራፒ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ የአቅራቢዎቻችንን የአድራሻ ዳይሬክተሪ ይመልከቱ https://thearcofnova.org/business-directory/

**የትራንስፖርት አገልግሎት**

**ግብ፡** የትራንስፖርት ክህሎቶችን በማስተማርና ዝቅተኛ ወጪ ያላቸውን የትራንስፖርት አማራጮች በመጠቀም ወደ/ከተግባራት ራሳቸውን ችለው ለመድረስ እንዲችሉ ማድረግ

| **እርምጃ መቼ እንደሚወሰድ** | **ምን መደረግ አለበት** | **ማገዝ የሚችለው ማነው** |
|---|---|---|
| ከ12 ዓመት ጀምሮ | ልጁ የጉዞ ክህሎቶችን ለማመር ያለውን ዝግጁነትና ማስተማር የሚገቡ ክህሎቶችን ከግምት ውስጥ ያስገቡ | https://www.dmv.virginia.gov/drivers/#id/get_id.asp |
| አንዴ ልጅ/ጎልማሳ ከቤት ውጥቶ መሄድ እንደጀመረ | ከቨርጂኒያ የሞተር ተሽከርካሪዎች መምሪያ የመንጃ ፈቃድ ያልሆነ የመታወቂያ ካርድ ይቀበሉ። እነዚህ ካርዶች የዕድሜ ገደብ የሌላቸው ሲሆን የተለማማጅ ፈቃድ ወይም የመንጃ ፈቃድ ላልያዘ ማንኛውም ሰው የሚሰጡ ናቸው። | ENDependence Center of Northern Virginia የጉዞ ስልጠና ከክፍያ ነጻ ያቀርባል። www.ecnv.org 703-525-3268<br><br>የ IEP ስብሰባ ከመካሄዱ በፊት የልጅዎን ት/ቤት የሽግግር አስተባባሪ እና/ወይም በት/ቤት ያሉትን የልዩ ትምህርት ድጋፍ አስተባባሪ ያነጋግሩ |
| በ12 ዓመት - ምርቃት | የጉዞ ክህሎት ግቦችን በ IEP እና በሽግግር ዕቅድ ውስጥ ያካትቱ | የሜትሮን የቅናሽ ታሪፍ መታወቂያ ካርድ ማመልከቻ ለማውረድ፣ ይህን ይመልከቱ፡ https://www.wmata.com/service/accessibility/reduced-fare.cfm<br><br>ቨርጂኒያ ውስጥ ያሉ ተደራሽ የትራንስፖርት አማራጮችን በተመለከተ ለተጨማሪ መረጃ ይህን ይጎብኙ፡ https://www.commuterpage.com/ways-to-get-around/paratransit-transit-accessibility/ |
| | ዝቅተኛ ዋጋ ያለው የትራንዚት ክፍያ መኖሩን ለማረጋገጥ፣ ከዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን የትራንስፖርት ባለስልጣን የሜትሮ የአካል ጉዳተኝነት መታወቂያ ካርድ ይቀበሉ። ካርዱ ብቁ የሆኑ አካል ጉዳተኞች በዋሽንግተን አካባቢ አውቶብስ፣ የምድር ውስጥ ባቡርና መደበኛ ባቡር ላይ የቅናሽ ታሪፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል። | የ MetroAccess paratransit አማራጮችን ይመርምሩ። https://www.wmata.com/service/accessibility/metro-access/<br><br>ለሜትሮ የአካል ጉዳተኛ መታወቂያ ካርድ ለማግኘትና የ SmarTrip ካርዶችን ለመግዛት ማመልከቻ የሚገኝባቸውን ዝርዝሮች ለማግኘት ቅጥያውን ይመልከቱ። |

**የቤት አማራጮች**
**ግብ፡** ልጅዎ የቤተሰቡን ቤት ለመልቀቅ ትክክለኛ በሚሆንበት ጊዜ በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲኖር ማድረግ።

| **እርምጃ መቼ እንደሚወሰድ** | **ምን መደረግ አለበት** | **ማገዝ የሚችለው ማነው** |
|---|---|---|
| በልጁ የአፍላ ወጣትነት ዕድሜ ላይ | በበርካታ ስሜታዊና የፋይናንስ ጉዳዮች ምክንያት ስለ ቤት ዕቅድ ማውጣት በጣም ፈታኝ ነገር ነው። ልጅዎ ሊገመት ለሚችል የወደፊት ጊዜ አብሮዎት እንዲኖር የሚፈልጉ ቢሆንም እንኳን የዕቅድ ማውጣት ሒደቱን በጉልምስና የመጀመሪያ ወቅት ላይ ይጀምሩ። ቤትን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ቀውስ በሚፈጠርበት ሁኔታ ውስጥ ሳይሆን በጥልቀትና በስልት ታግዘው ቢወሰኑ በጣም የተሻለ ነው። | የመኖሪያ ቤት ግብዓቶችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የ The Arc of Northern Virginia መምሪያ የሆነውን "Finding a Home for Adults with Disabilities" እዚህ ይመልከቱ https://thearcofnova.org/programs/transition/finding-home-adults-disabilities/ |
| በ18 ዓመት ዕድሜ | ከአማራጮች መካከል ላቅ ያለ ደረጃ ያላቸውን ይወቁ። የመኖሪያ ቤት ዝግጅት ዓይነቶች ጎብኝተው በ YouTube ላይ በምስል የቤቶች ጉብኝትን ይመልከቱ https://www.youtube.com/user/videosatTheArcofNoVa | የ Northern Virginia የቤቶችና የድጋፍ ሰጪ አገልግሎትን ድረ ገጽ ይጎብኙ http://www.novahss.org/ |

## ቅጥያ 1፡ ትክክለኛ መረጃዎችን መያዝ

መረጃ መሰብሰብና ቁልፍ ሰነዶችን መያዝ አካል ጉዳት ያለበት ልጅዎ የሕይወት ዘመን ሙሉ የሚጋፈጡትን የጥብቅና እና የእንክብካቤ ስራዎች ለመስራት ቀላል ያደርገዋል። ለምሳሌ፣ ለ SSI ሲያመለክቱ ልጅዎን ብቁ የሚያደርገው የአካል ጉዳት እንዳለበት በተግባር ማሳየት አለብዎት። ተወካይ ተከፋይ ከሆኑ፣ ጥቅማ ጥቅሞች እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋሉ የሚያሳዩ ዓመታዊ ሪፖርቶችን ፋይል ማድረግ አለብዎት። ለዶክተሮች፣ ለፋርማሲዎች፣ ለጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ ለባንኮችና ለማሕበራዊ አገልግሎት ኤጄንሲዎች ሞግዚትነትዎን ማረጋገጥ ሊያስፈልግዎት ይችላል።

የመጀመሪያው ሒደት ለእርስዎ የሚስማማ የፋይል አያያዝ ስርዓትን መዘርጋት ነው። ከዚያም ጠቃሚ ሰነዶችን ኮፒ ወይም ስካን በማድረግ በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ አድርገው ኦሪጂናሎችን ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያስቀምጡ። **የቤተሰብ አባላትና ጠበቃዎ እነዚህ ሰነዶች ያሉበትን ቦታ ማወቃቸውን እርግጠኛ ይሁኑ።**

**የፍላጎት መግለጫ ደብዳቤ**
በልጅዎ ፋይል ውስጥ ሊኖሩ ከሚገባቸው በጣም ጠቃሚ ሰነዶች መካከል የፍላጎት መግለጫ ደብዳቤ ሲሆን በዚህም ደብዳቤ ላይ የልጅዎን ወቅታዊ ሕይወት ጠቅሰው፣ ለወደፊት ሕይወቱ ያለዎትን ዋጋ፣ ምኞትና ራዕይ ይገልጹበታል። ምንም እንኳን ሕጋዊ አስገዳጅነት ባይኖረውም፣ የፍላጎት መግለጫ ደብዳቤ ልጅዎን የመንከባከብ ተግባርን ለሚረከቡ አካላት ጠቀሜታው የጎላ ነው። በሰነዱ ውስጥ የሚካተተው መረጃ እንደየግለሰቡ የሚለያይ ቢሆንም የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል

**ለልጅዎ ቀጣይ ሕይወት ያለዎት ራዕይ፡** ለልጅዎ ሕይወት፣ የትና ከማን ጋር እንደሚኖሩና ምን ዓይነት ተግባራት ቀጣይ መደረግ እንዳለባቸው በተመለከተ ያሉዎት ግቦች።

**ልጅዎ ለወደፊት ሕይወቱ ያለው ራዕይ።** በተቻለ ጊዜ ሁሉ የልጅዎን ሃሳቦችና ምኞቶች በሰነዱ ውስጥ እንዲካተት ያድርጉ፤ ለምሳሌ ተወዳጅ ቤተሰብ በሕይወታቸው ውስጥ ጠንካራ ቦታ እንዳለው፣ የቤት እንስሳት ማሳደግ ወይም በአንድ የተወሰነ ኢንዱስትሪ ወይም የስራ ቦታ ላይ መስራት የመሳሰሉትን ማረጋገጥ።

**የግላዊ ብቃቶች መግለጫ።** የወደፊት ተንከባካቢዎች የልጅዎ ልዩ ገጽታዎች ምን እንደሆኑ ቢያውቁ ይጠቀማሉ፡ አጠቃላይ ስብዕና እና ስሜት፣ ችሎታና ጥንካሬ፣ የነጻነት ደረጃ፣ የሕክምና ወይም የባህርይ ተግዳሮቶች፣ እና የለዛ ስሜት።

**የግለሰቡን ዕለታዊ ሕይወት የሚመለከቱ ዝርዝሮች**፡ የት/ቤት ወይም የስራ መርሃ ግብሮች፤ ለምሳሌ የሳምንቱ መጨረሻ ተግባራት፣ የሃይማኖት ትምህርት ወይም አቴንዳንስን ጨምሮ፤ የመኝታ ሰዓት መደበኛ ተግባራት፤ የምግብና የልብስ ምርጫዎች እና ስሱነቶች፤ ተመራጭ አሻንጉሊቶች፣ ጨዋታዎችና የዘወትር እንቅስቃሴ፤ እና መደበኛ የቡድን ሽርሽር።

**የሕክምና ታሪክ፡** ይህ ክፍል አጠር ያለ ቢሆንም (የበሽታ ልየታ፣ ወቅታዊ ሕክምና እና የመድሃኒት አሰጣጥ ስርዓቶች) ተጨማሪ ዝርዝር መረጃዎች ከየት እንደሚገኙ መግለጽ አለበት (ከታች ይመልከቱ)።

**የኑሮ ወጪዎች።**እንደ ምግብና የቤት ኪራይ፣ የሕክምና ጉብኝቶችና መሳሪያ፣ የጤና ኢንሹራንስ፣ የመዝናኛ ተግባራት እና ሙያዎች፣ ወዘተ… የመሳሰሉ ዓመታዊ ወጪዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የወደፊት እንክብካቤ ሰጪዎች የግለሰቡን ልዩ ፍላጎቶች ትረስት እና የጥቅማ ጥቅም ገንዘብ እንዴት ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት ሃሳብ ይስጡ።

**የግንኙነት መረጃ**፡ የቤተሰብ አባላት፣ ጓደኞች፣ ዶክተሮች/ቴራፒስቶች፣ የተመረጠ ፋርማሲ፣ የት/ቤት ወይም የቀጣሪ መረጃ፣ ጠበቆች፣ ባለአደራዎችና ተጠባባቂ ሞግዚቶች፣ የኢንሹራንስ ወኪሎች፣ ባንከሮችና የፋይናንስ ዕቅድ አውጭዎች፣ ወዘተ።

የፍላጎት መግለጫ ደብዳቤ አስፈላጊነትን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ https://www.autism-society.org/living-with-autism/future-planning/letter-of-intent/

The Arc ኦንላይን የወደፊት ሁኔታ ዕቅድ ማውጫ መሳሪያ ያቀረበ ሲሆን ይህም መሳሪያ የወደፊት ዕቅድ ለማዘጋጀት፣ ለማዘመንና ለማስቀጠል የሚያስችልዎ ሆኖ አድራሻውም ቀጣዩ ነው https://futureplanning.thearc.org/landing

**ፋይል ውስጥ የሚቀመጡ ሰነዶች**
ከፍላጎት መግለጫ ደብዳቤ በተጨማሪ፣ የሚከተሉትን ሰነዶች ያዘጋጁ እና/ወይም ሰብስበው በፋይል ውስጥ ያስቀምጡ፡

**መሰረታዊ የመታወቂያ ሰነዶች፡** የልደት ምስክር ወረቀት (አብዛኛውን ጊዜ የሚፈለገው ኦሪጂናሉ ነው)፣ የማሕበራዊ ዋስትና ካርድ፣ የአሽከርካሪ ወይም የአሽከርካሪ ያለሆነ ፈቃድ፣ ፓስፖርት፣ የ Medicaid ካርድ፣ የጤና ኢንሹራንስ ካርድ።

**የባንክ መረጃ**፣ ለልጅዎ ጥቅማ ጥቅም ተብለው የተከፈቱ ማናቸውም ሒሳቦች፣ የተወካይ ተከፋይ ሒሳቦች፣ ልጅዎ እንዲጠቀም የተፈቀዱለት ማናቸውም የዴቢት ወይም ክሬዲት ካርዶች ቁጥር እና ተዛማጅ የፒን ቁጥሮችን ጨምሮ።

**ሕጋዊ ሰነዶች** ለምሳሌ ኑዛዜ፣ የልዩ ፍላጎቶች ትረስት፣ የሞግዚትነት ትእዛዝ፣ የውክልና ስልጣን ወይም የተቀባጣሪነት ሰነዶች። የተጠባባቂ ሞግዚቶችና ባለአደራዎች ስሞች እዚህ ላይ ሊቀመጥና በፍላጎት መግለጫውም ላይ ሊጠቀስ ይችላል።

**የሕክምና ታሪክ**፣ የበሽታ ልየታዎች፣ የቀድሞና የአሁን ጊዜ ሕክምናዎችና ቴራፒዎች (የአገልግሎት አቅራቢዎችን የመገኛ መረጃ፣ የሕክምና ቀናት፣ እና የታከመበት ተቋምን ጨምሮ) እና የመድሃኒት ማዘዣ መረጃዎችን ይጨምራል።

**የፋይናንስ መረጃዎች**፣ የአካል ጉዳተኛውን ሐብቶች ወይም ንብረቶች የሚመለከቱ ማናቸውም ማስረጃዎች፣ የግብር ተመላሾች፣ የክፍያ ሰነዶች ወይም ሌላ የገቢ ማስረጃ፣ እና ለሕክምና አገልግሎቶች እና መሳሪያዎች የተከፈሉ ክፍያዎችን ጨምሮ።

## ቅጥያ 2፡ የጤና ኢንሹራንስን ማረጋገጥ

በቂ የሆነ የጤና ኢንሹራንስ መኖሩ የልጅዎን የፋይናንስና አካላዊ ጤንነት ለማስጠበቅ ወሳኝ ጉዳይ ነው። የዕድሜ ልክ አካል ጉዳት ያለባቸው ጎልማሳ ልጆች በወላጆቻቸው የጤና ኢንራንስ ውስጥ ላልተወሰነ ጊዜ ሊቆዩ ይችላሉ (ጉዳት አልባ ልጆች ግን ከ26 ዓመታቸው በኋላ ሽፋን አይኖራቸውም)። አሁን ከሚወስዷቸው እርምጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡

- ለአካል ጉዳተኛ ልጅዎ ለተጨማሪ የዋስትና ገቢ ክፍያዎች ማመልከት። ልጅዎ ለዚህ ፕሮግራም ብቁ ከሆነ፣ የ Medicaid ሽፋን ማግኘቱ በጣም ቀላል ይሆናል።
- እርስዎ ስራ ካቆሙ በኋላ ልጅዎ የሚኖረውን የጤና ኢንሹራንስ አማራጮችና ወጪ መፈተሽ።

### የግል አሰሪዎች የጤና ዕቅዶች

የ2010 Affordable Care Act የጤና እንክብካቤ ሽፋንን ለቤተሰቦችና ግለሰቦች ያሰፋ ሲሆን ለአካል ጉዳተኞችም ወሳኝ የሆኑ ጥበቃዎችን ይሰጣል።

የዕድሜ ልክ አካል ጉዳት ያለባቸው ጥገኞች ከ26 ዓመታቸው በኋላም አሰሪዎ ስፖንሰር ባደረገው ፖሊሲ ውስጥ መቆየት ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ስራ ተኮርና አዳዲስ የተናጠል ዕቅዶች ዕድሜው ከ19 ዓመት በታች የሆነውን ማንኛውም ልጅ አካል ጉዳትን ጨምሮ ከዚህ በፊት በነበረው ሁኔታ ምክንያት ሽፋን መከልከል ወይም ማግለል አይፈቀድላቸውም። እነዚሁ ዕቅዶች አካል ጉዳትን ጨምሮ ከዚህ በፊት በነበረው ሁኔታ ምክንያት ማንኛውንም ሰው ከሽፋን ማስወጣት ወይም ከፍ ያለ አረቦን እንዲከፍል ማድረግም አይችሉም።

### Medicaid

Medicaid አነስተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች፣ ለአረጋውያንና ለአካል ጉዳተኞች የቀረበ የፌዴራል የጤና ኢንሹራንስ ፕሮግራም ነው። Medicaid ለማግኘት አንደኛው መንገድ ለተጨማሪ ዋስትና ገቢ (SSI) ብቁ መሆን ነው። የ SSI መስፈርቶችን ካሟሉ፣ የ Medicaid መስፈርቶችንም ያሟላሉ።

የግል ጤና ኢንሹራንስ ቢኖርዎትም የ Medicaid ወይም FAMIS Plus (Plan First ሳይጨምር) ሽፋን ሊኖርዎት ይችላል። *ሌላ ኢንሹራንስ ካለዎት፣ የሕክምና አገልግሎት ወጪዎችን በቅድሚያ የሚከፍለው ሌላኛውን የኢንሹራንስ ዕቅድ ነው።* ሌላ የጤና ኢንሹራንስ ቢኖርዎትም ለአገልግሎት አቅራቢዎች በ Medicaid ተመዝጋቢነትዎ የሚከፍሉት የ Medicaid የጋራ ክፍያ መጠን አይቀየርም።

### የጤና ኢንሹራንስ አረቦን የክፍያ ፕሮግራም

ልጅዎ Medicaid ካለው፣ የጤና ኢንሹራንስ አረቦን ክፍያ (HIPP) የጤና ኢንሹራንስ አረቦንዎን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከፍሉ ሊያግዝዎት ይችላል።
የጤና ኢንሹራንስ ዕቅድዎ በ Medicaid የማይሸፈኑ አገልግሎቶችን ሊሸፍን ይችላል። HIPP ወጪውን ሊሸፍኑ የማይችሉት የጤና ኢንሹራንስ እንዲኖርዎ ያስችልዎታል። HIPP በጤና ኢንሹራንስ ዕቅድዎ ውስጥ የተሸፈኑ አገልግሎቶችን የሚገመግም ሲሆን ለ Medicaid ብቁ የሆነ የቤተሰብዎን አባል አማካይ የ Medicaid ወጪ ከእርስዎ የጤና ኢንሹራንስ አረቦን ጋር ያነጻጽራል።

በቀጣዩ የ DMAS ድረ ገጽ ላይ መረጃ ማግኘት ይቻላል፡ [http://www.dmas.virginia.gov/files/links/966/AmIEligible.pdf](http://www.dmas.virginia.gov/files/links/966/AmIEligible.pdf) ወይም ለ HIPP ፕሮግራም በስልክ ቁጥር 800-432-5924 ይደውሉ [https://www.coverva.org/hipp/](https://www.coverva.org/hipp/)

### የመረጃ ግብዓቶች

በ Affordable Care Act ምክንያት በግል የጤና እንክብካቤ ላይ ስለተደረጉ ለውጦች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይመልከቱ [www.healthcare.gov](http://www.healthcare.gov)።
የ Medicare እና የግል ኢንሹራንስ ጉዳዮችን ለመረዳት እገዛ ካስፈለገዎ፣ የቨርጂኒያ ኢንሹራንስ ማማከርና ድጋፍ ሰጪ ፕሮግራምን በስልክ ቁጥር 703-324-5851 ያነጋግሩ።

## ቅጥያ 3፡ ለጥቅማ ጥቅሞች ማመልከት፡ የማሕበራዊ ዋስትና የአካል ጉዳተኝነት ፕሮግራሞች

ልጅዎ ዕድሜው 18 ዓመት እንደሞላ የማሕበራዊ ዋስትና ጥቅማ ጥቅሞችን የማመልከቻ ሒደት መጀመር ይችላሉ። የመጀመሪያው ሒደት ለማንኛውም የጥቅማ ጥቅም ፕሮግራም *ብቁነትን ይወስኑ*፤ የማሕበራዊ ዋስትና አስተዳደር (SSA) የትኛው ፕሮግራም አግባብነት እንዳለው ይወስናል። ስለ SSI/SSDI የተዘጋጁ የቪድዮና የኢንተርኔት ውይይቶችን ለማየት The Arc of Northern Virginia የ YouTube ቻናልን (Videos at The Arc of NoVA) ይመልከቱ https://www.youtube.com/user/VideosatTheArcofNoVA

### SSI ከ SSDI ጋር ሲነጻጸር

ለተጨማሪ የዋስትና ገቢ (SSI) እና ለማሕበራዊ ዋስትና የአካል ጉዳተኝነት ገቢ (SSDI)፣ *አንድ ሰው በSSA ለአካል ጉዳተኝነት የተሰጠውን ፍቺ ማሟላት አለበት*። አካል ጉዳት ማለት በማንኛውም የጤና (አካላዊ እና/ወይም አእምሯዊ ወይም ዓይነ ስውርነት) ውስንነት ምክንያት ከፍተኛ ገቢ በሚያስገኝ ተግባር (SGA) ውስጥ ለመሳተፍ አለመቻል ማለት ነው። አካል ጉዳትዎ ከ12 ወራት ለማያንስ ጊዜ የቆዬ ወይም በተከታታይ እንደሚቆይ የሚጠበቅ ወይም ሞትን የሚያስከትል ሊሆን ይገባል። ለ 2019፣ የ SGA የደመወዝ ገደብ ያልተጣራ ገቢ/በወር $1,220 ነው።

**SSI**፡ SSI ውስን ገቢ ላላቸውና ዕድሜያቸው 65 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ወይም ለዓይነ ስውራን ወይም ለአካል ጉዳተኞች የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ የሚሰጥ ፕሮግራም ነው። ጎልማሳ የ SSI ተጠቃሚዎች የተገደበ ገቢና ሐብት ሊኖራቸው ይገባል ($2,000 የሚያወጣ ሐብት)፤ በጎልማሶች ማመልከቻ ውስጥ የወላጆች ገቢ ታሳቢ አይደረግም። ምንም ዓይነት የስራ ታሪክ ሊኖርዎት አይገባም። ወርሐዊ የጥቅማ ጥቅም ክፍያዎች የሚወሰኑት ከአሁኑ የጥቅማ ጥቅም ተመን (በ2019 በወር $771) ላይ ማንኛውንም "የሚቆጠር ገቢ" በመቀነስ ነው። ለ SSI ብቁ ከሆኑ፣ ለ Medicaid እንደዚሁ ብቁ ይሆናሉ።

**SSDI**፡ SSI በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ፕሮግራም ሲሆን፣ SSDI ደግሞ የኢንሹራን ፕሮግራም ሲሆን ቀደም ሲል ለሰርዓቱ በተከፈሉ ክፍያዎች ላይ ተመስርቶ ጥቅማ ጥቅሞች የሚከፈሉበት ነው። በሌላ አነጋገር፣ የ SSDI ተጠቃሚዎች ወደ FICA መዋጮ ለማድረግ በሚያስችል መጠን ለበቂ ጊዜ ስራ የሰሩ (ወይም ወላጆቻቸው ወይም የትዳር ጓደኞቻቸው ለበቂ ጊዜ መስራት ይኖርባቸዋል) መሆን አለባቸው። ወርሐዊ የጥቅማ ጥቅም ክፍያዎች የተመሰረቱት በማሕበራዊ ዋስትና የተሸፈኑ የሰራተኛው የዕድሜ ልክ አማካይ ገቢዎች ላይ ነው።

### ለጥቅማ ጥቅሞች ማመልከት

የማመልከቻ ሒደቶች የሚከተሉት ናቸው፡

**በአካል ጉዳተኝነት ሪፖርት ይጀምሩ**። ወደ ቀጣዩ ድረ ገጽ ገብተው http://www.socialsecurity.gov/pgm/ssi.htm የጎልማሶች አካል ጉዳት ሪፖርት የሚለውን ይጫኑ። (ወደ 1-800-772-1213 መደወል ወይም ወደ ማሕበራዊ ዋስትና የመስክ ጽ/ቤት መሄድ ይችላሉ።) በአካባቢው ጽ/ቤት ከሚኖርዎት ቀጠሮ በፊት የቻሉትን ያህል መረጃ እዚህ ላይ ያስገቡ። ማመልከቻው ልጅዎን ያከሙትን ዶክተሮችና ቴራፒስቶች ስም፣ አድራሻ እና የስልክ ቁጥርና በሆስፒታል ተኝቶ መታከምን የሚመለከት መረጃን ይጠይቃል። ለምሳሌ በቴራፒስቶች ወይም ት/ቤቶች የተከናወኑ የበሽታ ልየታ ወይም ምዘና የመሳሰሉ ይበልጥ ገላጭ የሆኑ የሕክምና መረጃዎች በመረጃ መለዋወጫ ቃለ መጠይቆች ወቅት መቅረብ ይችላሉ (ኮፒ ያድርጉ!)።

ማመልከቻውን በአካባቢው የ SSA ቢሮ በሚኖርዎት ቀጠሮ ወቅት መሙላትም ይችላሉ፤ ይህን ለማድረግ ግን ሁሉንም የሕክምና ማስረጃዎችዎን መውሰድና ከቃለ መጠይቅ አድራጊው ጋር በዛ ያለ ጊዜ ማጥፋትን ይጠይቃል።
ወደ ኮምፒዩተር መድረስ የማይችሉ ከሆነ፣ ወደ 800 ደውለው ማመልከቻ እንዲላክልዎት መጠየቅ ይችላሉ።

*የጥቅማ ጥቅሞችን ማመልከቻ ኦንላይን መሙላት አይችሉም፤ ወደ ማሕበራዊ ዋስትና ደውለው ቀጠሮ ማስያዝ አለብዎት።*

***ወደ ማሕበራዊ ዋስትና ይደውሉ***። ቀጠሮ ለማስያዝ ከሰኞ እስከ አርብ በስልክ ቁጥር **1-800-772-1213** (TTY **1-800-325-0778**) ይደውሉ ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የማሕበራዊ ዋስትና ቢሮ ያነጋግሩ። ወደ አካባቢ ቢሮ ከመደወል ይልቅ ወደ 800 መደወል የተሻለ ነው፤ ምክንያቱም የመስክ ጽ/ቤቶች የሰራተኛ እጥረት ያለባቸው በመሆኑና የወረፋ መጠበቂያ ጊዜያትም በጣም ረዥም ሊሆኑ ይችላሉ። አውቶማቲክ የመልስ ሰጪ ሰራተኛ የሚቀበልዎ ሲሆን ሰራተኛውም የደወሉበትን ምክንያት እንዲገልጹ ይገፋፋዎታል፤ እርስዎም "ለ SSI አመልክት" ይበሉ።

አውቶማቲክ መልስ ሰጪው የልጅዎን የማሕበራዊ ዋስትና ቁጥር እንዲናገሩ ወይም እንዲያስገቡ ይጠይቅዎታል። ከዚያም ጥሪዎ ወደ ተወካይ ይመራል። በስልክ ቃለ መጠይቁ ወቅት፣ ተወካዩ መረጃዎችን ወስዶ ወደ ኮምፒዩተር የሚያስገባ ሲሆን ኮምፒዩተሩም የማመልከቻውን ቀን ያረጋግጣል።

- የወረቀት ሰነዶች ይላኩለዎታል። ሰነዱን ሞልተው በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተመላሽ ያድርጉ።
- በስልክ ቃለ መጠይቁ ወቅት የሚመነጨው ሰነድም ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ እንዲፈረም ይላክልዎታል።
- ማንኛውንም ሰነድ ለኤጀንሲው መልሰው ከመላክዎ በፊት ኮፒ ማዘጋጀትዎን እርግጠኛ ይሁኑ።

***የማጣሪያ ቃለ መጠይቅ ያዘጋጁ።*** ቀደም ሲል በተደረገ የስልክ ቃለ መጠይቅ ወቅት፣ ተወካዩ ማጣሪያ የሚያዘጋጅ ሲሆን ይህም በአካባቢዎ የማሕበራዊ ዋስትና ጽ/ቤት የማመልከቻውን ሒደት ያስቀጥላል። ከ Northern Virginia አካባቢ ውጭ ከሆኑ፣ http://www.ssa.gov/locator በመጎብኘት የአካባቢዎን ጽ/ቤት ያግኙ።

**Alexandria Office**
PLAZA 500, Suite 190
6295 Edsall Road
Alexandria, VA 22312, 1-800-772-1213

**Fairfax Local Office**
11212 Waples Mill Rd
Fairfax, VA 22030-7401, 1-800-772-1213

***ወደ ማጣሪያ ቃለ መጠይቁ ይሂዱ።*** *የልጅዎን ዕድሜ፣ ዜግነት፣ አካል ጉዳት እና የሐብት/ንብረት አለመኖርን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማናቸውንም መረጃዎች በሙሉ ይዘው ይምጡ፡*

- ኦሪጂናል የልደተ ምስክር ወረቀት (ወይም ሌላ የዕድሜና የዜግነት ማረጋገጫ) እና የማሕበራዊ ዋስትና ካርድ
- አድራሻዎትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሰነድ
- የልዩ ፍላጎቶች ትረስት፣ የሞግዚትነት ወይም የተቆጣጣሪነት ትእዛዝ
- ግለሰባዊ የትምህርት ዕቅድ (IEP)
- ልጅዎ ገቢ ካለው፣ የገቢ ሰነዶች
- በልጅዎ ባለቤትነት ስር የሚገኙ ማናቸውም ሐብቶች፣ ለምሳሌ የቁጠባ ሒሳብ፣ ኢንቨስትመንት፣ የመኪና ባለመብትነት ወይም የሕይወት ኢንሹራንስን የሚመለከት መረጃ። *የSSI ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት የእነዚህ አጠቃላይ ዋጋ ከ $2,000 መብለጥ የለበትም*(በልዩ ፍላጎቶች ትረስት ወይም በ ABLE ሒሳብ ውስጥ ካልተቀመጠ በስተቀር)። የገቢ ገደብ ላላቸው ፕሮግራሞች ልጁ 18 ዓመት እስከሚሞላው ድረስ SSA የወላጆችን ገቢና ሐብት ከግምት ውስጥ እንደሚያስገባ ያስተውሉ፤ **ከ 18 ዓመት በላይ የሆናቸው ግለሰቦች ራሳቸውን የቻሉ ቤተሰቦች ተደርገው ይቆጠራሉ።**
- *ማመልከቻውን ኦንላይን ካልሞሉ፣ አስፈላጊ የሕክምና ማስረጃዎችና የመገኛ መረጃዎችን ወደ ማጣሪያው ቀጠሮ ይዘው ይምጡ።*
- የቼክ ደብተር ወይም የባንክ ሒሳብ ቁጥርን የሚያሳዩ ሌሎች ሰነዶች ጥቅማ ጥቅሞች በቀጥታ ወደ ተወካዩ ሒሳብ ገቢ እንዲደረግ ያስችለዋል።
- በወላጅና በልጅ መካከል የተፈረመ የኪራይ ስምምነት (ሙሉ ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት)። በዚህ ክፍል ውስጥ "ቤት እና የ SSI ጥቅማ ጥቅሞች" የሚለውን ይመልከቱ።

**ብቁነት እስከሚወሰን ድረስ ይጠብቁ።** *ኤጀንሲው የአካል ጉዳተኝነት ሪፖርት ቅጽዎን እና የሕክምና ታሪክዎን ወደ* Disability Determination Service (DDS፣ *የአካል ጉዳተኝነት መወሰን አገልግሎት) ይልከዋል።* DDS *የስራ ታሪክ፣ አካል ጉዳቱ የጀመረበትን ጊዜ እና ሕክምና መቼ እንደተሰጠ የመሳሰሉ ተጨማሪ መረጃዎችን ሊጠይቅ ወይም ላይጠይቅ ይችላል።* DDS *በ* SSA *ስም የሕክምና ወይም የስነ-ልቡና ምርመራ እንዲደረግ ሊጠይቅ ይችላል (በ* SSA *የተመረጠ ሐኪም ለሚያደርግው ምርመራ ወጪውን የሚሸፍነው* SSA *ነው)።*

*ለጥቅማ ጥቅም ብቁ መሆንን በተመለከተ በግምት በ* 60 *ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል። ጥያቄዎ ውድቅ ከተደረገ በ* 60 *ቀናት ውስጥ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ።*

*በስራ ላይ ያሉ ወይም ለመስራት የሚፈልጉ ሰዎችን በተመለከተ ማሕበራዊ ዋስትና እንዴት እንደሚያስተናግድ ለመረዳት ከ* Marilyn Morrison at Community Work Incentives Coordinator, 571-339-1305 [mmorrison@vaaccses.org](mailto:mmorrison@vaaccses.org) *ጋር ይነጋገሩ*

**የተወካይ ተከፋይ ሒሳብ ይክፈቱ።** ልጅዎ አንዴ ጥቅማ ጥቅም ከተቀበለ፣ የተወካይ ተከፋይ ሒሳብ መክፈት አለብዎት፤
ለሒሳቡ ትክክለኛውን ርዕስ መስጠትዎን እርግጠኛ ይሁኑ (SSA የቃላት አጠቃቀምን ሃሳብ ይሰጣል)።
*ጥቅማ ጥቅሞች ወዲያውኑ ተቀማጭ መደረጋቸው አስፈላጊ ነው።*

---

**ተወካይ ተከፋይ**

*ተወካይ ተከፋይ ማለት ገንዘቡን ለማስተዳደር ድጋፍ ለሚያስፈልገው ሰው የማሕበራዊ ዋስትና እና/ወይም የ* SSI *እንዲቀበል በ* SSA *የተሾመ ሰው ነው። ተወካይ ተከፋዩ የፋይናንስ መረጃዎችን ማስተናገድ ምቾት የሚሰጠውና የአካል ጉዳተኛ ተጠቃሚውን ጥቅሞች ለማስጠበቅ እምነት የሚጣልበት መሆን አለበት።*

*ተከፋዩ የወጪ መዛግብትን መያዝ ያለበት ሲሆን ሁሉም የ* SSI *ገንዘቦች ለምን ዓላማ እንደወጡ በየዓመቱ ማስረዳት መቻል አለበት።* SSA *"የተወካይ ተከፋይ ሪፖርት" በየዓመቱ ይልካል፤ ሪፖርቱን በፍጥነት ሞልተው መልሰው ይላኩት ወይም ሪፖርቱን ኦንላይን ማቅረብ ይችላሉ።*

*ተወካይ ተከፋይ ሆነው ለመሰየም ከፈለጉ በአካባቢዎ የሚገኘውን የ* SSA *ቢሮ ያነጋግሩ (ከላይ ይመልከቱ)። ከዚያም ማመልከቻ፣ ቅጽ* SSA-11 *እና ማንነትዎን የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ማቅረብ አለበዎት።* SSA *የተከፋይ ማመልከቻውን በፊት ለፊት ቃለ መጠይቅ እንዲሞሉ ይጠይቅዎታል።*

*የውክልና ስልጣን ማግኘት፣ ሕጋዊ ተወካይ መሆን ወይም ከተጠቃሚው ጋር የጣምራ የባንክ ሒሳብ መክፈት የተጠቃሚው የማሕበራዊ ዋስትና እና/ወይም የ* SSI *ክፍያዎችን ለመደራደርና ለማስተዳደር ሕጋዊ ስልጣን እንደማይሰጥዎት ያስተውሉ። ይህን ይመልከቱ*
[www.socialsecurity.gov/payee](http://www.socialsecurity.gov/payee)

---

## የቤትና የ SSI ጥቅማ ጥቅሞች

**SSI እንደ ቤት ኪራይ፣ ምግብና የአገልግሎት ክፍያ የመሳሰሉ የኑሮ ወጪዎችን ለመሸፈን የታሰበ ነው።** ለምሳሌ፣ ጎልማሳ ልጅዎ በቤተሰቡ ቤት ውስጥ የሚኖር ከሆነ **የቤት ኪራይ እንዲያስከፍሉት** ይመከራል። ***የሚጠየቀው የቤት ኪራይ አሁን ከሚያገኘው የፌዴራል ጥቅማ ጥቅም መጠን ቢያንስ 30% መሆን አለበት*** (ለ 2019 በወር $771)፤ ይህም ከፍተኛውን የ SSI ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ያስችላል።
በአካባቢዎ የሚገኙ የኪራይ ቤቶችን በማወዳደር ይህንኑ በኪራይ ስምምነት ውስጥ እንዲያካትቱ ይመከራል። የ SSI ጥቅማ ጥቅሞች በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ ሊቀንሱ እንደሚችሉ ይወቁ፡

*ባጠቃላይ፣ ከ* SSI *ጥቅማ ጥቅምዎ ውስጥ አንድ ሶስተኛ አካባቢ የሚሆነው ለቤት ነክ ወጪዎች (ለኪራይ ወይም ሞርጌጅ፣ ለአገልግሎት ክፍያ፣ ለንብረት ኢንሹራንስ/ለተከራይ ኢንሹራንስ፣ ወዘተ) እንደሚወጣና ቀሪው ሁለት ሶስተኛ ደግሞ እንደ ምግብና ልብስ ላሉ ሌሎች ወጪዎች እንደሚወጣ ታሳቢ ይደረጋል። በ* Northern Virginia *ውስጥ ያለውን የኑሮ ውድነት ታሳቢ ስናደርግ፣ ከ* SSI *ጥቅማ ጥቅምዎ ውስጥ ከአንድ ሶስተኛ በላይ የሚሆነው የቤት ወጪዎችን ለመሸፈን እንደሚውል ይታሰባል። ናሙና የሚሆን የኪራይ ስምምነት ከሪሶርስ ላይበረሪያችን ማግኘት ይቻላል*
[https://thearcofnova.org/programs-services/library/](https://thearcofnova.org/programs-services/library/)

ከልዩ ፍለጎቶች ትረስት የተገኘ ገንዘብ በሞርጌጅ ቤት ለመግዛት ከዋለና **ወርሐዊ የሞርጌጅ ክፍያዎች የሚከፈሉት በትረስቱ ከሆነ**፣ የተጠቃሚው የ SSI ክፍያዎች በየወሩ በአንድ ሶስተኛ ይቀንሳሉ (ከቤቱ ጋር የተያያዘ የ SSI ድርሻ)። ትረስት ካለዎት፣ የኪራይ ወይም የሞርጌጅ ገንዘብዎን ወደ ABLE ሒሳብ ማስተላለፍና ከ ABLE ሒሳበ ወጪ አድረገው ኪራይ መክፈል የሚችሉ ሲሆን የ SSI መጠንም አይቀንስም። የ ABLE ሒሳቦችን አጠቃቀም በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የትረስት ድረ ገጻችንን www.thearcofnovatrust.org፣ የ ABLE National Resource Center ድረ ገጽና www.ablenrc.org የ Virginia ABLE ፕሮግራምን ደረ ገጽ https://www.able-now.com/ ይጎብኙ።

ቤቱ የተገዛው በእጅ በእጅ ወይም በሞርጌጅ ቢሆንም፣ እንደ ታክስ፣ ማሞቂያ፣ ኤሌክትሪሲቲ፣ ውሃ፣ ፍሳሽ ማስወገጃና የደረቅ ቆሻሻ መሰብሰቢያ የመሳሰሉ **የቤተሰብ ወጪዎች በትረስቱ የሚከፈሉ ከሆነ** የ SSI ክፍያዎች ከአንድ ሶስተኛ ትንሽ ከፍ ባለ መጠን ይቀንሳሉ።

እነዚህን ይመልከቱ፡
https://secure.ssa.gov/poms.nsf/lnx/0500835300 እና
https://secure.ssa.gov/poms.nsf/lnx/0500835901

**ገቢን ሪፖርት ማድረግ**

የ SSI ተጠቃሚዎች ማናቸውም ገቢያቸውን ለማሕበራዊ ዋስትና ሪፖርት ***ማድረግ አለባቸው።*** በዚህም ውስጥ የሚካተቱት ከስራ የሚገኝ ገቢ፣ የአንድ ጊዜ ክፍያ፣ የልጅ ተቆራጭ፣ የትረስት ክፍያዎች፣ ወዘተ.. ናቸው። SSI በፍላጎት ላይ ተመስርቶ ከወር እስከ ወር የሚሰጥ ጥቅማ ጥቅም ነው። ለ SSA ሪፖርት በማድረግ ሒደት የሚፈጠር ማንኛውም መዘግየት ጥቅማ ጥቅሞች በእላፊ መጠን እንዲከፈሉ ያደርጋል። ለማሕበራዊ ዋስትና የላኩትን ሰነድ መዝግበው ይያዙ። የተረጋገጠ መልእክት ይጠቀሙ ወይም መረጃውን በፋክስ ከላኩት፣ የፋክስ ማረጋገጫ ገጽን ያስቀምጡ።

የማሕበራዊ ዋስትና አካል ጉዳት ፕሮግራሞች ተጠቃሚዎች ሪፖርት የሚያደርጉባቸውን ሁኔታዎች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ሪሶርስ ላይብረሪያችንን ይጎብኙ፡
https://thearcofnova.org/programs-services/library/

## ቅጥያ 4፡ ለጥቅማ ጥቅሞች ማመልከቻ ማስገባት፡ የ Medicaid Waiver ፕሮግራሞች

ይህ መረጃ ከ The Arc of Northern Virginia ድረ ገጽ የተወሰደ ነው። ለተጨማሪ መረጃ፣ www.thearcofnova.org/programs/waivers

የቤተሰብ ገቢና የቤተሰብ ሐብቶች በ Medicaid Waiver ፕሮግራም ውስጥ ታሳቢ አይደረጉም። የልጅዎ የግል ገቢና ሐብቶች ብቁ የሚያደርጉት ከሆነ፣ አካል ጉዳት እንዳለበት በምርመራ ከተረጋገጠ እና የተግባራዊ ብቁነት መስፈርትን የሚያሟላ ከሆነ። የ Waiver ሒደቶችን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የሚየስረዱ የተቀረጸውን የኢንተርኔት ገለጻችንን ለማየት ይህን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡ https://www.youtube.com/watch?v=3sG85EQjuKE

ስለ አዳዲስ መሻርያዎች (Waivers) ተጨማሪ መረጃ ከዚህ ማግኘት ይችላሉ፡ http://mylifemycommunityvirginia.org/ or call their hotline at 1-844-603-9248።

## በ Waivers የሚሸፈኑ አገልግሎቶች

**የዕድገት አካል ጉዳተኝነት መሻርያዎች (The Developmental Disability (DD) Waivers):** 3 ዓይነት የ DD Waivers አሉ፤ እነርሱም (1) የማህበረሰብ ኑሮ፣ (2) የቤተሰብና የግለሰባዊ ድጋፎች፣ እና (3) ራስን የመቻል Waivers ማዳበር ናቸው። እነዚህ waivers በተለያዩ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚሰጡ ድጋፎችን ይሸፍናሉ፤ በእነዚህም ውስጥ በልጁ ቤተሰብ ቤት ውስጥ በሰዓት የሚከፈለው ሰራተኛ እና 24 ሰዓት ሰራተኛ ያለው የቡድን ቤት ማዕቀፎች ይገኙበታል። እነዚህ ሶስት waivers በትምህርት ገበታ ላይ ለማይገኙ ሰዎች የሚሰጡ የተለያዩ የስራ ቅጥርና ትርጉም ያለው የእንክብካቤ ድጋፎችንም ይሸፍናሉ። አንዳንድ ተጨማሪ አገልግሎቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡ ፋታ መስጫ እንክብካቤ፣ የቤት ውስጥ ድጋፍ፣ የአብሮ ነዋሪ እንክብካቤ፣ አጋዥ ቴክኖሎጂ፣ የአካባቢ ማሻሻያዎች፣ የቴራፒ ነክ ምክክር፣ አጣዳፊ ያልሆነ የሕክምና ትራንስፖርት፣ የግል ነርሲንግ አገልግሎት፣ የሰለጠነ ነርሲንግ፣ እና ግላዊ የድንገተኛ ምላሽ ስርዓት (PERS) ናቸው።

**<u>የማህበረሰብ ኑሮ Waiver</u>** 24/7 የመኖሪያ ቤት ውስጥ አገልግሎትን በዚህ ደረጃ ድጋፍ ለሚፈለጉ ሰዎች የሚሸፍን ሁሉን አቀፍ waiver ነው። ለጎልማሶችና ለልጆች የሚሰጡ አገልግሎቶችና ድጋፎችንም የሚጨምር ሲሆን ከፍተኛ የሕክምና እና/ወይም የባህርይ ፍላጎት ያላቸው በዚህ ውስጥ ይካተታሉ።

**<u>የቤተሰብና የግለሰቦች ድጋፍ መስጫ Waiver</u>** የተቀረጸበት ዓላማ ከቤተሰቦቻቸው፣ ጓደኞቻቸው ጋር ወይም በራሳቸው ቤት ውስጥ የሚኖሩ ግለሰቦችን ለመደገፍ ነው። የተወሰነ የሕክምና ወይም የባሕርይ ፍላጎት ያለባቸውን ግለሰቦች የሚደግፍ ሲሆን ለጎልማሶችና ለልጆች የሚቀርብ ነው።

**<u>ነጻነትን የማዳበር Waiver</u>** 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸውና በአነስተኛ ድጋፍ ማህበረሰቡ ውስጥ ለመኖር የሚችሉ ጎልማሶችን ይደግፋል። ይህ waiver 24/7 የቤት ውስጥ አገልግሎቶችን አይጨምርም። ግለሰቦች የራሳቸውን የኑሮ ሁኔታ በባለቤትነት መያዝ፣ መከራየት ወይም መቆጣጠር የሚችሉ ሲሆን ድጋፎችም በ waiver ወጪው በማይሸፈን የኪራይ ድጎማ ሊታገዝ ይችላል።

የ waiver አገልግሎቶችን የሚያገኙ ግለሰቦች በየሁለት ዓመቱ (በልጅነት) እና በየሶስት ዓመቱ (በጉልምስና) የድጋፎች ጥልቀት ሚዛን [Supports Intensity Scale (SIS)] የተባለ ምዘና የሚደረግላቸው ሲሆን ይህም የድጋፍ ፍላጎታቸውን ጥልቀት ለመለካት የሚደረግ ነው። ሰዎች በጊዜ ሂደት ፍላጎቶቻቸው ከተቀየሩ በእነዚህ ሶስት የ DD Waivers መካከል ማቀያየር ይችላሉ። የበለጠ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ወደሚያገለግል waiver ለመዛወር አንዳንዴ ወረፋ መጠበቅን ሊያስከትል ይችላል፤ ምክንያቱም "በቅድሚያ የመጣ በቅድሚያ ይስተናገድ" የሚል ስርዓት በመሆኑ ነው።

**የብቁነት መስፈርት**

ማንኛውም ሰው ለ Medicaid DD Waiver ብቁ ለመሆን ሊያሟላቸው የሚገቡ መስፈርቶች አሉ፡

(1) <u>የመስራት ችሎታ</u>፡ ይህ የሚወሰነው በ VIDES የዳሰሳ ጥናት ነው። VIDES ዕድሜያቸው ከ0-3 ዓመት ለሆናቸው ልጆች አንድ ፈተና፣ ዕድሜያቸው ከ3-18 ዓመት ለሆናቸው ልጆች አንድ ፈተና እና ለጎልማሶች ደግሞ አንድ ፈተና አለው። የዳሰሳ ጥናቶቹ ግለሰቡ በተለያዩ የዕለታዊ ኑሮና ራስን የመቻል ክህሎት ተግባራት ያለውን ፍላጎት ይመዝናሉ። የ VIDES የዳሰሳ ጥናቶች ሪሶርስ ላይብረሪያችን ውስጥ ይገኛሉ https://thearcofnova.org/programs-services/library/

(2) <u>የበሽታ ልዬታ</u>፡ ለ Waiver የሚያመለክቱ ሰዎች ለ DD Waivers የተቀመጡትን ችግር ለይ የብቁነት መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። ይህ ማለት አንድ ሰው በቨርጂኒያ ሕግ አንቀጽ 37.2-100 በተገለጸው መሰረት የዕድገት አካል ጉዳት ሊኖርበት ይገባል።

a. "የዕድገት አካል ጉዳት" ማለት በአንድ ግለብ ላይ የደረሰ ከባድና ስር ሰደድ የአካል ጉዳት ሆኖ (i) ከአእምሮ ወይም አካላዊ ውስንነት ወይም ከአእምሮና አካላዊ ውስንነቶች ከሀሉቱም ጋር የተያያዘና ከአእምሮ ሕመም ብቻ ጋር ያልተያያዘ ሲሆን፤ (ii) ግለሰቡ ዕድሜው 22 ዓመት ከመሙላቱ በፊት ከታዬ፤ (iii) ላልተወሰነ ጊዜ የሚቀጥል ከሆነ፤ (iv) ከሚከተሉት ዋና ዋና የሕይወት ተግባራት መካከል ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑት ላይ ከፍተኛ የሆነ ውስንነትን ካስከተለ፡ ግለ እንክብካቤ፣ ተቀባይና ገላጭ ቋንቋ፣ መማር፣ እንቅስቃሴ፣ ራስን መምራት፣ ራስን ችሎ የመኖር ችሎታ፣ በኢኮኖሚ ራስን መቻል፤ እና (v) ግለሰቡ ልዩና ዘርፈ ብዙ ወይም አጠቃላይ አገልግሎቶች፣ ግላዊ ድጋፍ ወይም የዕድሜ ልክ ወይም ረዥም ቆይታ ያላቸውና በግልሰብ ደረጃ ታቅደው ሊተገበሩ

የሚችሉ ድጋፎች ያለውን ፍላጎት የሚያንጸባርቅ ሲሆን ነው። አንድ ግለሰብ ተወልዶ ዘጠኝ ዓመት እስከሚሞላው ድረስ ከፍተኛ የሆነ የዕድገት መዘግየት ወይም የተወሰነ አብሮ የሚወለድ ወይም ከወላጅ የተወረሰ የጤና ችግር ያለበት ማንኛውም ሰው በአንቀጽ (i) እስከ (v) ውስጥ የተዘረዘሩትን ሶስት ወይም ከዚያ በላይ መስፈርቶች ባያሟላም እንኳን እንደ አካል ጉዳተኛ የሚቆጠር ሲሆን ለዚህም ግን ግለሰቡ አገልግሎትና ድጋፍ ሳያገኝ እነዚህን መስፈርቶቸ በሕይወቱ ቀጣይ ክፍል ውስጥ ሊያሟላቸው እንደሚችል ከፍተኛ ዕድል ሲኖር ነው።

(3) <u>ፋይናንስ ነክ:</u> የተግባርና ችግር መለያ መስፈርቶች ከተሟሉ፣ የልጁ ገቢና ሐብቶች ከግምት ውስጥ ይገባሉ። የልዩ ፍላጎቶች ትረስት እና የ ABLE ሒሳቦች የፋይናንስ ብቁነት በሚፈተሸበት ጊዜ ከግምት ውስጥ አይገቡም። ከ 18 ዓመት በላይ የሆናቸው ሰዎች የሐብት ገደባቸው $2,000 ነው። Waiver የሚያገኝ ማንኛውም ሰው ወርሐዊ የገቢ ገደቡ አሁን ካለው የማሕበራዊ ዋስትና ገቢ መጠን 300% ነው (በ 2019 የ SSI መጠን $771 ስለሆነ ከፍተኛው ወርሐዊ ገቢ ከ $2,313 መብለጥ የለበትም)።

**<u>የ Commonwealth Coordinated Care (CCC) Plus Waiver</u>** የግል እንክብካቤ፣ ፋታ መውሰጃ እንክብካቤ፣ የመድሃኒት ክትትል፣ የግል ነርሲንግ፣ አጋዥ ቴክኖሎጂ፣ የአካባቢ ማሻሻያዎች እና ግላዊ የድንገተኛ ምላሽ (PERS) ስርዓትን ይሸፍናል። የግል እንክብካቤ ድጋፍ መስጫ ሰዓት በሳምንት እስከ 56 ሰዓት ድረስ ሊፈቀድ የሚችል ሲሆን በአንድ የስቴት የበጀት ዓመት ውስጥ ከ 480 ሰዓት መብለጥ የለበትም።

አንድ ሰው ለዚህ waiver ብቁ ለመሆን በ Virginia Uniform Instrument (UAI) በሚደረገው ምዘና መሰረት የአካል ጉዳትና የሕክምና እንክብካቤ ፍላጎት ሊኖረው ይገባል፡ https://www.dss.virginia.gov/files/division/dfs/as/as_intro_page/forms/032-02-0168-01-eng.pdf

### ለተጠባባቂ ዝርዝር ብቁ መሆን

ለ Developmental Disabilities Waiver ተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ሊቆዩና ለ CCC Plus Waiver ሊያመለክቱ የሚችሉ ሲሆን፣ ይህ የሚሆነው ግን ለ CCC Plus Waiver እንደዚሁ ብቁ መሆንዎን ታሳቢ በማድረግ ነው። የ CCC Plus Waiver የተጠባባቂ ዝርዝር ስለሌለውና የተወሰኑ ጊዜያዊ ድጋፎችን ስለሚሰጥ በርካታ ሰዎች ይህን ያደርጋሉ።

### የጥበቃ ጊዜው ምን ያህል ነው?

የ Developmental Disability Waivers በፍላጎቱ አጣዳፊነት ላይ የተመሰረተ የተጠባባቂ ዝርዝር አለው። በአንድ ዓመት ውስጥ በአጣዳፊ ፍላጎት አገልግሎቶች የመጀመሪያ ቅደም ተከተል ውስጥ ያሉ ሰዎች፣ በ1-5 ዓመታት ውስጥ በደረጃ ሁለት ቅደም ተከተል ውስጥ ያሉ ሰዎች እና ለበርካታ ዓመታት በደረጃ ሶስት ቅደም ተከተል ውስጥ የቆዩ ሰዎች ይወጣሉ። የቆይታ ጊዜ አስቀድሞ ሊገመት የማይችል ሲሆን በደረጃ አንድ ዝርዝር ውስጥ ያሉ ሰዎች ለ waiver በርካታ ዓመታት ይጠብቃሉ። የኑሮ ሁኔታዎ ሲቀያየር፣ ለምሳሌ እርስዎ ወይም ባለቤትዎ ሲታመሙ፣ ስራ አጥ ሲሆኑ፣ ወዘተ… ለድጋፍ አስተባባሪዎ ያሳውቁ፤ ምክንያቱም እነዚህ ሁኔታዎች የድጋፍ አገልግሎቶችን ለማግኘት የፍላጎትዎን አጣዳፊነት ይጨምሩታል።

**ለ Developmental Disabilities Waivers ለማመልከት የአካባቢዎን Community Services Board ያነጋግሩ።**

Alexandria City CSB: (703) 746-3400
Arlington DHS/IDD Services: (703) 228-1700
Fairfax/Falls Church CSB/IDS: (703) 324-4400

Northern Virginia ውስጥ የማይኖሩ ከሆነ፣ የአካባቢዎን CSB ለማግኘት ይህን ይጎብኙ፡ http://www.dbhds.virginia.gov/community-services-boards-csbs

### ለ CCC Plus Waiver ለማመልከት የካውንቲዎን Department of Social Services ያነጋግሩ

Alexandria City: (703)746-5700
Arlington: (703)228-1350
Fairfax/Falls Church: (703)324-7948

Northern Virginia ውስጥ የማይኖሩ ከሆነ፣ የአካባቢዎን የማሕበራዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት (DSS) ለማግኘት ይህን ይጎብኙ፡ http://www.dss.virginia.gov/localagency/index.cgi

### የ IFSP የገንዘብ ድጋፍ

በ Waiver የተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ላሉ

ለ waiver የተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ከሆኑ፣ ለ Individual and Family Support Program (IFSP፣ ግለሰባዊና የቤተሰብ ድጋፍ ፕሮግራም) ለማመልከት ብቁ ነዎት። ይህ ፕሮግራም በዓመት አንድ ጊዜ የሚከፈት ሲሆን ዓላማውም ለ Developmental Disability Medicaid Waivers የተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች በራሳቸው ማህበረሰብ ውስጥ በራሳቸው ቤት እንዲቆዩ የሚያግዛቸው የአጭር ጊዜ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማድረግ ነው። መረጃ፣ ማመልከቻዎችና መመሪያዎችን እዚህ ማግኘት ይቻላል፡ http://dbhds.virginia.gov/developmental-services/ifsp

## ቅጥያ 5፡ ድሕረ ሞት የሐብትና ንብረት ማስተላለፊያ ዕቅድ ማዘጋጀት

*ሁሉም*ወላጆች ኑዛዜ ማስቀመጥ ያለባቸው ሲሆን አካል ጉዳተኛ ልጆች ያላቸው ደግሞ ልጁ ሊያገኝ የሚችለውን ማንኛውም መንግስታዊ ጥቅማ ጥቅም ለማስጠበቅ የልዩ ፍላጎቶች ትረስት ማቋቋም አለባቸው።

ልጅዎ ወደ 18 ዓመት ዕድሜው (ለአቅመ አዳም ወይም ሔዋን) እየተጠጋ ከሆነ፣ የሕክምና፣ የፋይናንስ እና ሕጋዊ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ እገዛ ከፈለገና መፈለጉን የሚቀጥል ከሆነ የተወሰነ ሕጋዊ ድጋፍ እንዲያገኝ ማሰብ አለብዎት። (የውሳኔ አሰጣጥ አማራጮችን እና ሕጋዊ ስልጣንን በተመለከተ ቀጣዩን ቅጥያ ይመልከቱ)።

**ኑዛዜ ማድረግ**

እርስዎ ከሞቱ በኋላ ሐብቶችዎ እንዴትና ለማን እንደሚከፋፈሉ ፍላጎቶችዎ ይፈጸሙ ዘንድ ኑዛዜ ወሳኝ ነው። አካል ጉዳተኛ ልጅ ካለዎት፣ ይህ እጅግ አስፈላጊ ይሆናል። በልዩ ፍላጎቶች ዕቅድ አወጣጥ ስፔሻላይዝ ያደረገ ጠበቃ ይፈልጉ፤ የእያንዳንዱን ልጅዎን ልዩ ፍላጎቶች ለማስተናገድና የአካል ጉዳተኛ ልጅዎ ጥቅማ ጥቅሞች ወይም አገልግሎቶች እና/ወይም በወንድምና እህት አማቾችና በቤተሰብ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ማድረግ ይችላል። * የጠበቆች ዝርዝር በድረ ገጻችን የአቅራቢዎች አድራሻ ማውጫ ላይ ይገኛል https://thearcofnova.org/directory/። በርካታ ኑዛዜዎች የቤተሰብ መተማመንን የሚፈጥሩ ቢሆንም፣ አካል ጉዳተኛ ልጅዎ የሚያገኛቸው ጥቅማ ጥቅሞች ወይም አገልግሎቶችን አደጋ ላይ ላለመጣል ሲሉ ራሱን የቻለ *የልዩ ፍላጎቶች ትረስት* (ከታች ይመልከቱ) ማቋቋም አለብዎት።

**ተጠቃሚዎችን መቃኘት**

በኑዛዜ አማካይነት የሚወረስ ገንዘብ ተጠቃሚው የልዩ ፍላጎቶች ትረስት እንዲሆን ከመሰየም በተጨማሪ፣ **ከኑዛዜዎ ውጭ ናቸው ተብለው ለሚታሰቡ ሐብቶች የተጠቃሚ ስያሜን መቃኘት አለብዎት**፤ እነዚህም የሚያካትቱት፡

በአሰሪ የሚቀርብ የሕይወት ኢንሹራንስ (ሁለቱም ወላጆች ስራ የሚሰሩ ከሆኑና በስራቸው አማካይነት ኢንሹራንስ ካላቸው፣ የሁለቱንም ተጠቃሚዎች ማጣራትዎን ያረጋግጡ)፤ የግል የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲዎች (የሁሉንም ፖሊሲዎች ተጠቃሚዎች አሁንም ያጣሩ) የግለሰብ የጡረታ ሒሳቦች፣ Roth IRAs* ጨምሮ 401K እና 403(b) ሒሳቦች*፣ SEP Plans*፣ Thrift Savings Plans*፤ ግለሰባዊ ተንቀሳቃሽና የቁጠባ ሒሳቦች፤ Brokerage ሒሳቦች፤ Savings Bonds

የልዩ ፍላጎት ትረስትን የአንድ ወይም ከአንድ በላይ የጡረታ ሒሳብዎ (የ * ምልክት የተደረገባቸው) ተጠቃሚ አድርገው ሲሰይሙ ልዩ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። የልዩ ፍላጎቶች ትረስት የሚያቋቁምበት ሰነድ (ኑዛዜ ወይም ራሱን የቻለ ትረስትም ቢሆን) ትረስቱ ከጡረታ ሒሳቦች የሚከፋፈሉ ክፍያዎችን ለመቀበል የተዘጋጀ "የተጠራቀመ ትረስት" መሆኑን መግለጽ አለበት።

(ይህ ተግባራዊ መሆን የሚጀምረው አካል ጉዳተኛ ልጅዎ 18 ዓመት ሲሞላውና በጎልማሳነት ለ SSI ብቁ ሲሆን ነው። ከ18 ዓመት በኋላ፣ SSI የሚቀበል ጎልማሳ ሊኖረው የሚችለው ሐብት $2,000 ብቻ ነው። በተለመደው አሰራር፣ አንድ ሰው የጡረታ ሒሳብ ሲወርስ፣ ከሒሳቡ በተወሰነ ወቅት ክፍያ መቀበል የሚጀምሩ ሲሆን ይህ ደግሞ እንደ SSI እና Medicaid ካሉ የፌዴራል ጥቅማ ጥቅሞች ሊያስወጣቸው ይችላል)።

ከቤተሰብ አባላት ወይም ከጓደኞች ውጭ ያሉ ወንድም ወይም እህታማቾች ለሚወዱት ሰው የተወሰነ ገንዘብ ለመተዉ ከፈለጉ፣ የልዩ ፍላጎቶች ትረስትን እንደ ተተጠቃሚ አድርገው መሰየም እንዳለባቸው ማሳወቅዎን እርግጠኛ ይሁኑ። የትረስቱን ትክክለኛ ስምና የተመሰረተበትን ቀን ይስጧቸው።

**የልዩ ፍላጎቶች ትረስት (SNT)**

የልዩ ፍላጎቶች ትረስት (አንዳንድ ጊዜ የተጨማሪ ጥቅማ ጥቅሞች ትረስት ተብሎ ይጠራል) ቤተሰቦች አካል ጉዳተኛ የሆኑ ወዳጅ ዘመዶቻቸውን የወደፊት የፋይናንስ መረጋጋት እንዲያስተማምኑ ያስችላቸዋል። አንዳንድ የፌዴራል ጥቅማ ጥቅሞች ፕሮግራሞች በተጠቃሚው ሐብቶችና ንብረቶች ላይ ጠበቅ ያሉ ገደቦችን የሚጥሉ በመሆኑ፣ ልጅዎ ለምሳሌ ያልተጠበቀ ውርስ ወይም ከፍ/ቤት ክስ ክፍያ ሲያገኙ ከጥቅማ ጥቅሞች ውጭ ሊደረግ ይችላል። ይሁን እንጂ፣ ቤተሰቦች መንግስታዊ ጥቅማ ጥቅሞችን ***ሳያጡ*** ውርስ፣ አክሲዮን፣ ንብረት፣ የኢንሹራንስ ክፍያ ወይም ሌሎች ሐብቶችን የሚያስቀምጡበት የልዩ ፍላጎቶች ትረስት (SNT) እንዲያቋቁሙ ሕጉ ይፈቅድላቸዋል።

አካል ጉዳተኛ የሆነ የቤተሰብዎ አባል የተጨማሪ ዋስትና ገቢ (SSI) እና Medicaid ከተቀበለ (ወይም እነዚህን ጥቅማ ጥቅሞች ለማግኘት ጥያቄ እንዲያቀርብ ለማድረግ እያሰቡ ከሆነ)፣ የልዩ ፍላጎቶች ትረስት ማቋቋም ግዴታ ይሆናል፤ እነዚህ ፕሮግራሞች የቤተሰብዎ አባል ብቁ እንዲሆን ሐብቱ በ $2,000 እንዲገደብ ያደርጋሉ።

ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ለማሕበራዊ ዋስትና የአካል ጉዳተኝነት ገቢ (SSDI) ፕሮግራም የተቀመጠ የገቢ ወይም የሐብት ገደብ ባይኖርም፣ የ SSDI ጥቅማ ጥቅሞችን የሚያገኙ ግለሰቦች ለገንዘብ አስተዳደር ዓላማ ሲባል የአንደኛ ወገን የልዩ ፍላጎቶች ትረስት (ከታች ይመልከቱ) ማቋቋም አለባቸው።

**ሁለት ዓይነት ትረስቶች**

አብዛኞቹ የልዩ ፍላጎቶች ትረስቶች ***የሶስተኛ ወገን ትረስቶች*** (ወጪያቸው በቤተሰብ የሚሸፈን ትረስቶች) ሆነው የሚቋቋሙትም ለአካል ጉዳተኛ ልጆቻቸው በወላጆች ወይም እንደ The Arc of Northern Virginia ባሉ የተፈቀደላቸው ለትርፍ የማይሰሩ ድርጅቶች ነው። ትረስቱን የሚያቋቁመው ሰው በተለምዶ ሴትለር ተብሎ የሚጠራ ሲሆን የራሱን የተወሰነ ሐብት ተጠቃሚውን (አካል ጉዳተኛውን) ለመጥቀም ዝግጁ ያደርጋል።

እነዚህ ትረስቶች በወላጆች የሕይወት ዘመን የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙ ሊሆኑ ይችላሉ። በሕይወት እያሉ መዋጮ ሊያደርጉባቸው ይችላሉ ወይም ወላጅ(ጆች)፣ ጓደኛ፣ ወዘተ ሲሞት በውርስ፣ በሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ወይም ከሌላ ትረስት በማስተላለፍ ወጪውን ሊሸፍኑ ይችላሉ።

***አንደኛ ወገን ትረስቶች***(ወጪያቸው በራስ የሚሸፈን ወይም በራስ የሚከፈል) በተጠቃሚው፣ በወላጅ፣ በአያት፣ በአሳዳጊ ወይም በፍ/ቤት ትእዛዝ መሰረት የሚቋቋሙ ሆነው የገንዘብ ምንጫቸውም የአካል ጉዳተኛው ሐብቶች ናቸው። የአንደኛ ወገን ትረስቶች የተለመዱ የገንዘብ

ምንጮች አስቀድመው የተመቻቹ ክፍያዎች፣ ከማሕበራዊ ዋስትና የተገኘ ጥቅል ተመላሽ ክፍያ፣ አካል ጉዳተኛ ልጅ ላለው ጎልማሳ በማይሻር ሁኔታ የተመደበ የልጅ ተቆራጭና የጉዳት ሰለባ ጥቅማ ጥቅሞችና በስህተት ለአካል ጉዳተኛው የተላለፈ ውርስ ናቸው።

በአጠቃላይ ጉዳዮች ላይ እውቀት ያለው ጠበቃ ጋር በርካታ ሕግ ነክ ጉዳዮች ሊከናወኑ ቢችሉም፣ SNTs ባላቸው የውስብስብነት ባህርይ ምክንያት በአካል ጉዳተኝነትና በዚህ ዓይነት ትረስት ላየ ልምድ ያካበተ የሕግ ወይም የልዩ ፍላጎቶች ጠበቃ አገልግሎትን ማግኘት ሊያስፈልግዎ ይችላል።

**ትረስት ማቋቋም**
ወላጅ ከሞት በኋላ አጠቃላይ ሐብቱን የሚያስተላልፈበትን ሁኔት ሲያቅድ የልዩ ፍላጎቶች ትረስት መቋቋም ይችላል ወይም መቋቋም አለበት።

በየትኛውም አማራጭ ቢሆን ትረስቱን ለማቋቋምና ምናልባትም ገንዘቡን ለማስተዳደር ክፍያ መክፈል ይኖርብዎታል። The Arc of Northern Virginia's የልዩ ፍላጎቶች ትረስት ፕሮግራም መነሻ ተቀማጭ እንዲኖር አይጠይቅም።

**የትረስት ፈንዱ አገልግሎት**
ከልዩ ፍላጎቶች ትረስት የሚገኝ ገንዘብ አብዛኛውን ጊዜ በቀጥታ ለተጠቃሚው አይከፋፈልም፣ የዚህ ምክንያት ደግሞ አንዳንድ መንግስታዊ ጥቅማ ጥቅሞችን አደጋ ላይ እንዳይጥል ነው። ከዚህ ይልቅ፣ ለተጠቃሚው ጥቅምና ደስታ የሚውሉ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ለሚያቀርቡ ሶስተኛ ወገኖች ይከፋፈላል። የትረስት ገንዘቦች የወዳጅዎን ለመንግስታዊ ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ መሆን ስጋት ላይ በማይጥል ሁኔታ ለተለያዩ ሕይወትን ለሚያጎለብቱ ወጪዎች ይውላሉ፡
አንዳንድ ምሳሌዎች ቀጥሎ ቀርበዋል፡

- ለትምህርትና ለግል ጥናት
- ከኪስ ለሚከፈል የሕክምና እና የጥርስ ሕክምና ወጪዎች
- ትራንስፖርት (የመኪና ግዥን ጨምሮ)
- የተሽከርካሪ እድሳት፣ የመኪና ኢንሹራንስ
- ለሆቢ ወይም ለመዝናኛ ተግባራት የሚውሉ ቁሳቁስ ለመግዛት
- ጉዞ፣ ሽርሽር፣ ሆቴሎች፣ የአውሮፕላን ትኬት
- እንደ ፊልም ወይም የኳስ ጨዋታ ያሉ መዝናኛዎች
- ኮምፒዩተሮች፣ ቪድዮ፣ የቤት ዕቃ ወይም ኤሌክትሮኒክስ
- የአትሌቲክስ ስልጠና ወይም ውድድሮች
- ልዩ የምግብ ፍላጎቶች
- አልባሳት
- የቤት ውስጥ ወጪዎች (ምንም እንኳን የ SSI ጥቅማ ጥቅሞችን ቢቀንስም)
- ዝርዝሩ በጣም ሰፊ ነው!

**ባለአደራ ሆኖ መስራት**
ባለአደራ ማለት የትረስት ሐብቶችን የሚቆጣጠርና የትረስት አከፋፈልን የሚያስተዳድር ሲሆን፣ እነዚህም የሚያካትቱት ኢንቨስት ማድረግ፣ ሒሳብ ሪፖርት ማድረግና ታክስ ሪፖርት ማድረግ፣ የቼክ አጻጻፍና የክፍያ አፈጻጸም ናቸው። የ The Arc of Northern Virginia ባለአደራ ወሳኝ የግል ባንክ (Key Private Bank) ሲሆን ትረስቱን የሚያስተዳድረውና የዕለት ተዕለተ የደንበኞች ግንኙነትን የሚመራው ደግሞ The Arc ነው። ሙያዊ የሆነ የሕግ እና የኢንቨስትመንት ምክር የልዩ ፍላጎቶች ትረስትን ለሚያስተዳድሩ ባለአደራዎች እጅግ ወሳኝ ነው።

በ The Arc of Northern Virginia ለተቋቋመ ትረስት፣ ቤተሰቡና ተጠቃሚው ይህን ትረስቱን የማስተዳደር ሸክም የለባቸውም። የትረስቱ ሰራተኞች ሁሉንም አስተዳደራዊ ስራዎችና የደንበኞች ግንኙነትን የሚያከናውኑ ሲሆን፣ Key Bank ደግሞ ሁሉንም የገንዘብ ነክና የኢንቨስትመንት ተግባራትን ያከናውናል።

ባለአደራ ስለመሆን ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ከቀጣዩ ድረ ገጽ ነጻ የመረጃ ጥራዝ ያውርዱ፡
https://www.specialneedsalliance.org/

ስለ The Arc of Northern Virginia የልዩ ፍላጎቶች ትረስት የበለጠ ለማወቅ ይህን ይጎብኙ https://thearcofnovatrust.org/ ወይም Tia Marsili, Director of Special Needs Trusts በቀጣዩ አድራሻ አግኝተው ነጻ የምክር አገልግሎት ያግኙ tmarsili@thearcofnova.org ወይም ቀጣዩን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡ http://thearcofnovatrust.org/make-an-appointment/። በተጨማሪም፣ በልዩ ፍላጎቶች ትረስት ላይ ያተኮሩ የአነስተኛ ቡድን ውይይቶችን በወር ሁለት ጊዜ ዘወትር ማክሰኞ Trust Talk በሚል ርዕስ እናቀርባለን https://thearcofnovatrust.org/events/።

## የ ABLE ሒሳቦች
የ ABLE ሒሳቦች አንዳንድ አካል ጉዳተኞችና ቤተሰቦቻቸው ብቁ የሆኑባቸው ጥቅማ ጥቅሞች እንደተጠበቁ ሆነው ለወደፊቱ ገንዘብ የሚቆጥቡበት ተጨማሪ መንገዶች ናቸው።

በ2014 መጨረሻ ላይ በኮንግረስ የጸደቀው የ Achieving a Better Life Experience (ABLE) Act ግዛቶች ለተወሰኑ አካል ጉዳተኞች ከአካል ጉዳታቸው ጋር በተያያዘ ለሚያወጧቸው ወጪዎች ከታክስ ነጻ የሆኑ የቁጠባ ሒሳቦችን እንዲያቋቁሙ ይፈቅዳል።
በተጨማሪም፣ እነዚህ ገንዘቦች ለተጨማሪ ዋስትና ገቢ (SSI) ፕሮግራም (እስከ $100,000)፣ ለ Medicaid እና ለተወሰኑ ሌሎች በፌዴራል ለሚተዳደሩ ጥቅማ ጥቅሞች እንዲውሉ አይታሰቡም።

የ ABLE ሒሳቦች በቤተሰብ ወጪው የሚሸፈን የልዩ ፍላጎቶች ትረስትን አስፈላጊነት የማያስቀሩ ሲሆን በጣምራ ግን ሊያገለግሉ ይችላሉ። በ ABLE ሒሳብ ውስጥ ያለ ገንዘብ ለተረጋገጡ ከአካል ጉዳት ጋር የተያያዙ ወጪዎች ብቻ መዋል አለበት። የ ABLE ሒሳቦች ዋና ዋና ክፍሎች ከአንደኛ ወገን ወይም በራስ ወጪ የሚሸፈን ትረስት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፤ ምክንያቱም ተጠቃሚው በሚሞትበት ወቅት የ Medicaid ተመላሽ ክፍያን ስለሚጠይቁ ነው።

ስለ ABLE ሒሳቦች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ፡ www.ablenlc.org። በቨርጂኒያ ውስጥ ስለ ABLE የበለጠ ለማወቅ ወይም ሒሳብ ለመክፈት፣ ወደ ABLEnow https://www.able-now.com/ይግቡ። በልዩ ፍላጎቶች ትረስት እና በ ABLE ሒሳቦች መካከል ስላለው ልዩነት የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት፣ ቀጣዩን የ Arc of Northern Virginia Trusts ድረ ገጽ ይጎብኙ፡
https://thearcofnovatrust.org/pooled-trusts/abel-accounts/

## ቅጥያ 6፡ የውሳኔ አሰጣጥ ድጋፎችና የሕጋዊ ስልጣን አማራጮች

ቤተሰቦች ብዙውን ጊዜ የሞግዚትነትና ሌሎች የሕጋዊ ስልጣን መንገዶችን አስፈላጊነትና ዋጋ ለመወሰን ይቸገራሉ፣ በተለይ ደግሞ "ለሰው ጥበቃ ከማድረግ" ጋር የተያያዙ ሲሆኑ። አግባብነት ያለው የትኛው ነው ለሚለው መልሱ በሰውዬው ላይ የተመሰረተ ነው። *ሞግዚትነትና ተመሳሳይ እርምጃዎች በሆነ ወረቀት ላይ የተጻፉ ሕጋዊ ስልጣኖች መሆናቸውን ማስታወሱ እጅግ ወሳኝ ነገር ነው። አንድ ሰው የሆነ ነገር እንዳያደርግ ሊከለክሉት አይችሉም። አንዳንድ የፋይናንስ ችግሮችን "ለማጽዳት" አጋዥ ሊሆኑ ይችላሉ።*

The Disability Law Center of Virginia www.dlcv.org የተለያዩ የሕጋዊ ስልጣን አማራጮችን መመዘንን በተመለከተ በድረ ገጹ ላይ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን የውክልና ስልጣን ማስረጃ የመሳሰሉ ሰነዶችን ለማዘጋጀት ማውረድ የሚችሏቸውን ናሙናዎችና የሕክምና መመሪያዎችም ያቀርባል።

### የስጋት እና የሚደገፍ ውሳኔ አሰጣጥ ልዕልና

በቅርብ ዓመታት ውስጥ ሁላችንም ውሳኔ ልንሰጥበት ስለሚገባ "የስጋት ልዕልና" ስለመነጋገር እንቅስቃሴ ተጀምሯል። ጽንሰ ሃሳቡ ሁላችንም ሰዎች አንዳንድ ውሳኔዎችን ለመወሰን እገዛ ያስፈልገናል፣ ሁላችንም የምንማረው ደግሞ መጥፎ ውሳኔዎችን በመወሰን ነው ይላል። ለምሳሌ፣ የዕድገት መዘግየት የአካል ጉዳት የሌለባቸው በርካታ ሰዎች ሕይወት ነክ ውሳኔዎች እነርሱ በሚገባቸው ቀላል ቃላት እንዲነገራቸው በታክስ አካውንታንቶች ወይም ዶክተሮች ላይ ይተማመናሉ። ይህ ሃሳብ "የተደገፈ ውሳኔ አሰጣጥ" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ከዚህ ፖሊሲ አንጻርም እያደገ የመጣ ዓለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ አለ። ለአካል ጉዳተኛ የሚጨነቁ ሰዎችን የያዘ ቡድን የድጋፍ ክበብ ይመሰርቱና ሰውየው ውሳኔዎችን እንዲረዳና እንዲያሳልፍ ያገዙት ዘንድ አብረው እንዲሰሩ ጠየቃቸው። ሕጋዊ መብቶችን ማሳጣትን የማይጨምር ቢሆንም በጊዜ ሂደት ግን ድጋፍ ሰጪ ቡድን እና ውሳኔ የመስጠት ችሎታና ራስን መቻልን ይገነባል። ወጪ የሌለው ሲሆን ምናልባትም ቀደም ሲል እየሰሩት ያሉት ነገር ሊሆን ይችላል። የተደገፈ ውሳኔ አሰጣጥ ቡድኑ ግለሰቡን ወክሎ እንዲናገር ወይም ውሳኔውን እንዲሽር የሚያችለው ምንም ዓይነት ሕጋዊ ስልጣን አይሰጠውም። የተደገፈ ውሳኔ አሰጣጥን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘትና በርዕሱ ላይ የተዘጋጁ የቪድዮ መረጃዎችን እዚህ ይመልከቱ http://supporteddecisionmaking.org/

"የስጋት ልዕልና" ማለት የተወሰኑ መጥፎ ውሳኔዎችን መወሰን ችግር እንደሌለው መገንዘብም ማለት ነው። ለሁላችንም የተፈቀደ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜም የበለጠ የምንማረው በዚህ መንገድ ነው። በርካታ ሰዎች የሚማሩት በጣም ብዙ ወጪ ካወጡ በኋላ በመሆኑ የአገልግሎት ሂሳብ ለመክፈልና ብዙ ስለሚመገቡም ከክብደት መጨመርና ከጤና ችግሮች ለመማርም አስቸጋሪ ነው። ይህ መብት የሁሉም ሰዎች በመሆኑ በየቀኑም ይተገብሩታል። አካል ጉዳተኞች በቀጣይ ጊዜ እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው ውሳኔዎችን ለመወሰንና በተፈጥሯዊ ተከታይ ውጤቶች እና በድጋፍ ሰጪ ቡድን አማካይነት ለመማር ተመሳሳይ ዕድሎች ሊኖራቸው ይገባል።

### የሕጋዊ ስልጣን አማራጮች፡ አማራጮችን መመዘን

ሞግዚት ወይም የንብረት ጠባቂ መሾም የመጨረሻው አማራጭ ተደርጎ መቆጠር አለበት። የሕጋዊ ስልጣን አማራጮችን ዝርዝርና መግለጫ በገጽ 32 ላይ የሚገኘውን ቻርት ይመልከቱ። የሞግዚትነት አመልካቾች አንድ ሰው የተወሰኑ ውሳኔዎችን ለመወሰን "ችሎታ የሌለው" ስለመሆኑ ማስረጃ አቅርበው ዳኛውም ሊያጸናው ይገባል።

ይሁን እንጂ፣ ግለሰቡ "ችሎታ የሌለው" ባይባልም አሁንም እገዛ ካስፈለገው፣ ግለሰቡና ቤተሰቡ ከሌሎች በርካታ አማራጮች መካከል ሊመርጡ ይችላሉ። እነዚህ አማራጮች ተንከባካቢ (ውሳኔዎችን ለመወሰን ሕጋዊ ስልጣን የሌለው) ከመመደብ አንስቶ ለሚታመን ሰው ትምህርት፣ ሕክምና፣ ሕግ ነክና ፋይናንስን በተመለከተ ውሳኔዎችን እንዲወስን የሚያስችል ዘላቂ የውክልና ስልጣን እስከመስጠት ሊደርሱ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ የተወሰነ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ግለሰብ የውክልና ስልጣን ወይም የቅድሚያ የሕክምና መመሪያ በመፈረም እርስዎ ወይም ሌላ የቤተሰብ አባል የውሳኔ አሰጣጥ ወኪላቸው እንዲሆኑ ማድረግ ይችላል።

### ለትምህርት ጉዳይ የሚሰጥ የውክልና ስልጣን

መብቶችን ስለማስተላለፍ ከ IEP ቡድንዎ ጋር ይነጋገሩና ለትምህርት ጉዳይ የሚሰጥ የውክልና ስልጣንን ያስቡ። ይህ አማራጭ ተማሪው ውሳኔ አሰጣጡን እንዲቆጣጠር ያስችለዋል። "የትምህርት ጉዳይ ተወካይ" ማለት ወላጅ፣ የቤተሰብ አባል ወይም የጐልማሳ ተማሪን በመወከል ትምህርት ነክ ውሳኔዎችን እንዲወስን የተፈቀደለት ሌላ ጎልማሳ ሰው ነው። የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን የሙብት ማስተላለፍ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ከዚህ ያገኛሉ፡ www.doe.virginia.gov/special_ed/regulations/state/transfer_rights_students_disabilities.pdf። ለትምህርት ጉዳይ የሚሰጥ የውክልና ስልጣን ናሙና ከዚህ ማግኘት ይቻላል፡ http://www.doe.virginia.gov/special_ed/regulations/state/transfer_rights_students_disabilities.pdf።
FCPS የሚሞላ የ PDF ለትምህርት ጉዳይ የሚሰጥ የውክልና ስልጣን ያቀርባል https://www.fcps.edu/sites/default/files/media/forms/se340.pdf.

### የቁም ኑዛዜ

የቁም ኑዛዜ እርስዎና ልጅዎ ወደፊት በመረጃ የተደገፈ ውሳኔ ለመስጠት ወይም ፍላጎቱን ለመግለጽ በማይችልበት ጊዜ እንዲዘጋጅ ያግዛችኋል። ወኪል (ወላጅ፣ ዘመድ ወይም ሌላ ታማኝ ጎልማሳ) አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ የጤና እንክብካቤ ውሳኔዎችን የሚወስን ሲሆን ግለሰቡም ለመወሰን የሚችለውን ውሳኔ የመወሰን ሙብት ይሰጠዋል። የቁም ኑዛዜ የሚደረገባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡ ናሙና ቅጾችን እዚህ ማግኘት ይችላሉ፡ http://www.virginiaadvancedirectives.org/፤ እርስዎና ልጅዎ የቁም ኑዛዜ ስለማድረግ ከዶክተርዎ ጋር መነጋገር አለባችሁ፤ የቁም ኑዛዜ ለመፈጸም ጠበቃ መቅጠር ይችላሉ። የልጅዎ የቁም ኑዛዜ አንዴ ከተጻፈ፣ ሁለት ምስክሮች በተገኙበት መፈረም አለበት። በቨርጂኒያ ሕግ መሰረት በውል አዋዋይ መረጋገጥ ባያስፈልገውም፣ ከተቻለ ይህን ማድረጉ ጥሩ ሃሳብ ነው። አስፈላጊ ፊርማዎች ከሰፈሩበት በኋላ፣ ለወኪሉ፣ ለዶክተሮችና ሌሎች ታማኝ የቤተሰብ አባላት ኮፒዎችን መስጠት አለብዎት። የቁም ኑዛዜውን ወደዚህ ገብተው ኦንላይን ማስመዝገብም ይችላሉ፡ www.virginiaregistry.org።

*ይህ መረጃ ከ www.dlcv.org (The Disability Law Center of Virginia) የተወሰደ ነው።*

### ሞግዚትነትና የንብረት ተቆጣጣሪነት

ሞግዚቶችና የንብረት ተቆጣጣሪዎች ችሎታ የሌለውን ሰው፣ ማለትም መረጃ በትክክል ተቀብሎ ወይም ገምግሞ የጤና፣ የእንክብካቤና የደህንነት

ፍላጎቶቹን ለማሟላት ወይም የንብረት ወይም የፋይናንስ ጉዳዩን ለማስተዳደር የማይችልን ሰው ለመጠበቅ በአካባቢው ፍ/ቤት ይሾማሉ። አንድ ግለሰብ በሞግዚት ስር የሚደረገው የተሳሳተ ሕሊናዊ ፍርድ ስላለው ብቻ ሳይሆን ጥሩ ምርጫዎችን የመገንዘብና የመምረጥ ችሎታቸው ውስን ስለሆነ ነው።

ሞግዚት እና/ወይም የንብረት ተቆጣጣሪ አብዛኛውን ጊዜ ለአካል ጉዳተኛ ሰው ይሾምለታል። ይሁን እንጂ፣ **አንድ ሰው ችሎታ የሌለው መሆኑን የሚወስነው የወረዳ ፍ/ቤት ዳኛ ብቻ ሲሆን** ለዚሁ ግለሰብ ሞግዚት እና/ወይም የንብረት ተቆጣጣሪ የሚሾመውም ይሄው አካል ነው። የሞግዚት ወይም የንብረት ተቆጣጣሪ ሹመት መደበኛ ተግባር አይደለም፤ እንደ የሕግ ስርዓቱ ሁሉ እኛም በጣም ትልቅ ቁምነገር ጉዳዩን ማየታችን ተገቢ ነው።

በመሰረቱ፣ **ሞግዚትነት** አንድ ሰው (ለምሳሌ ወላጆች) ውሳኔዎችን ሙሉ በሙሉ በራሱ መወሰን በማይችል ሰው ስም *ሕጋዊ ውሳኔዎችን እንዲወስን* ኃላፊነት ይሰጠዋል። ሞግዚት የሕክምና፣ የመኖሪያ ቦታና ሌሎች ማሕበራዊ ውሳኔዎችን ይወስናል። ቨርጂኒያ ውስጥ፣ ሞግዚትነት ከግለሰቡ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም መደረግ ይችላል፣ ለዚህም የተወሰኑ መብቶች ተወስደው የተወሰኑት ይጠበቃሉ (ማለትም፣ ድምፅ የመስጠት መብት)። በሞግዚትነት ሕግ ልምድ ያለው ጠበቃ ለግለሰቡ ተስማሚ የሆነና እርስዎም ለአካል ጉዳተኛው ጠንካራ ተሟጋች ሆነው እንዲቀጥሉ የሚያስችልዎትን ሞግዚትነት በማዘጋጀት ረገድ ሊያግዝዎ ይችላል። **የንብረት ተቆጣጣሪ** ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት የሚያተኩረው የግለሰቡን የፋይናንስና የንብረት ጉዳዮች ማስተዳደር ላይ ነው። እንደ ሞግዚቱ ሁሉ፣ የንብረት ተቆጣጣሪው ስልጣንም ችሎታ ባጣው ሰው ሁኔታ መሰረት ሊገደብ ይችላል።

ፍ/ቤቱ ሞግዚት ብቻ፣ ንብረት ተቆጣጣሪ ብቻ፣ ወይም ሁለቱንም ሊሾም ይችላል። ለአብዛኞቹ አካል ጉዳተኛ ታዳጊ ጎልማሶች ሞግዚት ብቻ ነው የሚያስፈልጋቸው። አብዛኛውን ጊዜ፣ አፍላ ጎልማሳው የሚኖረው ሐብት ከ $2,000 ያነሰ ነው፤ ብቸኛው ገቢው ከ SSI የሚገኝ ነው ወይም በተወካይ ተከፋይ ወይም ግለሰቡ የተወሰነ ድጋፍ አግኝቶ ሊያስተዳድራቸው የሚችላቸው ገቢዎች ናቸው። የሞግዚቱ ወይም የንብረት ተቆጣጣሪው የስልጣን ወሰን በዳኛው ውሳኔ እና በቨርጂኒያ ሕግ ውስጥ ይገለጻል።

**ሞግዚትነትን ማሰብ**
በሞግዚትነት ውስጥ፣ ሕጉ የጎልማሳውን መብቶችና ግላዊ ነጻነት በማስጠበቅና የ Commonwealth of Virginia (የቨርጂኒያ ጋራ ብልጽግና) ራሳቸውን ወይም ንብረታቸውን በተመለከተ ውሳኔዎችን የመወሰን በቂ ችሎታ የሌላቸውን ግለሰቦች ለመጠበቅ ባለው ግዴታ መካከል ሚዛን ያስጠብቃል።

ቤተሰቦች ግለሰቡ "ችሎታ የሌለው" የሚለውን መስፈርት አያሟላም ብለው ካሰቡ፣ ለሞግዚትነት ከማመልከታቸው በፊት ገዳቢነታቸው አነስተኛ የሆኑ አማራጮችን ማሰብ አለባቸው። ሞግዚትነትን እያሰቡ ያሉ ወላጆች የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው:

- ባጠቃላይ፣ ሞግዚትነት **ቨርጂኒያ ውስጥ ያለ ተለዋዋጭ ስርዓት**መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።
- ሞግዚትነት **ከልጅዎ ፍላጎቶች ጋር እንዲጣጣም** ሊደረግ ስለሚችል ወላጆች ጠንካራ የተሟጋችነት አቋማቸውን ይዘው እንዲቆዩ ያስችላቸዋል።
- የዚህ የተለዋዋጭነት አንድ አካል በመሆኑም፣ **ሞግዚትነት ሁሉንም የግለሰቡን መብቶች ማሳጣት አያስፈልገውም።** ለምሳሌ፣ ድምፅ የመስጠት መብት፣ መንጃ ፈቃድ የመያዝ መብትና ሌሎች መብቶችን ጠብቆ ማቆየት በጣም የተለመደ ነው።
- ጎልማሳ ልጅዎ በሞግዚትነት ስር ቢሆንም እንኳን ችሎታው እስከፈቀደለት ድረስ ሕይወቱን በተመለከተ **የውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ሊሳተፍ ይችላል።** የሞግዚትነት ትእዛዙ አካል ጉዳተኛው ሃሳቡ እንዲጠየቅና ፍላጎቱም ከግምት ውስጥ እንዲገባ ይገልጻል።
- **ልጅዎ ለመንግስታዊ ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ መሆኑ ይቀጥላል።** አንድ ሰው ሞግዚት ስለተሾመለት ብቻ መንግስታዊ ጥቅማ ጥቅሞቹን አያጣም። የአካል ጉዳተኛው ጎልማሳ ጥቅማ ጥቅሞች በሚሰሉበት ወቅት የሞግዚቱ ገቢና ሐብቶች ከግምት ውስጥ አይገቡም።
- ሞግዚትነት **በሞግዚትነት ስር ላለ ሰው የፋይናንስ ኃላፊነት አያስከትልብዎትም።** ለምሳሌ፣ ሞግዚት የሆኑ ወላጆች ለልጃቸው ምግብና መጠለያ ማቅረብ ባይጠበቅባቸውም ልጃቸው የት እንደሚኖርና ምን ዓይነት እንክብካቤ እንደሚያገኝ የተመለከቱ *ውሳኔዎችን* የመወሰን ኃላፊነት አለባቸው።
- ሞግዚት እንደመሆንዎ፣ **ለልጅዎ የፋይናንስ፣ የፍትሐ ብሔር ወይም የወንጀል ተጠያቂነት ኃላፊነት የለብዎትም።** በሞግዚትነት ስር ያለ ግለሰብ ሌላ ሰው ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ካደረሰ፣ ሞግዚቱ ተጠያቂ አይደለም። ተጠያቂ ቢደረጉ ኖሮ፣ ሞግዚት ሆነው ለመስራት የሚፈልጉ ሰዎች ጥቂት በሆነ ነበር። ሞግዚቶች ለግለሰቡ ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን ለማመቻቸት የመሞከር ግዴታ አለባቸው።

ወላጆች ብዙ ጊዜ በሞግዚትነት የሚሾሙ ቢሆንም፣ ሌሎች የቤተሰብ አባላት፣ ጠበቃ፣ ጓደኛ ወይም የሕዝብ ሞግዚትም በዚህ ኃላፊነት ማገልገል ይችላሉ።

ለታዳጊ ጎልማሳዎ ተገቢው ምርጫ ሞግዚትነት መሆኑን ለመወሰን እንዲያግዝዎ፣ ማጣሪያውን ያጠናቅቁ። በግብአት ቤተ መጻሕፍታችን ውስጥ ሕጋዊ ስልጣን በሚለው ስር ያለው "Thinking About Guardianship Checklist" http://www.virginiaadvancedirectives.org/።

**ሞግዚትነት ማግኘት**
ሞግዚትነት ለማግኘት፣ ወላጆች ግለሰቡ በሚኖርበት ክልል ወሰነ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ አለባቸው። አብዛኛውን ጊዜ፣ ወላጆች የጋራ ሞግዚት ሆነው የሚሾሙ በመሆናቸው እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው እንዲንቀሳቀሱ ያስችላቸዋል። ሞግዚትነት ያስፈለገበትን ምክንያት ለመደገፍ የሚወዱትን ሰው የሕክምና ወይም የስነ-ልቦናና ግምገማ ውጤት ማቅረብ አለብዎት። እርስዎ ማገልገል በማይችሉ ጊዜ መተካት የሚችሉ "ተጠባባቂ" ሞግዚቶችን እንዲሾም ፍ/ቤቱን ሊጠይቁ ይችላሉ።

አቤቱታው ሲቀርብ፣ ፍ/ቤቱ guardian ad litem (GAL) ይሾማል። GAL በግል የጥብቅና ስራ ላይ የተሰማራና ከተፈቀደው ዝርዝር ውስጥ የተመረጠ ጠበቃ ነው። የ GAL ተቀዳሚ ስራ የአካል ጉዳተኛው ግለሰብ መብቶች መጠበቃቸውን ማረጋገጥ ነው። ስለዚህ፣ GAL ከግለሰቡ ጋር ይገናኛል፣ የፍ/ቤት ሰነዶችን ይሰጠዋል፣ መብቶቹንም ያስረዳዋል። GAL ለፍ/ቤቱ ሪፖርት የሚያቀርብም ሲሆን ሞግዚት መሾሙ አስፈላጊ ስለመሆኑና ማን መሾም እንዳለበት በተመለከተ አስተያየቱንም ይሰጣል።

GAL ሪፖርት ካቀረበ በኋላ ችሎቱ በፍ/ቤት ይካሄዳል። አብዛኛውን ጊዜ፣ በሞግዚትነት የሚሾሙት ሰዎች በችሎት መገኘት አለባቸው፣ ከችሎቱ መጠናቀቅ በኋላም ወደ ፍ/ቤቱ ጸሐፊ ሄደው አስፈላጊ የሆኑ የወረቀት ስራዎችን ያጠናቅቃሉ። ሞግዚት የሚሾምለት ግለሰብ በችሎቱ ላይ ሊገኝ ወይም ላይገኝ ይችላል። ሞግዚትነት ለማግኘት የሚወስደው የተለመደ ጊዜ ወደ 3 ወር አካባቢ ቢሆንም እስከ 6 ወር ድረስ ሊወስድ ይችላል። ሞግዚት በመሆንዎ፣ በአካባቢዎ ለሚገኝ የማሕበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ በየዓመቱ ሪፖርት ማቅረብ አለብዎት፤ ቅጹን ከፍ/ቤት ማግኘት ይችላሉ።

ሞግዚትነት ወይም ሌላ ሕጋዊ ስልጣን ለማግኘት ፍላጎት ካለዎት፣ The Arc of Northern Virginia የአገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር ስር የአረጋውያን ተንከባካቢ ጠበቆችን ዝርዝር ማግኘት ይችላሉ https://thearcofnova.org/directory/

1በዚህ ክፍል ውስጥ ለሰሩት ስራና ወላጆች በሞግዚትነት ላይ ውሳኔ ሲወስኑ በሚያጋጥሟቸው ጉዳዮች ላይ ለሰጡት ሃሳብ ምስጋና ለ Kelly Thompson, Esq., and Loretta Morris Williams, Esq.

**ውሳኔ የመስጠት የስራ ድርሻን መወሰን**

| ዓይነት | ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነቶች | ማስታወሻዎች |
|---|---|---|
| የተደገፈ ውሳኔ አሰጣጥ | አካል ጉዳተኛ ግለሰብ ከቤተሰብ ወይም ተዛማጅ እውቀት ካላቸው ከሌሎች አካላት በሚያገኘው ድጋፍ ውሳኔ ይወስናል | www.supporteddecisonmaking.com |
| ለጎልማሳ የግል ደህንነት ጥበቃ አገልግሎቶች የሚሰጥ አጣዳፊ ትእዛዝ። | የአጭር ጊዜ ሞግዚትነት (15 ቀናት) አጣዳፊ ሁኔታን ለማስተናገድ ወይም አጣዳፊ ሁኔታ ያስከተሉ ሁኔታዎችን ለማስተካከል | የአካባቢው የማሕበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ ጊዜያዊ የሞግዚትነት ትእዛዝ እንዲሰጥ ለወረዳ ፍ/ቤት ማመልከት አለበት |
| ዘላቂ የውክልና ስልጣን | ወላጅ ወይም ሌላ ሰው (ወኪል) አካል ጉዳተኛውን (ወካይ) በመወከል ውሳኔዎችን እንዲወስን ስልጣን የሚሰጥ የጽሑፍ ሰነድ። ወካይ ችሎታ ቢያጣም እንኳን ወኪል ተግባሩን ማከናወን ይችላል። | ወኪል ውሳኔዎችን መሻር አይችልም<br>ወካይ ከሻረው ወይም ከሞተ ስልጣኑ ያበቃል |
| ለትምህርታዊ ውሳኔዎች የሚሰጥ የውክልና ስልጣን | ወላጅ ወይም ሌላ ሰው በ IDEA ስር ለሚተላለፉ ትምህርታዊ ውሳኔዎች የውክልና ስልጣን የሚሰጥ የተጻፈ ሰነድ | የናሙና ቅጾችን ከ FCPS ማግኘት ይቻላል፡ https://www.fcps.edu/sites/default/files/media/forms/se340.pdf and VDOE http://www.doe.virginia.gov/special_ed/regulations/state/transfer_rights_students_disabilities.pdf |
| የቁም ኑዛዜ | አካል ጉዳተኛው ስለ የጤና እንክብካቤ ሕክምና ያለውን ምኞት በተመለከተ መመሪያ የሚሰጥ ሲሆን እርሱ በማይችልበት ጊዜ የጤና እንክብካቤ ውሳኔዎችን የሚወስን ወኪል ይሰይማል። ከሕክምና የውክልና ስልጣን ጋር ሊጣመር ይችላል። ቨርጂኒያ ውስጥ በምስክር መረጋገጥ አለበት። | የወኪሉ ስልጣኖች በሰነዱ ውስጥ ይገለጻሉ።<br>ወኪሉ ውሳኔዎችን መሻር አይችልም። |
| የጤና እንክብካቤ የውክልና ስልጣን | ከዘላቂ የውክልና ስልጣን ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም የጤና እንክብካቤ ላይ ብቻ ያተኮረ ነው።<br>ትክክለኛውን ወኪል መምረጡ በጣም አስፈላጊ ነው፤ የግለሰቡን ምኞቶች፣ እሴቶችና ምርጫዎች ማወቁንና ጠንካራ ተሟጋች እንደሚሆንለት ያረጋግጡ | ወካዩ ግለሰብ ችሎታ በሚያጣበት ወቅት አንድ ሰው ማናቸውንም ወይም ሁሉንም የጤና እንክብካቤ ውሳኔዎች እንዲወስን ያስችለዋል።<br>ዶክተር እና ቤተሰብ የግለሰቡን ፍላጎቶች ሊያውቁና ሊያከብሩ ይችላሉ |
| ተወካይ ተከፋይ | አንድን ሰው በመወከል ከመንግስት የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞችን ይቀበልለታል፤ ጥቅማ ጥቅሙን ለተጠቃሚው የኑሮ ወጪዎች የመጠቀም ኃላፊነት አለበት | ግለሰቡ ፋይናንሱን ለማስተዳደር የማይችል መሆን አለበት።<br>ተወካይ ተከፋይ በየዓመቱ ለማሕበራዊ ዋስትና አስተዳደር ሪፖርት ማድረግ አለበት |
| የተገደበ የንብረት ተቆጣጣሪነት | በዳኛው በሚገለጸው መሰረት የአገልግሎት ክፍያ መክፈል ወይም የታክስ ተመላሽ ማስገባት የመሳሰሉ የተወሰኑ የፋይናንስ ጉዳዮችን የተመለከቱ ውሳኔዎች። የንብረት ተቆጣጣሪው የዋስትና ቦንድ ማስያዝ አለበት። | ግለሰቡ ችሎታ ያጣ መሆን አለበት።<br>የንብረት ተቆጣጣሪው በገቢ እና ወጪዎች ላይ ሪፖርት ማድረግ አለበት |
| ሙሉ የንብረት ተቆጣጣሪነት | የአገልግሎት ክፍያ መክፈል፣ ገንዘብ ኢንቨስት ማድረግና ንብረት መሸጥን ጨምሮ ሁሉንም የፋይናንስ ነክ ውሳኔዎች። የንብረት ተቆጣጣሪው የዋስትና ቦንድ ማስያዝ አለበት። | የንብረት ተቆጣጣሪው ሁሉንም የፋይናንስ ግብይቶች በተመለከተ ዓመታዊ ሪፖርት ማቅረብ አለበት |
| ተጠባባቂ ሞግዚት | አሁን የተሾመው ሞግዚት ሲሞት ሞግዚት እንዲሆን በሞግዚትነት ትእዛዝ ውስጥ የተሰየመ ሰው | ተቀዳሚው ሞግዚት እስከሚሞት ድረስ ምንም ዓይነት ኃላፊነት አይኖረውም |
| የተገደበ ሞግዚትነት | በዳኛው በሚወሰነው መሰረት በውስን ጉዳዮች (ለምሳሌ የጤና እንክብካቤ ብቻ) ላይ ውሳኔ ለመወሰን። ይህም ግለሰቡ ሌሎች ውሳኔዎችን በሙሉ እንዲወስን ነጻ ያደርገዋል። | ግለሰቡ ችሎታውን ያጣ መሆን አለበት።<br>ሞግዚት ለማሕበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ ዓመታዊ ሪፖርት ማቅረብ አለበት |
| ሙሉ ሞግዚትነት | ሞግዚት ሁሉንም የፋይናንስ፣ የሕግ፣ የግል እንክብካቤና ማሕበራዊ ውሳኔዎችን ይወስናል | ግለሰቡ ችሎታውን ያጣ መሆን አለበት።<br>ሞግዚት ለማሕበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ ዓመታዊ ሪፖርት ማቅረብ አለበት |

## ቅጥያ 7፡ ከት/ቤት ተኮር የሽግግር አገልግሎቶች ጋር መስራት

ሶስቱም የአካባቢ መስተዳድሮች ከት/ቤት ስርዓት ወጥተው ወደ ጎልማሶች አለም ለሚቀላቀሉ ተማሪዎች የሽግግርና የስራ ቅጥር አገልግሎቶችን ያቀርባሉ። ተማሪዎ በሚማርበት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የሚገኙት የሽግግር አስተባባሪ የሽግግር ሒደቱ እንዴት እየሄደ ስለመሆኑ ጠይቀው ለት/ቤት አቀፍ እና ለሕዝባዊ የሙያ ፕሮግራሞች ያላቸውን ምክረ ሃሳቦች ያግኙ።

የአካባቢ አስተዳደሮች በሽግግር ላይ ላሉ ተማሪዎች በሚሰጧቸው አገልግሎቶች ይለያያሉ። የት/ቤትዎ ስርዓት ከሚከተሉት አገልግሎቶች መካከል የሚያቀርበው መኖሩን ይጠይቁ፡

**ተግባራዊ የኑሮ ክህሎቶች**ፕሮግራሞች የስራ ዘመን/ቴክኒካዊ ውህደት፣ ማህበራዊ ብቃት፣ የማህበረሰብ ቅንጅት፣ ግለሰባዊ ዕድገት፣ ጤናና አካል ብቃት፣ የቤት ውስጥ አኗኗር፣ እና ተግባራዊ የአካዳሚክ ክህሎቶችን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ የክህሎት ማሳደጊያ ተግባራትን ያከናውናሉ።

**የስራ ስልጠና አገልግሎቶች**ራሱን ለቻለ የስራ ቅጥር የስራ ዝግጁነት ክህሎቶችን ለሚያሳዩና ልዩና የአጭር ጊዜ ድጋፍና ስልጠና ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች።

**ት/ቤት ተኮር የስራ ዘመን ምዘናዎች**ተማሪዎች የዳሰሳ ወይም የስልጠና መስኮችን እንዲመርጡ ለማገዝ ቀለል ያሉ የስራ ዘመን ፍላጎቶችና የተፈጥሯዊ ባህርይ ግምገማን ያቀርባሉ።

**ግለሰባዊ የስራ ዘመን ምዘናዎች**፣ የተማሪውን ፍላጎቶች፣ የተፈጥሮ ባህርይ፣ የተቀጣሪነት ባህርያትና የስራ ዘመን ውሳኔ አሰጣጥ ክህሎቶችን ሁሉን አቀፍ ምስል ለማዘጋጀት የታሰቡ ግለሰባዊ የፍላጎት ቆጠራዎችን፣ ደረጃቸውን የጠበቁ ፈተናዎችና የዳሰሳ ተግባራትን ያካትታሉ።

**የአሌክሳንድሪያ ከተማ**
**የሽግግር አስተባባሪዎች**
ከ T.C. Williams High School, 3330 King Street, Alexandria ውጭ የሰፈሩ

Ameeta Shah, Employment Specialist,
Project SEARCH (703) 504-3687
ameeta.shah@acps.k12.va.us

Jim Cooney, Employment Support Specialist
703-824-6800 ext.6892
James.cooney@acps.k12.va.us

Angela Brown, Employment Support Specialist
(703) 824-6800, ext. 6254
angela.brown@acps.k12.va.us

**Project Search**
www.projectsearch.us/Home.aspx
በአካባቢ ደረጃ፣ Project SEARCH በ Inova Alexandria Hospital ውስጥ ፕሮግራም ያካሂዳል። ይህ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሽግግር ፕሮግራም አንድ ዓመት የሚፈጅ ከት/ቤት ወደ ስራ የሚያደርስና ሙሉ በሙሉ በስራ ቦታ ላይ የሚካሄድ ነው። ሙሉ በሙሉ ወደ ስራ ቦታ መግባት የክፍል ውስጥ ትምህርትን፣ የስራ ዘመን ዳሰሳንና ተዛማጅ የስራ ክህሎቶች ስልጠናን ያቀላጥፋል።

በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ ስላሉት የሽግግር አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ይህ ይጎብኙ፡
http://www.acps.k12.va.us/curriculum/special-education/transition/

**አርሊንግተን ካውንቲ**
**የሽግግር አስተባባሪዎች**
Joy Haley, Yorktown HS
(703)228-2545 joy.haley@apsva.us

Christina Eagle, Arlington Career Center (703)228-5738
Christinaeagle@apsva.us

Thomas Sweet, Washington-Liberty
(703)228-6265
thomas.sweet@apsva.us

Jennifer DeCamp, Wakefield HS
703-228-6728
Jennifer.decamp@apsva.us

Joyce Kelly, Stratford Program
703-228-6450
joyce.kelly@apsva.us

Brian Stapleton, Contract Services
703-228-6360
Brian.stapleton@apsva.us

**ለስራ ቅጥር ዝግጁነት ፕሮግራም (PEP)**
በ Arlington Career Center ውስጥ የሚገኝ የሽግግር ፕሮግራም ነው። የ PEP ዕድሎች የተመሰረቱት አሁን ባሉት የንግድ ስራ አዝማሚያዎችና ፍላጎቶች ላይ ሲሆን ይህም ዘላቂና ትርጉም ያለው የስራ ቅጥር ለማግኘትና ለማስቀጠል አስፈላጊ የሆኑ ማሕበራዊ ክህሎቶችን ጨምሮ ተማሪዎች አሁን ባለው ገበያ ውስጥ ስራ ለማግኘት የሚያስፈልጋቸውን ተዛማጅ ክህሎት እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል። ፕሮግራሙ የተቀረጸው ተማሪዎች የኢንተርንሺፕ/የስራ ላይ ልምምድ ተሞክሮ እንዲያገኙ ታስቦ ሲሆን ከምረቃ በኋላ በቀጥታ የንግድ ማረጋገጫ፣ ፈቃድ፣ የኮሌጅ ክሬዲት፣ የኔትወርክ ትስስር፣ እና/ወይም የስራ ዕድል ሊያስገኙላቸው ይችላል።

PEP ዓላማው የተማሪዎችን የስራ ዝግጁነት ክህሎቶች በመጨመር በጎልማሳነታቸው ወቅት ስራ የሚያገኙበትና ይዘው የሚቆዩበትን ዕድል ለማሳደግ ነው።

በተማሪው ፍላጎቶች መሰረት፣ የስራ ልምድ ሙሉ በሙሉ ድጋፍ ከሚደረግለት የካምፓስ ፕሮግራም አንስቶ ሙሉ በሙሉ ራሱን እስከቻለ በአካባቢ የንግድ ስራ ላይ እስከሚገኝ የስራ ልምድ ይደርሳል። የተወሰኑ ተማሪዎች ከስራ ቦታ ልምዶቻቸው ጎን ለጎን በ Career Technical Education (CTE) ኮርሶች ውስጥ ይሳተፋሉ። የ PEP መምህራንና አስተዳዳሪዎች ከ DARS እና Arlington County IDDS የኬዝ ሃላፊዎች ጋር በመተባበር ወደ ጉልምስና የሚደረገውን ሽግግር ይደግፋሉ።

ዕድሜያቸው ከ18-21 የሆኑና IEP ያላቸው የአርሊንግተን ተማሪዎች ለ PEP ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሽግግር አስተባባሪዎን ያነጋግሩ ወይም ለ Christina Eagle ኢሜይል ያድርጉ Christinaeagle@apsva.us

በአርሊንግተን ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች ውስጥ ስላሉ የሽግግር አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ: http://www.apsva.us/transition-services/

**ፌርፋክስ ካውንቲ**
**የሽግግር አስተባባሪዎች**
Career & Transition Services, 571-423-4150
Janelle Ellis, Coordinator
ፌርፋክስ በእያንዳንዱ 29 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትና ማዕከል ውስጥ የስራ ቅጥርና የሽግግር ተወካዮች (ETRs) አሉት። ስለእነዚህ አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ: https://www.fcps.edu/academics/academic-overview/special-education-instruction/career-and-transition-services

ከ FCPS ጋር ኮንትራት ወዳላቸው የግል ት/ቤቶች ለተመደቡ ተማሪዎች Multi Agency Services https://www.fcps.edu/node/32709 ያነጋግሩ። Adam Cahuantzi, Program Manager agcahuantzi@fcps.edu 571-423-4030.

ETRs ተማሪው ት/ቤት ውስጥ እያለ የሽግግርና የስራ ቅጥር አገልግሎቶችን በማቅረብ ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ የሚኖራቸውን ሽግግር ያመቻቻሉ። የስራ ቅጥር አገልግሎቶች በውስጣቸው የስራ ፍለጋ ክህሎቶች፣ የስራ ማጎልበቻ እና የስራ ምደባ፣ የስራ አያያዝና ስራ ተኮር ትምህርቶችን ያካትታሉ። የሽግግር አገልግሎቶች ስለ ድሕረ ሁለተኛ ደረጃ አማራጮችና የመረጃ ምንጮች መረጃ መጋራት፣ ወደ ት/ቤት ተኮር አገልግሎቶች ማስተላለፍ፣ ለተማሪዎች በመጨረሻ የት/ቤት ቆይታቸው ድጋፍ ማድረግና በሚመረቁበት ጊዜ ወደ ጎልማሳ አገልግሎት ኤጀንሲዎች ማስተላለፍን ያካትታሉ።

የስራ ዘመንና የሽግግር አገልግሎቶችም እንደዚሁ የስራ ዘመንና የኮሌጅ ዝግጁነትና ለማጎልበት የተለያዩ አገልግሎቶችና ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን ያቀርባሉ። እነዚህም የሚያካትቱት የስራ ዘመን ምዘና፣ የስራ ግንዛቤ እና ሽግግር(WAT) ትምህርት፣ ትምህርት ለስራ (EFE) ክላስ፣ በቢሮ ውስጥ ትምህርት ለስራ (EFEO)፣ የስራ ስልጠና፣ እና የአካዳሚ ድጋፍን ነው።

እስከ 22 ዓመታቸው ድረስ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ለሚፈልጉ ተማሪዎች፣ የስራ ዘመንና የሽግግር አገልግሎቶች በተቀጣሪነትና በኑሮ ክህሎቶች ላይ ያተኮሩ የተለያዩ ፕሮግራሞችን የሚያቀርብ ሲሆን እነርሱም በ ሻንቲሊ (Chantilly)፣ ሳውዝ ሌክስ (South Lakes)፣ ማርሻል (Marshall)፣ እና ማውንት ቬርነን (Mount Vernon) ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚሰጡት የ Davis and Pulley Career Centers እና Secondary Transition to Employment Programs (STEP) እና Transition to Independence (TIP) ይገኙበታል። TIP በ Davis ወይም Pulley Centers ውስጥ ለተመዘገቡ ተማሪዎች በ Northern Virginia Community College የ Annandale እና Alexandria ካምፓሶች ውስጥ ለስራ የመቀጠር ክህሎቶችን የሚያሳድግ ስልጠና ይሰጣል።

***የመረጃ ምንጮች***
የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሽግግር አስተባባሪዎችም ዓመቱን በሙሉ በሚካሄዱትና ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ዝግጅቶች ላይ ተጨማሪ መረጃ ሊሰጧችሁ ይችላሉ።

***የአገልግሎት ሰጪ የመረጃ መስጫ ትርኢቶች***—ፌርፋክስ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች እና የአርሊንግተን የሕዝብ ት/ቤቶች በበልግ ወቅት ዓመታዊ የመረጃ መስጫ ትርኢቶች የሚያዘጋጁ ሲሆን ይህም የጎልማሶች አገልግሎቶችን በተመለከተ መረጃ ለሚፈልጉ ተማሪዎች ነው።

**Flash Forward** – የድሕረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትና የስራ ቅጥር አማራጮች። በየዓመቱ በፀደይ ወቅት የሚካሄድ ሲሆን አዘጋጁም FCPS ነው። ይህ ዝግጅት የአገልግሎት አቅራቢዎችን ትርዒትና ወርክሾፕ ያካትታል።

**Super Transition Saturday** በየዓመቱ በክረምት ወቅት የሚካሄድ ሲሆን አዘጋጁም FCPS ነው። ይህ ዝግጅት የአንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ለሽግግር በሚዘጋጁበት ወቅት መረጃ የሚሰጥ ነው።

**Future Quest** (George Mason Univ.) ለመለስተኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የሚዘጋጅ የኮሌጅና የስራ ዘመንን የሚመለከት ዝግጅት ሲሆን በየሁለት ዓመት ይዘጋጃል፤ ቀጣዩ ኦክቶበር 2019 ላይ ይካሄዳል።

**የወላጆች የመረጃ መስጫ ማዕከላት፡**
**Alexandria City PRC**
https://www.acps.k12.va.us/Page/397
Special Education Family Resource Center
TC Williams HS, 3801 West Braddock Rd, Alexandria, VA (703)824-0129

**Arlington Public Schools PRC**
https://www.apsva.us/special-education/parent-resource-center/
2110 Washington Boulevard, Suite 158, Arlington, VA 22204 (703) 228-7239

**Fairfax County Public Schools PRC**
https://www.fcps.edu/resources/family-engagement/parent-resource-center
Dunn Loring Center for Parent Services
2334 Gallows Road, Rm 105, Dunn Loring, VA 22027
(703)204-3941 prc@fcps.edu

## Wilson Workforce and Rehabilitation Center (WWRC)

ከአካባቢው የት/ቤት ስርዓቶች በተጨማሪ፣ የ Commonwealth of Virginia (ቨርጂኒያ የጋራ ብልጽግና) በሽግግር ላይ ያሉ ተማሪዎችን በ Wilson Workforce and Rehabilitation Center (WWRC፣ ዊልሰን የሰራተኛ ሐይል እና የተሐድሶ ማዕከል) በኩል የሚያግዙ ፕሮግራሞችን ያቀርባል፡

***Post-Secondary Education Rehabilitation and Transition Program (PERT፣ ድሕረ 2ኛ ደረጃ ትምህርት የተሐድሶና የሽግግር ፕሮግራም)***

የ PERT ፕሮግራም አካል ጉዳተኛ ለሆኑ የመንግስት 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ከ5-10 ቀን የሚቆይ የሙያ፣ እና ራስን የመቻል ኑሮ፣ ማህበራዊና የመዝናኛ ክህሎቶች አጠቃላይ ምዘና ያካሂዳል። መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች ዕድሜያቸው 16 ዓመትና ከዚያ በላይ ሆኖ IQ 60 ወይም ጥሩ የሆነ የመላመድ ክህሎቶች ማስረጃ ሊኖራቸው ይገባል፤ ተማሪው ከ PERT ክፍለ ጊዜ በኋላ በበልግ ወቅት ወደ ት/ቤት መመለስ አለበት (በሌላ አነጋገር፣ በመጨረሻ የትምህርት ዓመት ላይ መሆን የለብዎትም)።

PERT የሚከተሉትን ያቀርባል፡

- የኑሮ ክህሎቶች ምዘና
- የሙያ ምዘና
- የቴራፒ ምዘና
- የሙያ ስልጠና ፕሮግራሞች

ለ PERT ለማመልከት፣ በ2ኛ ደረጃ ት/ቤትዎ የሚገኙትን የሽግግር አስተባባሪ ያነጋግሩ። ማመልከቻዎ ተቀባይነት የሚኖረው ከ Department for Aging and Rehabilitative Services (DARS) ጋር የተከፈተ ጉዳይ ካለዎት ነው። ስለ PERT ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ http://wwrc.virginia.gov/PERT.htm ይጎብኙ።

## ቅጥያ 8፡ የኢንተርንሺፕ ፕሮግራሞችና የሽግግር ድጋፎችን መፈተሽ

## የኢንተርንሺፕ ፕሮግራሞች

**John Hudson Internship Program (ጆን ሃድሰን የኢንተርንሺፕ ፕሮግራም)**
ይህ ለአካል ጉዳተኛ የኮሌጅ ተማሪዎችና የቅርብ ጊዜ ተመራቂዎች በፌርፋክስ ካውንቲ መንግስት የሚዘጋጅ የበጋ ወቅት የኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ነው
(703) 324-5421 ወይም
https://www.fairfaxcounty.gov/familyservices/disabilities/john-hudson-internship

**Educating Youth through Employment (EYE)**
ይህ ፕሮግራም በበጋ ወቅት የሚዘጋጅ ሲሆን በጋራ የሚያዘጋጁትም SkillSource እና የፌርፋክስ ካውንቲ የቤተሰብ አገልግሎቶች መምሪያ ናቸው። ፕሮግራሙ ዕድሜያቸው ከ18-24 የሚሆኑ ወጣቶችን መልምሎ፣ የሚያጣራ ሲሆን በግሉ ዘርፍና በሌሎች የንግድ ስራ መስኮች ከሚፈጠሩ ፕሮፌሽናል ዕድሎች ጋር ያገናኛቸዋል።
http://www.myskillsource.org/page/id/42/eye-program

## የሽግግር ድጋፎችን የሚሰጡ ድርጅቶች

### Adult and Community Education (ACE፣ የጎልማሶችና የማህበረሰብ ትምህርት)

ACE የፌርፋክስ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች በሁሉም ዕድሜ ላይ ላሉ ሰዎች ያዘጋጀው ፕሮግራም ሲሆን በስራ ዘመን እና ለስራ ዝግጁነት ላይ አጽንኦት ይሰጣል። በስራ ላይ ልምምድ፣ የሰርትፊኬት ፕሮግራሞች፣ ቢዝነስ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ጤና እና ሜዲካል እና የንግድና የኢንዱስትሪ ፕሮግራሞች ላይ የተለያዩ የስልጠና ዕድሎችን ይሰጣል። ለተጨማሪ መረጃ፣ ይህን ይጎብኙ:
https://aceclasses.fcps.edu/PolicyDetails.aspx?StaticPage=About%20U

**STEMSkills**
www.stemskills.org
ፈጠራዊና በቴክኖሎጂ በታገዙ ኢንዱስትሪዎች ላንት ያላቸው ውስጥ ለመስራት አካል ጉዳተኛ ወጣቶች ላይ ትኩረት ያደርጋል። በኑሮ ስልጠና፣ ስራ አፈላለግ፣ ስራ መዳሰስ፣ የስራ ላይ ልምምድና ብጁ የስራ ቅጥር ላይ ያተኮሩ አገልግሎቶችን ይሰጣል። STEMSkills ኦቲዝም፣ ADHD እና LD ላለባቸው ወጣቶች የስራ ባህል ልማዶችን እንዲፈትሹና የማስፈጸም ተግባር ክህሎቶችን እንዲገነቡ የሚያስችል የማህበረሰብ ካምፕም ያቀርባል። በቀጣዩ አድራሻ ከ Eric Duer ጋር ይነጋገሩ
EDuer@stemskills.org። (202)744-2452

**Social Graces, LLC**
www.socialgracellc.com
ለአካል ጉዳተኛ ወጣት ጎልማሶችና ለቤተሰቦቻቸው ድጋፍ ያቀርባል። ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል ጥብቅና እንደዚሁም ማህበራዊ ክህሎቶች፣ የማስፈጸም ተግባርና በት/ቤት፣ በስራ እና በተጨባጭ ዓለም ውስጥ ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጉ ክህሎቶች ላይ ኢላማ ያደረጉ፣ ግለሰባዊ ድጋፍና ፕሮግራሞች ይገኙበታል። የበጋ ካምፖችንም ያቀርባል። በቀጣዩ አድራሻ ከ Ginny Conroy ጋር ይገናኙ
info@socialgrace.llc (703)593-9224

**የመጪው ዘመን የሽግግር ምክር አግልግሎት (Next Level Transition Consulting)**
ለሽግግር አገልግሎቶች፣ ለስራ ዘመን ፍተሻ፣ ለስራ ዘመን ዕቅድ አወጣጥና ለስራ ስልጠና እና ራሱን ለቻለ የኑሮ ድጋፍ ይሰጣል። የግል ክፍያ ይቀበላል፣ ከ DARS የገንዘብ ድጋፍ ያገኛል።
www.nextleveltransition.com Contact: Scott Wilbur, Transition Director (571)332-2992
scottwilbur@nextleveltranstion.com

### Starfish Savers

ከሚያቀርባቸው አገልግሎቶች መካከል ምክክርና ጥብቅና፣ ስልጠና እና የኑሮ ክህሎቶችና ማህበረሰብ አቀፍ የሽግግር ስልጠና ይገኙበታል። የግል ክፍያ ይቀበላል፣ ከ DARS የገንዘብ ድጋፍ ያገኛል።
www.starfishsavers.com
የግንኙነት ተጠሪ፡ Larrie Ellen Randall (703) 631-9551
Larrie.Ellen@starfishsavers.com

**Inclusion Consultants**
በሚከተሉት አገልግሎቶች አማካይነት ግለሰቦች አስደሳችና አካታች ሕይወትን እንዲገነቡና እንዲኖሩ የሚያስችሏቸውን መሳሪያዎች ያቀርባል፡ መምከር፣ ማሰልጠን፣ ማመከርና ማስተሳሰር።
አገልግሎቶቻቸው በሁሉም የሕይወት ደረጃና በማህበረሰቦች ውስጥ አካታች አሰራሮችን ለመተግበር ይፈልጋሉ።
www.inclusionconsultants.com
ከ Nancy Mercer ጋር ይነጋገሩ (703)304-8537
nancy@inclusionconsultants.com

## ድሕረ 2ኛ ደረጃ የሽግግር ፕሮግራሞች

**MOST ፕሮግራም**
ትርጉም ያላቸው ዕድሎች ለስኬታማ ሽግግሮች [Meaningful Opportunities for Successful Transitions (MOST)] ተግባራትና ስልጠናን ያካተተ የአንድ ዓመት ግለሰባዊ ፕሮግራም ሲሆን ወደ ጎልማሳ ማህበረሰብ ስኬታማ ሽግግርን ለማመቻቸት የተቀረጸ ነው። ፕሮግራሙ በሶስት ማዕቀፎች ውስጥ የተሳታፊዎችን ውጤቶች ማመቻቸት ላይ ያተኩራል፡

- ራስን መቻል - ራስን ማገዝ፣ ራስን ችሎ መኖርና የደህንነት ክህሎቶችን ይጨምራል።
- ማህበረሰብ - ማህበራዊ ክህሎቶች፣ ትራንስፖርትና መዝናኛን ይጨምራል።

- ሙያ - የስራ ቅጥር፣ ትምህርት፣ የሙያ ስልጠና እና የትስስር መፍጠርን ጨምሮ።

MOST CSB እና የ Waiver የገንዘብ ድጋፍ ይቀበላል። ለተጨማሪ መረጃ፣ http://www.jfgh.org/services/services/ Marcie Bennett, MOST ፕሮገራመ አስተዳዳሪን ያነጋግሩ 240-283-6031 MBennett@JFGH.org

## ቅጥያ 9፡ ድሕረ 2ኛ ደረጃ ትምህርት የመረጃ ምንጮችና የትምህርት ድጋፎችን መዳሰስ

### ለኮሌጅ ሕይወት መዘጋጀት

**Adaptive College Experience (ACE)**
www.neuroscience-inc.com/adaptive-college-experience/
የ ACE ፕሮግራም በወር ሁለት ጊዜ የሚደረጉ የቡድን ክፍለ ጊዜያትን የሚያካትት ሲሆን ዓላማውም የሚሸጋገሩ ተማሪዎችን ወይም በኮሌጅ ውስጥ የሚማሩና ASD፣ ADHD ወይም የመረበሽ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ለኮሌጅ ማዕቀፍ በሚሆኑ ተላማጅ ክህሎቶች መስክ ለመደገፍ ነው፤ በዚህም ውስጥ ድርጅታዊ፣ ግለ ቁጥጥር እና ማህበራዊ ክህሎቶችን ይጨምራል። ከ Dr. Sajjad Khan ጋር ይነጋገሩ 703-787-9090

**The Faison Center**
https://www.faisoncenter.org/college-101-program Ready. Set. Go! የተባለ የበጋ ኮሌጅ 101 ፕሮግራም የሚያቀርብ ሲሆን ፕሮግራሙ የተቀረጸውም የመጨረሻ ዓመት የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎችን ስለ ኮሌጅ ልምድ እንዲያዳብሩ ዕድል መስጠት ነው። ፕሮግራሙ በ University of Richmond ካምፓስ ውስጥ የሁለት ሳምንት የምሽት የኮሌጅ ተሞክሮን ያቀርባል።
(804)612-1947

**Strive Program at NVCC Annandale**
የ STRIVE ፕሮግራም የመማር ውስንነት ላለባቸው ወጣት ጎልማሶች ከት/ቤት ወደ ድሕረ 2ኛ ደረጃ ስልጠና፣ ወደ ስራ ቅጥርና ስኬታማ የማህበረሰብ አኗኗር የሚሸጋገሩባቸውን ዕድሎች ይሰጣል።
ከ Richard Stone ጋር ይነጋገሩ strive05@icloud.com
571-212-4482

### ዲግሪ የማያስገኙ የኮሌጅ ተሞክሮዎች

**Mason LIFE Program**
የአእምሮና የዕድገት አካል ጉዳት ኖሮባቸው ድጋፍ በሚሰጠው የአካዳሚክ አካባቢ ውስጥ የዩኒቨርሲቲ ተሞክሮ እንዲኖራቸው ለሚፈልጉ ወጣት ጎልማሶች የተዘጋጀ ድሕረ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ነው።
https://masonlife.gmu.edu/
ፕሮግራም ዳይሬክተር፡ Heidi J. Graff, Ph.D.
(703)993-3905

**VCU's ACE-IT in College Program**
ACE-IT in College የአእምሮ አካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች የሚሆን አካታች የኮሌጅ ተሞክሮ ነው። ተማሪዎች የትምህርት ክፍሎችን በመቁጠር ከስራ አሰልጣኝ በሚያገኙት ድጋፍ የተለያዩ የካምፓስ ተግባራት፣ የስራ ልምዶችና ተግባራት ውስጥ ይሳተፋሉ። የመጨረሻ ግቡም ተማሪው ፍላጎት በሚያሳድርባቸው መስኮች ተወዳዳሪ የሆነ የስራ ቅጥር ማግኘት ነው።
www.aceitincollege.org

### የኮሌጅ ፕሮግራሞች

**Mason Autism Support Initiative (MASI)**
ሁሉን አቀፍና በክፍያ ላይ የተመሰረተ ፕሮግራም ሲሆን ከተለመዱት የትምህርት ሁኔታዎች ባለፈ ለተማሪዎች በ Autism Spectrum ላይ ተጨማሪና ጥልቀት ያለው የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል። ተማሪዎች በአቻ ለአቻ የሚሰጥ ስልጠና፣ የትምህርት ስትራቴጂስት፣ የክህሎት ግንባታ ትምህርቶችና ወርሐዊ ማህበራዊ ዝግጅቶችን ማግኘት ይችላሉ።
https://ds.gmu.edu/mason-autism-support-initiative/
(703)993-2474

**Northern Virginia Community College**
የአካል ጉዳተኝነት አገልግሎቶች ዳይሬክተር
https://www.nvcc.edu/disability-services

**College Steps**
ለአገልግሎት ክፍያ የሚያስከፍል ፕሮግራም ሲሆን ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ልዩ ግብዓቶችና ድጋፎችን በሚሰጡት የ Annandale፣ Alexandria እና የ Loudon NOVA ካምፓሶች ውስጥ ይሰጣል። ፕሮግራሙ ከ NOVA ጋር በመተባበር ዕድሜያቸው ከ17-26 የሆኑ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን በአቻ ለአቻ ስልጠና እና በካምፓስ ውስጥ የድጋፍ አገልግሎቶች አማካይነት ለኮሌጅ ሕይወታቸው ድጋፍ ያደርጋል። ለአገልግሎት ሞዴል ሰዓታዊ ክፍያ ያስከፍላል።
www.collegesteps.org 1-888-732-1022 ወይም
contactus@collegesteps.org

**College Living Experience**
የተለያዩ አካል ጉዳቶች ላሉባቸው ወጣት ጎልማሶች ድሕረ 2ኛ ደረጃ ድጋፎችን ያደርጋል።
www.experiencecle.com
Montgomery College, 401 North Washington Street, Suite 420 Rockville, MD

CLE ወደ መጨረሻ ዓመታቸው ለሚገቡ ወይም በቅርቡ ለተመረቁ የተለያዩ ተማሪዎች የ 3 ሳምንት የበጋ ፕሮግራም ያቀርባል። http://experiencecle.com/summer-program-2/

**College Internship Program (CIP)**
www.cipworldwide.org 703-323-3000
በኦቲዝም ስፔክትረም ውስጥ ላሉና የመማር ልዩነቶች ላላቸው ወጣት ጎልማሶች ሁሉን አቀፍ ድሕረ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ድጋፍ መስጫ ፕሮግራም ነው።

**Bass Educational Services, LLC**
የመማር ልዩነቶች ላሉባቸው ቤተሰቦችና ተማሪዎች ትምህርታዊ የማማከር አገልግሎት ይሰጣል።
8304 Old Courthouse Road, Suite B, Vienna, VA
703-462-0654
www.basseducationalservices.com

## ድሕረ ሁለተኛ ደረጃ የኦንላይን መረጃ ምንጮች

www.heath.gwu.edu ለአካል ጉዳተኞች በድሕረ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ላይ የሚሰራ ኦንላይን clearinghouse

www.thinkcollege.net የአእምሮ አካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች የኮሌጅ ፕሮግራሞችን ለማፈላለግ የሚያገለግል ኦንላይን የመረጃ ቋት።

www.bestcolleges.com/resources/disabled-students/
ለአካል ጉዳተኞች የኮሌጅ የመረጃ ምንጮችን አጠቃላይ ዕይታ ያቀርባል።

**2ኛ ደረጃ ት/ቤት ከኮሌጅ ጋር ሲነጻጸር**
**Individuals with Disabilities Education Improvement Act (የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ማሻሻያ ሕግ)**
**እና Americans with Disabilities Act (የአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ሕግ)**

| 2ኛ ደረጃ ት/ቤት (IDEIA) | ኮሌጅ (ADA) |
|---|---|
| IEP ሁሉንም መስተንግዶዎችና አገልግሎቶች ይመራል፣ መምህራንንና አማካሪዎችን ያካትታል፣ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ተማሪዎች ምንጊዜም የወላጅ ፊርማን ይጠይቃል። | ትምህርታዊ ዕቅድ የሌለ ሲሆን፣ መምህራንንም በተማሪው ካልሆነ ማነጋገር አይቻልም። አብዛኛውን ጊዜ፣ ወላጆች የተማሪውን የፈተና ውጤት መቀበል የሚችሉት ከተማሪው በጽሑፍ የተሰጠ ፈቃድ ሲኖር ነው። |
| ተማሪው ለመንግስት ትምህርት ብቁ የሆነው በትክክለኛው ዕድሜ ላይ ስለሚገኝና የአካል ጉዳት ስላለበት ነው። | በሌላ መልኩ ብቁ የሆነማለት ተማሪው መስተንግዶ የሚያኝም ሆነ አልሆነ ሁሉንም የመግቢያና የአካዳሚክ መስፈርቶች ማሟላት አለበት ማለት ነው። |
| በ IDEA አሰራር መሰረት፣ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች "ነጻ እና አግባብነት ያለው የመንግስት ትምህርት" የማግኘት መብት አላቸው። | ተማሪዎች ከፍተኛ ትምህርትን በእኩልነት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ማስከበር የሚገባቸው የሲቪል መብቶች አሏቸው። ሁሉንም ነገር የማግኘት መብት ያለው ሰው የለም። |
| የመንግስት ት/ቤቶች የተማሪውን የአካል ጉዳቶች በአግባቡ የመመዘን ኃላፊነት አለባቸው። | ኮሌጆች ተማሪዎችን መመዘን ባይጠበቅባቸውም፣ ባሉት መመሪያዎች መሰረት ተማሪዎች አካል ጉዳተኝነታቸውን እንዲያስረዱ መጠበቅ ይችላሉ። |
| የተማሪ ምደባ የሚወሰነው በተማሪው የ IEP ቡድን ነው። ምደባው ገዳቢነቱ አነስተኛና ለተማሪው ተገቢ በሆነ አካባቢ ሊሆን ይገባል። | ተማሪዎች ከኮሌጅ ማህበረሰብ ጋር ይዋሃዳሉ፣ አካባቢውም በመስተንግዶ አማካይነት ይስተካከላል። ኮሌጆች አካባቢን በቅድሚያ ለመምረጥ ምክክር አያካሂዱም። |
| የአንድ ተማሪ የአካል ጉዳቶች እና ፍላጎቶች በ IEP ውስጥ ይሰነዳሉ። ይህ መረጃ ከተማሪው ጋር ለሚሰሩ ሰራተኞች ዝግጁ ይደረጋል። | ማወቅ ያለብዎ፡ ተማሪዎች ስለ አካል ጉዳቶቻቸው እንዲገለጽላቸው ለኮሌጅ ፕሮፌሰሮች ግልጽ ፈቃድ መስጠት አለባቸው። ተማሪዎች መስተንግዶ ከማግኘት ጋር የተያያዙ እርምጃዎችን በሙሉ ለእያንዳንዱ ኮርስና ለእያንዳንዱ ሴሚስተር ከእያንዳንዱ ፕሮፌሰር ጋር ማስጀመር አለባቸው። ተማሪዎች የማይፈልጉትን ወይም የማያስፈልጋቸውን መስተንግዶ ያለመቀበል የሲቪል መብት አላቸው። |
| ምዘና፣ አካላዊ ወይም ሙያዊ ቴራፒ፣ የንግግርና የቋንቋ አገልግሎቶች፣ የግል እንክብካቤ እና/ወይም ሌላ ማንኛውም ቴራፒ በት/ቤቱ የሚቀርብ ሲሆን ይህም በተማሪው የትምህርት ዕቅድ ላይ የሚገለጽ ይሆናል። | የኮሌጅ ተማሪዎች ልክ ራሳቸውን ችለው እንደሚማሩና ኮሌጅ ውስጥ እንዳልሆኑ ሁሉ ለየትኛውም እና ለሁሉም የግል አገልግሎቶች ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፣ እነርሱም የግል ወይም የሕክምና እንክብካቤ የመሳሰሉት ናቸው። |
| በትምህርት ዕቅዱ ውስጥ አስፈላጊነቱ ከተገለጸ፣ አንድ ተማሪ ዘና ብሎ የሚሰራቸው የሒሳብ ፈተናዎች ሊሰጡት ይችላሉ። | ዘና ተብለው የሚሰሩ የሒሳብ ፈተናዎች ምክንያታዊ ተደርገው አይቆጠሩም። የጊዜ ማራዘሚያዎች ምክንያታዊ ሊሆኑ ይችላሉ (በተለምዶ አንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን ከእጥፍ ሰዓት ግን አይበልጥም)። |

## ቅጥያ 10፡ ለቅጥር ስራ መዘጋጀትና ከ DARS ጋር መስራት

ለስራ ወይም ለስራ ዘመን ምን ማድረግ እንደሚገባ ማወቁ የማንኛውም ወጣት ጎልማሳ ፈተና ነው። ልጅዎ በተሻለ ሁኔታ ሊሰራው የሚችለውን (ወይም ሊሰራው *የማይፈልገውን*) ስራ አስቀድሞ የሚያውቅ ቢሆንም፣ አብዛኞቹ ወጣት ጎልማሶች ለስራ መዘጋጀትና ስራ ማግኘት ምን እንደሚጠይቅ ብዙም ግንዛቤ የላቸውም።

ሁሉንም ለማወቅ ደግሞ ጊዜ ይጠይቃል። ወላጆችና ተማሪዎች እነዚህን አምስት እርምጃዎች ሊወስዱና ከመለስተኛና 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ጀምሮ ስለ ስራ እና ስራ ነክ ክህሎቶች ማሰብ መጀመር አለባቸው። የአካል ጉዳተኞችን የስራ ቅጥር በተመለከተ ለተጨማሪ መረጃ *Entering the World of Work: A Guide to Employment Programs for Adults with Disabilities in Alexandria, Arlington, Fairfax & Falls Church* የሚለውን ከዚህ ድረ ገጽ ይመልከቱ፡ http://www.thearcofnova.org/programs/transition/transition-points.

**የስራ ዓይነት ልምድ ያግኙ**
ልጅዎ ቀደም ሲል ስለሚሰራው ነገርና ይህም እንዴት የስራ ክህሎቶችን ሊያስተምር እንደሚችል ወይም ወደ ስራ ዘመን ፍላጎት እንዴት ሊሰፋ እንደሚችል በማሰብ ረገድ ፈጣሪ ይሁኑ። አብዛኞቹ ሰዎች ስለ ስራው ዓለም መማር የሚጀምሩት በሚከተሉት ዓይነት ተግባራት አማካይነት ነው፡ የቤት ውስጥ ስራዎች፣ የበጎ ፈቃድ ስራ፣ በቦይ ወይም ገርል ስካውቶች ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት፣ ኢንተርንሺፕ እና እንደ ኮምፒዩተር ጥገና ወይም እንስሳትን መንከባከብ የመሳሰሉ ስራ ነክ ክህሎቶችን በሚያስተምሩ ኮርሶች አማካይነት።

ለበጎ ፈቃደኝነት የስራ ልምዶች፣ የሚከተሉትን ይፈትሹ፡

**Volunteer Match**
www.volunteermatch.org

**Volunteer Alexandria**
ስልክ፡ (703) 836-2176
ድረ ገጽ፡ http://www.volunteeralexandria.org/

**Volunteer Arlington**
ስልክ፡ (703) 228-1760
ድረ ገጽ፡ https://volunteer.leadercenter.org/

**Volunteer Fairfax/Falls Church**
ስልክ፡ (703) 246-3460
ድረ ገጽ፡ http://www.volunteerfairfax.org

**የስራ ፍላጎቶችና ክህሎቶችን መመዘን**
አዎንታዊ የግል ፕሮፋይል በመጠቀም ልጅዎ ለስራ ወይም ለስራ ዘመን ምን ማድረግ እንደሚፈልግ ወይም እንደምትፈልግና ወደ ስራ ቦታ የሚያመጣው ችሎታ፣ መገለጫ ባህርይና ክህሎት ምን እንደሚሆን አጠቃላይ ምስል ይኑርዎት። በተቻለ መጠን፣ በሽግግር ላይ ያለው ልጅዎ በዚህ ጭውውት ውስጥ እንዲሳተፍ ያድርጉ፤ ስለሚወደውና ስለማይወደው ነገር እንደዚሁም ያስፈልገኛል ብሎ ስለሚያስበው እገዛ በታማኝነት የሚናገርበት ቦታ ነው።

ከክህሎቶችና ችሎታዎች ሌላ በስራ ላይ ደስተኛና ስኬታማ ሊያደርጉዎ የሚችሉ ነገሮችን እንዲለዩም ያስችልዎታል፤ ለምሳሌም፡

- የሚመርጡት ስራ ዓይነት፣ ለምሳሌ በርካታ ደንበኛ ጋር የሚያገናኙ አገልግሎት ሰጪ ስራዎች፣ ከሕዝብ ወይም ከስራ ባልደረቦች ጋር አነስተኛ ንክኪ የሚፈጥሩ የማምረቻ ወይም ቁሳቁስ የማንቀሳቀስ ስራዎች።
- የስራ ላይ አካባቢ፣ እርስዎ የሚሰሩበት አካላዊ ቦታ መጠን፣ የሚረብሽ ጩኸት መጠን፣ የቤት ውስጥ ወይም ከቤት ውጭ።
- አለቃዎትና የስራ ባልደረቦችዎ (የቡድን አባል ሆነው የመስራት ወይም ነጻነትዎን ጠብቀው የመስራት ምርጫ)
- የስራ መርሃ ግብርዎ፡ የሙሉ ጊዜ፣ የትርፍ ሰዓት፣ ቅዳሜና እሁድ ወይም በስራ ቀናት፣ በቀን ፈረቃ ወይም በምሽት ፈረቃ፣ ወዘተ…
- መጓጓዣዎ። የጉዞ ጊዜው ምን ያህል ሰዓት እንደሚፈጅና ምን ያህል ወጪ እንደሚያስወጣ ማወቁ የአንድን ስራ ምቹነት ለመመዘን አስፈላጊ ነው።

ፕሮፋይሉ ያላለቀ ስራ መሆን አለበት፤ የበለጠ አካዳሚክ፣ የበጎ ፈቃድ ወይም የክፍያ ስራ ልምድ ባገኙ ቁጥር በየዓመቱ መከለስ እንዳለብዎት ያስቡ።

**አዎንታዊ የግል ፕሮፋይል**

| ህልሞችና ግቦች | ችሎታዎች |
|---|---|
| ክህሎቶችና እውቀት | የመማሪያ ዘይቤዎች |
| ፍላጎቶች | አዎነታዊ የስብዕና መገለጫ ባህርያት |
| የተፈጥሮ ፀባይ | እሴቶች |
| የሕይወትና የስራ ልምዶች | የድጋፍ መስጫ ስርዓት |
| የተወሰኑ ተግዳሮቶች | ፈጠራዊ መፍትሄዎችና አያያዞች |
| አካባቢያዊ ምርጫዎች | የማይወደዱ ነገሮች |
| ፈጠራዊ የመሆን እድሎችና ሃሳቦች | |

**ምንጭ፡** Dr. George Tilson, Transcen, Inc. 1 . "*Developing a Positive Personal Profile*" **Note**: የዚህ መሳሪያ የሚሞላ PDF ከአጋዥ የመረጃ ፍንጮች ጋር እዚህ ይገኛል፡ https://www.pdffiller.com/jsfiller-desk15/?projectId=335224385&expId=5498&expBranch=1#f87f164cf996551d027c7e87eb50

### ከሽግግር አስተባባሪ ጋር ይገናኙ

በእርስዎ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ያሉ የሽግግር አስተባባሪ ስል ድሕረ 2ኛ ደረጃ ትምህርት አማራጮች መረጃ ለማግኘት የመጀመሪያ ቦታ ሲሆን፣ በዚህም ውስጥ የስራ ቅጥርና የእንክብካቤ አገልግሎቶች፣ የሽግግር ፕሮግራሞችና የ DARS አገልግሎቶች ይገኙበታል። የአካባቢ አስተዳደሮች ለሚሸጋገሩ ተማሪዎች በሚሰጡት አገልግሎት ይለያያሉ።

### ለቅድመ ETS (Employment Transition Services) ለ DARS ያመልክቱ

ከ2019 ጀምሮ፣ DARS (Department of Aging and Rehabilitative Services) በአጠቃላይ የሽግግር ዕቅዱ መሰረት ለተማሪዎች ከ14 ዓመት ጀምሮ የቅድመ ETS አገልግሎቶችን መስጠት ጀምሯል። ይህ አዲስ አገልግሎት ከ DARS ጋር የሚሰሩ ተማሪዎችን ቁጥርና የሚሰጡ አገልግሎቶችን ስፋት ጨምሮታል። የት/ቤትዎ የስራ ቅጥርና የሽግግር ተወካይ ለአገልግሎቶቹ እንዲያመለክቱ ሊያግዝዎት ይችላል ወይም በቀጥታ ከ DARS ጋር መነጋገር ይችላሉ። አንድ ገጽ የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ብቻ ማመልከት ይቻላል።

አገልግሎቶቹ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የስራ ዕድል መዳሰሻ የመጀመሪያ መነሻ እንዲሆኑና የሽግግር ዕቅድንና ተማሪዎች ወደ ስኬታማ የስራ ዘመንና የጉልምስና እድሜ እንዲገቡ ለማዘጋጀት አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን ቀጣይነት ለማበልጸግ ታስበው የተዘጋጁ ናቸው። እነዚህ አገልግሎቶች የተማሪ/የወላጅ የፋይናንስ ተሳትፎ የማይደረግባቸው ሲሆን በ2ኛ ደረጃ፣ በድሕረ 2ኛ ደረጃና በሌሎች በታወቁ ፕሮግራሞች ውስጥ ላሉ፣ ዕድሜያቸው 14-21 ዓመት ለሆናቸውና ልዩ ትምህርት ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶችን እያገኙ ላሉ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚቀርብ ነው። ሁሉም አገልግሎቶች ነጻና በ DARS አማካሪዎችና ሰራተኞች እንደዚሁም በስራ ቅጥር አገልግሎት ድርጅቶች የሚሰጡ ናቸው።

### 5ቱ ቅድመ ETS

**ስለስራ አሰሳ ማማከር**

ተማሪዎች ስለ ስራ ዘመን አቅጣጫዎች፣ ስለሚፈለጉ ኢንዱስትሪዎችና የስራ መደቦች፣ ስለ ሰራተኛ ገበያና ስለ ሰራ ዘመን ፍላጎቶቻቸው እንዲማሩ ያግዛል። የፍላጎት ቆጠራና አሰሳ በዚህ ውስጥ የሚካተቱ ምሳሌዎች ናቸው።

**ስራ ተኮር የመማሪያ ተሞክሮዎች**

ተማሪዎች ስለስራው ዓለምና ስለተለያዩ የስራ መደቦችና የስራ ዘመን አቅጣጫዎች እንዲያውቁ በማገዝ የስራ ክህሎቶችን ለመተግበርና ለማሻሻል ዕድሎችን ያቀርባል። ከምሳሌዎች መካከል መረጃ መስጫ ቃለ መጠይቆች፣ የስራ ቦታ ጉብኝቶች፣ ከሌላ ሰራተኛ መማር፣ በጎ ፈቃደኝነት፣ ኢንተርንሺፕ፣ ወዘተ… ይገኙበታል።

**ድሕረ 2ኛ ደረጃ ትምህርትና የስልጠና ዕድሎችን በተመለከተ ማማከር**

ተማሪዎች ስለ ድሕረ 2ኛ ደረጃ የትምህርትና የሙያ ስልጠና ዕድሎች ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ የሚያግዝ ሲሆን የስራ ዘመን አቅጣጫ አቀራረብ ላይ አጽንኦት ይሰጣል። ከምሳሌዎች መካከልም ስለ ቅበላ መስፈርቶች ማስተማር፣ በኮሌጅ/የሙያ ፕሮግራም ትርኢቶችና ጉብኝቶች ላይ አቴንዳንስ እንዲኖር መደገፍ፣ የገንዘብ እርዳታ አማራጮችን መለየትና የማስፈጸም ተግባራዊ ክህሎቶችን መጠቀምን ማጎልበት ይገኙበታል።

**የስራ ቦታ ዝግጁነት ስልጠና**

ለጉልምስና ሕይወት መዘጋጀትንና አሰሪዎች ከአብዛኞቹ ሰራተኞች የሚጠብቋቸው የተለመዱ ክህሎቶች ማጎልበትን ይደግፋል። ከምሳሌዎች መካከልም በቀላል ክህሎቶች፣ ማሕበራዊ/ግለሰባዊ ክህሎቶች ላይ የሚሰጥ ስልጠና፣ በስራ ፍለጋ ላይ የሚሰጥ ስልጠና፣ እና ራስን ችሎ የመኖር ክህሎቶች ላይ የሚሰጥ ስልጠና ይገኙበታል።

**በግለ ተሟጋችነት ላይ የሚሰጥ ትምህርት**

ውጤታማ የተግባቦትና የውሳኔ አሰጣጥ ክህሎቶች መዳበርን የሚደግፍ ሲሆን፣ የራስን ዕድል በራስ ለመወሰን አጽንኦት ይሰጣል። ከምሳሌዎች መካከልም ግቦችን ማስቀመጥ፣ የችግር አፈታት ክህሎቶች ላይ ስልጠና መስጠት፣ ተማሪዎች አካል ጉዳታቸውን እንዴት መግለጽ እንዳለባቸው፣ የሚፈልጉትንና የሚያስፈልጋቸውን ነገር በሚገባ እንዴት እነደሚገልጹ፣ ሕይወታቸውን በማቀድ ረገድ ኃላፊነት እንዴት እንደሚወስዱና ግብረ-መልስ እንዴት እነደሚቀበሉ ማስተማር፣ ወዘተ… ይገኙበታል።

---

### ወላጆች ሊያግዙ የሚችሉባቸው መንገዶች

- ልጅዎ ቤት ውስጥ የሚሰራው ስራ ይስጡትና የቻለውን ያህል ብዙ ስራ ቤት ውስጥ እንዲሰራ ያድርጉ።
- ልጅዎ የግል፣ የትምህርትና የስራ ታሪኩን የያዘ መግለጫ እንዲያረቅቅ ያግዙት። በት/ቤት ላሉ የሽግግር ሰራተኞችና ለ DARS አማካሪው ያጋሩት
- በ IEP ስብሰባዎች ላይ ይካፈሉ፣ አዎንታዊ የግል ፕሮፋይል ያጋሩ፣ ለ IEP እና ከተማሪዎ የስራ ቅጥር ጋር ተዛማጅነት ላላቸው ሌሎች ዕቅዶች ወይም ግቦች ሃሳብዎን ያበርክቱ።
- እርስዎና ተማሪዎ በአስፈላጊነታቸው ላይ በተስማማችሁባቸው ማናቸውም ምክረ ሃሳቦችና ድጋፎች ላይ ከሽግግር ቡድኑ ጋር ይወያዩ።
- አስፈላጊ ሲሆን ይሟገቱ፣ በተቻለ መጠን ግን ልጅዎ ለራሱ እንዲናገር ያድርጉ።

---

## ከ DEPARTMENT OF AGING AND REHABILITATION SERVICES (DARS) ጋር መስራት

DARS የፌዴራልና የግዛት ፕሮግራም ሲሆን አካል ጉዳተኞች ለስራ ቦታ እንዲዘጋጁ፣ ስራ እንዲያገኙና በስራ ላይ እያሉም የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ ለማገዝ ለአንድ የተወሰነ ዓላማ የሚሰጡ የአጭር ጊዜ አገልግሎቶች ይሰጣል። DARS የተቀናጀና ማህበረሰብ አቀፍ የውድድር ስራ ቅጥር ላይ ያተኩራል።

DARS ተማሪዎች ሙያዊ ተሐድሶ (የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ ከማቀዳቸው ሶስት ዓመት በፊት የሚሰጡ አገልግሎቶች) እንዲፈትሹ ይመክራል። ይህ የቅድሚያ ተሳትፎ ተማሪዎች የ VR አማካሪያቸውን እንዲያውቁ የሚያግዛቸው ሲሆን፣ አማካሪውም ከተማሪው ጋር አብሮ በመስራት የስራ ቅጥር ግብ እንዲሳካ የሚያደርግ ተግባራትን ለመዘርዘር ያግዛዋል።

የ DARS አገልግሎቶች መካከል፡ ኢጋዥ ቴክኖሎጂ፣ የስራ ዘመን አሰሳ፣ የስራ ዘመን መምሪያና ማማከር፣ የስራ ማጎልበት፣ የስራ ምደባ፣ ከሌላ ሰው መማር፣ የስራ ላይ ስልጠና፣ ድሕረ 2ኛ ደረጃ ስልጠና እና ትምህርት፣ PERT፣ የተደገፈ የስራ ቅጥር፣ እና የሙያ ግምገማና ምዘና ይገኙበታል። ስለ DARS አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘትና መምሪያቸውን ለማውረድ፣ ይህን ይጎብኙ፡ https://www.vadars.org/drs/transitionservices.htm

### የአማካሪዎ የስራ ድርሻ

የሙያ ተሐድሶ (VR) አማካሪዎ በአካል ጉዳተኝነትና በስራ ዘመን ማማከር ላይ ኤክስፐርት ነው። በኤልክሳንድሪያ፣ አርሊንግተን፣ ፌርፋክስና ፎልስ ቸርች ውስጥ ለሚገኙ ት/ቤቶች የተመደበ አማካሪ አለ። አማካሪው እርስዎ የ DARS አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ መሆንዎን ይወስናሉ፣ በውድድር ላይ የተመሰረተ የስራ ቅጥርን መሰናክሎች ለመለየት ያግዛሉ፣ ከእርስዎ ጋር በመሆንም በግለሰባዊ የስራ ቅጥር ዕቅድዎ (IPE) ላይ ይሰራሉ።

አማካሪዎ ከእርስዎ ዶክተሮች፣ ቴራፒስቶች፣ የቀድሞ አሰሪዎች (ካሉ) እና ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር እንዲነጋገሩና ሰነዶችን እንዲቀበሉ ለማስቻል የመልቀቂያ ስምምነት መፈረም አለባችሁ እርስዎ ወይም (የእርስዎ ወላጅ)።

### የ DARS ደንበኛ መሆን

ለመሳተፍ፣ የሚከተሉትን ሒደቶች ማለፍ አለባችሁ፡ ቅብብሎሽ፣ መረጃ መሰብሰብ፣ ብቁነትን መወሰን፣ ፍላጎትን መመዘንና ዝግጅትና ትግበራን ማቀድ።

### ቅብብሎሽ

አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች (IEPs ወይም 504 Plan ያላቸው) ለ DARS የሙያ አገልግሎቶች እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ። የሽግግር ስፔሻሊስትዎ እንዲያስተላልፉዎ ይጠይቁ ወይም ለ DARS በስልክ ቁጥር 800-552-5019 መደወል ይችላሉ።

### መረጃ መለዋወጥ

አሁንም ት/ቤት ውስጥ ከሆነ ያሉት፣ የሽግግር አስተባባሪዎ ከ DARS አማካሪዎ ጋር የመጀመሪያ ስብሰባ እንዲያደርጉ ሊያመቻችልዎ ይችላል፣ ወይም ራስዎ ለአካባቢው ጽ/ቤት መደወል ይችላሉ። የዚህ የመጀመሪያ ስብሰባ ዓላማ ስለ ስራ ዕቅዶችዎ፣ ስለ አካል ጉዳትዎ፣ ትምህርትዎና ስለ ማንኛውም የስራ ታሪክዎ እና DRS እንዴት ሊያግዝዎ እንደሚችል ለመነጋገር ነው።

በዚህ ስብሰባ ላይ፣ አማካሪዎ ተጨማሪ መረጃ እንዲቀርብ ወይም የስነ-ልቦና ምርመራ ወይም የተሐድሶ ቴክኖሎጂ ምዘና የመሳሰሉ ተጨማሪ ምርመራዎች (እርስዎ ወጪ ሳያወጡ) እንዲደረጉ ሊጠይቁ ይችላሉ። DARS የእርስዎን መረጃዎች ጠይቆ ለማግኘት እንዲያስችለው መልቀቂያ እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ።

### ብቁነት

በተቀናጀ የስራ ማዕቀፍ ውስጥ በውድድር ላይ የተመሰረተ የስራ ቅጥር የማግኘት ግብ ካለዎትና የብቁነት መስፈርቱንም የሚያሟሉ ከሆነ፣ ለ DARS ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ብቁ የሆኑ ግለሰቦች የተሰነደ አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ስሜታዊ፣ ወይም የመማር አካል ጉዳት ያለባቸውና ጉዳታቸውም ስራ ማግኘት ወይም ይዞ መቆየት ላየ ከፍተኛ መሰናክል የሚፈጥርባቸው ሊሆኑ ይገባል።

የፋይናንስ ብቁነት በቤተሰብ ገቢ ላይ የተመሰረተ ነው። DARS እያደገ የሚሄድ ስኬል የሚጠቀም ሲሆን ይህም በቅርብ ጊዜ በቀረበ የገቢ ግብር ተመላሽ ላይ በተዘረዘሩ ጥገኞች ብዛት ላይ የሚመሰረት ነው። ይሁን እንጂ፣ ተማሪዎች በአካል ጉዳታቸው ምክንያት ማሕበራዊ ዋስትና አካል ጉዳት (SSDI) ወይም ተጨማሪ የዋስትና ገቢ (SSI) የሚያገኙ ከሆነ፣ ስራ ለመቀጠር ፍላጎት ካላቸው ለ DARS አገልግሎቶች ብቁ እንደሆኑ ይታሰባል።

ከእርስዎና ከመዝገብዎ የተገኙ መረጃዎችና ማናቸውም አዳዲስ ሪፖርቶች ስለ አካል ጉዳትዎ፣ የስራ ችሎታዎ ላይ ስለሚያሳድረው ተጽእኖ እና የ DARS አገልግሎቶች ስራ እንዲያገኙ ያስችሉዎት እንደሆነ ለማወቅ ያገለግላሉ። የአካል ጉዳት ቢኖርብዎትም እንኳን እርስዎና አማካሪዎ ሁሉንም የብቁነት መስፈርቶችን ማሟላትዎን መወሰን አለባችሁ።

ለማመልከት፣ ከ DARS የተሐድሶ አማካሪ ጋር መረጃ ይለዋወጡ። የማሕበራዊ ዋስትና ካርድ፣ ፎቶ ያለበት መታወቂያ ካርድ፣ የበሽታ ዓይነት የሚገልጹ ሰነዶች፣ የጤና ኢንሹራንስ መረጃና ተማሪው ከ18 ዓመት በታች ከሆነ የወላጅ ፈቃድን የያዙ ሰነዶች ማቅረብ አለብዎት። የመጀመሪያው ስብሰባ በተደረገ በ 60 ቀናት ውስጥ የብቁነት ግምገማው ይጠናቀቃል። መረጃዎችዎን ለአማካሪዎ በማቅረብ ወይም አማካሪዎ መረጃዎቹን እንዲጠይቅ በመፍቀድና ቀጠሮዎችዎን በማክበር እገዛ ማድረግ ይችላሉ።

### ፍላጎቶችን መገምገም

የብቁነት መስፈርቱን ካሟሉ፣ እርስዎና አማካሪዎ ስለ ሙያዊ ግብዎ ተነጋግራችሁ ለእርስዎ ትክክለኛ የሆነውን **የስራ ዓይነት** ለመምረጥ አብራችሁ ትሰራላችሁ።

ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገዎ፣ አማካሪዎ የሙያ ምዘና እንዲደረግ (እርስዎ

ወጪ ሳያወጡ) ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላሉ። የሙያ ምዘና ከሚያካትታቸው መካከል የማማከር አገልግሎት፣ መፈተን፣ የስራ ናሙናዎችና የስራ ላይ ምዘናዎች ይገኙበታል። ውጤቶቹም እርስዎ መስራት ስለሚችሉትና በጣም ሊሰሩት ስለሚፈልጉት ስራ ዓይነት ሁለታችሁም እንድታውቁ ሊያግዟችሁ ይችላሉ።

ቀጥሎም፣ ለተባለው ዓይነት ስራ ለመዘጋጀትና ስራውን ለማግኘት **ምን ዓይነት አገልግሎቶች** እንደሚያስፈልግዎ እርስዎና አማካሪዎ በጋራ ትወስናላችሁ። በነጻ ከሚቀርቡ አገልግሎቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡

- የስራ ዘመን ዳሰሳ
- የስራ ዘመን መምራትና ማማከር
- የአካል ጉዳተኝነት ግንዛቤ ማማከር
- ከስራ ምደባ በኋላ የሚሰጡ የክትትል አገልግሎቶች
- የስራ ፍለጋና ምደባ (የስራ አሰልጣኝ አያስፈልግም)
- የሙያ ምዘና
- የስራ ላይ ስልጠና ፕሮግራም
- ያል ክፍያ የሚሰራ ስራ ልምድ

የወጪ መጋራት ሊኖራቸው ከሚችል አገልግሎቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡

- ኮሌጅ
- የስልጠና ፕሮግራሞች
- ለረዥም ጊዜ የሚያገለግል የሕክምና መሳሪያ ወይም ሌሎች ዕቃዎች
- አጋዥ ቴክኖሎጂ
- ቴራፒዎች ወይም ሌሎች የሕክምና አገልግሎቶች
- የሚደገፍ የስራ ቅጥር (ከስራ አሰልጣኝ ጋር መስራት)

**ግለሰባዊ የስራ ቅጥር ዕቅድ (IPE)** ለ DARS ብቁ መሆንዎ ከተረጋገጠ በኋላ፣ እርስዎና ቤተሰብዎ ከ VR አማካሪ እና/ወይም የወደፊት አገልግሎት አቅራቢ ጋር አብራችሁ በመስራት ግለሰባዊ የስራ ቅጥር ዕቅድ (IPE) ታዘጋጃላችሁ። ግለሰባዊ የስራ ቅጥር ዕቅዱ (The IPE):

- የግለሰቡን የስራ ዘመን ፍላጎቶችና በመረጃ የተደገፈ ምርጫውን ያንጸባርቃል
- በስራ ቅጥር ግብ ላይ ያተኩራል
- የስራ ቅጥርን ግቦች ለማሳካት መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ይዘረዝራል
- ለአስፈላጊ ዕቅዶችና የገንዘብ ድጋፍ ዕቅዶችን ያወጣል

ስለ አስፈላጊ አገልግሎቶች ስታስቡ፣ እርስዎ፣ ወላጆችዎና የ VR አማካሪው ለስራ ለመዘጋጀት፣ ብቁ ለመሆን ወይም ለማመልከት ወይም በስራ ላይ ለመቆየት ችሎታዎ ላይ ተጽእኖ ሊያስከትል የሚችል ማንኛውም ነገር ከግምት ውስጥ ታስገባላችሁ። በእነዚህም ውስጥ የሚካተቱት፡ እንቅስቃሴ፣ በራስ መመራት፣ ራስን መንከባከብ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር የመግባባት ችሎታ፣ የተግባቦት ክህሎቶች፣ ድርጅታዊ ክህሎቶች፣ ለራስ የመሟገት ክህሎቶች፣ ጽናት፣ የገንዘብ አያያዝ፣ እና የመድሃኒት አወሳሰድ ይገኙበታል።

IPE ላይ ሲፈርሙ፣ ስራ ለመቀጠር በዕቅዶችዎ ውስጥ የተገለጹትን እርምጃዎች እንደሚወስዱ ቃል እየገቡ ነው ማለት ነው። የ IPE ዕቅድ ማውጣት ስራን ከአማካሪዎ፣ ከወላጆችዎ ወይም ሞግዚትዎ ጋር ሆነው እንዳከናወኑትም ያሳያሉ። በ IPE ስር ያለዎትን የስራ ድርሻ፣ መብቶችና ኃላፊነቶች መረዳትዎን እርግጠኛ ለመሆን ጥያቄዎችን ይጠይቁ። IPEs ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ይከለሳሉ።

የሙያ ተሐድሶዎ ላይ ውጤት ስለሚያስከትሉ ማናቸውም ለውጦች (አድራሻ ወይም የስልክ ቁጥር፣ የፋይናንስ ሁኔታ ወይም የቤተሰብ ብዛት፣ የሕክምና ኢንሹራንስ፣ አካል ጉዳትዎ ወይም አጠቃላይ ጤናዎ ወይም ከመንግስት የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች) ለአማካሪዎ ማሳወቅ አለብዎ።

## የ DARS አገልግሎት መስጫዎች

**Wilson Workforce and Rehabilitation Center (WWRC)** አድራሻው Fishersville የሆነው WWRC ለአካል ጉዳተኞች መጠነ ሰፊና ግለሰባዊ አገልግሎቶችን በማቅረብ ስራ እንዲቀጠሩና ነጻነታቸው እንዲሻሻል ያደርጋል። WWRC የሙያ ምዘናና ስልጠና፣ የሕክምና ተሐድሶ፣ የኑሮ ክህሎቶች ግምገማና ስልጠና፣ አጋዥ ቴክኖሎጂና ሌሎች አገልግሎቶችን ይሰጣል። ስለ WWRC ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ፡ http://wwrc.virginia.gov

**ድሕረ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ተሐድሶና የሽግግር ፕሮግራም (PERT)**
የ PERT ፕሮግራም በ WWRC ውስጥ የሚተገበር ከት/ቤት ወደ ስራ የሚያደርስ ጅማሮ ሲሆን አካል ጉዳት ላለባቸው የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በሙያ፣ ራስን ችሎ በመኖር፣ በማህበራዊና በመዝናናት ክህሎቶች ላይ ከ5-10 ቀን የሚቆይ ሁሉን አቀፍ ምዘና ያካሂዳል። መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች ዕድሜያቸው 16 ዓመትና ከዚያ በላይ ሆኖ IQ 60 ወይም ጥሩ የሆነ የመላመድ ክህሎቶች ማስረጃ ሊኖራቸው ይገባል፤ ተማሪው ከ PERT ክፍለ ጊዜ በኋላ በበልግ ወቅት ወደ ት/ቤት መመለስ አለበት (በሌላ አነጋገር፣ በመጨረሻ የትምህርት ዓመት ላይ መሆን የለብዎትም)።
PERT የሚከተሉትን ያቀርባል፡

- የኑሮ ክህሎቶች ምዘና
- የሙያ ምዘና
- የቴራፒ ምዘናዎች
- የሙያ ስልጠና ፕሮግራሞች

ለ PERT ለማመልከት፣ በ2ኛ ደረጃ ት/ቤትዎ የሚገኙትን የሽግግር አስተባባሪ ያነጋግሩ። ማመልከቻዎ ተቀባይነት የሚኖረው ከ DARS ጋር የተከፈተ ጉዳይ ካለዎት ነው። ስለ PERT ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ወደ [1][g1]http://wwrc.virginia.gov/PERT.htm[/g1] ][4] ይግቡ

**የቅድመ ቅጥር እና ለትምህርት ዝግጁነት ፕሮግራም (PREP)**
ይህየዘጠኝ ሳምንት ቆይታ ያለው የማስተዋወቂያ ፕሮግራም በ WWRC ውስጥ በሶስት ሞጁሎች የተከፋፈለ ነው። ደንበኞች ወደ ስራ ቅጥርና ራስን መቻል ሲሸጋገሩ ለሚያስፈልጓቸው ክህሎቶች መሰረት እንዲሆኑ በታሰቡ የትምህርት ክፍሎች ላይ ይሳተፋሉ። ከሚካተቱ ግቦች መካከል ተማሪው ስራ ለመፈለግና ለማግኘት ያለውን ችሎታ የሚደግፉ ክህሎቶችን እንዲያውቅ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ስለሚኖር መስተጋብር ያለን ግንዛቤ ማሳደግና ግላዊ የአስተዳደር ክህሎቶችን ማጎልበት ይገኙበታል። [g1] በካምፓስ ውስጥና ከካምፓስ ውጭ የሚከናወኑ ተግባራት ከገንዘብ አስተዳደር፣ አስቤዛ ሸመታና ምግብ ማብሰል አንስቶ እስከ ግላዊ የጤና እንክብካቤ፣ የአካል ጉዳተኝነት ግንዛቤ፣ ለራስ

መሚገትና የስራ ማፈላለጊያ ክህሎቶች የመሳሰሉ ጉዳዮችን ያስተዋውቃሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ ወደ http://wwrc.net/LSTP.htm ይግቡ

ለማመልከት፣ የ DARS አማካሪዎን ያነጋግሩ። ቡድኑ ከተስማማበት፣ ከአማካሪዎ ጋር ሆነው ማመልከቻ ይሞላሉ፤ ከዚያም ማመልከቻው ለ WWRC የቅበላ ኮሚቴ የሚቀርብ ሲሆን ኮሚቴውም የመጨረሻውን ውሳኔ ይወስናል።

**የ DARS ውስንነቶች**

DARS በማንኛውም ጊዜ ስራ እንደሚገኝ ዋስትና አይሰጥም። የራስዎን የስራ ፍለጋ ማካሄድዎን መቀጠል አለብዎት። ወደ ት/ቤት ወይም ሌላ ዓይነት መዋቅር እንደሚልክዎትም ቃል መግባት አይችልም።

DARS የሚደረግለት የገንዘብ ድጋፍ ውስን ሲሆን፣ DARS ለአገልግሎቱ ቅደም ተከተል (የመምረጫ ቅደም ተከተል) እንዲያዘጋጅ ሕጉ ያስገድደዋል፤ በዚህም መሰረት እጅግ ከባድ የአካል ጉዳትና የተግባር ውስንነት ላለባቸው (በ DARS በተሰጠው ፍቺ መሰረት እንቅስቃሴ፣ በራስ መመራት፣ ራስን መንከባከብ፣ የተግባቦት ክህሎቶች፣ የስራ ክህሎቶች፣ የግንኙነት ወይም የስራ መስተንግዶ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር የሙያ መሰናክል ወይም እንቅፋት) ቅድሚያ መስጠት አለበት።

**ክልላዊ የ DARS ጽ/ቤት አድራሻ**

**የአሌክሳንድሪያ DRS ጽ/ቤቶች**

ለአርሊንግተን እና አሌክሳንድሪያ አገልግሎት ይሰጣል
5904 Old Richmond Highway Suite 410
Alexandria, VA 22303
Karen.Brown@dars.virginia.gov (703) 960-3411

**የፌርፋክስ/ፎልስ ቸርች DRS ጽ/ቤት**

11150 Fairfax Blvd. Suite 300
Fairfax, VA 22030
Leanne.rerko@dars.virginia.gov (703) 359-1124

**የማናሳስ DRS ጽ/ቤት**

9300 West Courthouse Road, Suite 302, Manassas, VA
Tiffany.Jenkins@dars.virginia.gov (703)335-5550

ከ Northern Virginia አካባቢ ውጭ ከሆኑ፣ https://vadars.org/offices.aspx በመጎብኘት የአካባቢዎን ጽ/ቤት ማግኘት ይችላሉ።

DARS ብቁ ለሆኑ ደንበኞች በርካታ የአጭር ጊዜ የቅጥር አገልግሎቶችን ለመስጠት የቅጥር አገልግሎት ድርጅቶች (ESO) ከሚባሉ ውጫዊ ድርጅቶች ጋር ኮንትራት አለው። ለምሳሌ፣ ለሁኔታዊ ምዘናዎች ብቁ መሆንዎን ለመወሰን ከ VR አማካሪዎ ጋር ሊገናኙ ይችላሉ፤ ከዚያም ከ DARS የተመደቡት የ VR አማካሪ ከ ESO ከመጣ የቅጥር ስፔሻሊስት ጋር ኮንትራት በመግባት በሁኔታዊ ምዘና ውስጥ እንዲሳተፉ ወደ ቦታው ይወስድዎታል። እነዚህ አገልግሎት አቅራቢዎች ለትርፍ ያልተቋቋሙ ወይም ለትርፍ የሚሰሩ የግል ድርጅቶች ሊሆኑ ይችላሉ። የእነዚህ አገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር ገጽ 50 ላይ ይጀምራል።

**የስራ ቅጥር ስፔሻሊስት የስራ ድርሻ**

አንዴ የ DARS ደንበኛ ከሆኑ በኋላ ከ DARS ከመጣ የሙያ አማካሪ ወይም ከ DARS ጋር ኮንትራት ካለው የቅጥር አገልግሎት ድርጅት (ESO) ከመጣ የስራ ቅጥር ስፔሻሊስት ጋር በቅርብ ይሰራሉ። ስለ ESO ተጨማሪ መረጃ በቀጣዩ ክፍል ውስጥ ይገኛል። የወደፊት ተቀጣሪ ሰራተኛ በመሆንዎ፣ የስራ ቅጥር ስፔሻሊስቱ በሚከተሉት መስኮች ሊያግዝዎ ይችላል: ለስራ ለመዘጋጀት፣ ስራ ለማግኘትና በስራ ላይ ለመቆየት፤ እምርታዎን በተመለከተ ከቤተሰብዎ ጋር መረጃ ለመለዋወጥ፤ አስፈላጊ ማመልከቻዎችና የግል ታሪክ ጽሁፎችን ለማጠናቀቅ፤ እንዳስፈላጊነቱ በመጀመሪያው ስልጠናዎ እርስዎን ለማገዝ፤ የትራንስፖርት ግብዓቶችና የጉዞ ስልጠናን መለየት።

የስራ ቅጥር ስፔሻሊስቶች በስራ መስፈርቶችና በእርስዎ ክህሎቶች መካከል መጣጣም መኖሩን ለማረጋገጥ ከእያንዳንዱ ቀጣሪ ድርጅት ጋር አብረው ይሰራሉ፤ ከስራዎቹም መካከል:
ከአሰሪው ጋር በመስራት ስላለው የስራ ዕድል ማወቅ፤ የስራውን ወሰን ለማወቅ ከቀጣሪ ኃላፊ ጋር በቅርበት ይሰራል፤

የስራ ክፍሉን ወሳኝ ስራዎችና ባህላዊ ገጽታዎች በተመለከተ የስራውን አካባቢ ይተነትናል፤ የቃለ መጠይቅ ፕሮግራም ለመያዝና ለማቀድ ለሰው ሐይል መምሪያ ድጋፍ ያደርጋል፤ እርስዎ የሚያስፈልግዎትን መስተንግዶ እና/ወይም የመላመድ ሁኔታ ይለያል፤
ከአሰሪው ጋር ግንኙነት በማድረግ እምርታዎን ይገመግማል፤ እንዳስፈላጊነቱም ለስራ ባልደረቦች ስለ አካል ጉዳት ግንዛቤ መስጫ ስልጠና ይሰጣል።

ስፔሻሊስቱ ከ DARS አማካሪ ጋር በመቀናጀት ስለ ስራ ስትራቴጂዎች፣ የአሰሪውንና የስራ ባልደረባዎች አሳሳቢ ጉዳዮች፣ በስራ ቦታ ስለሚያስፈልጉ ተፈጥሯዊ ድጋፎች ዝግጅት ይመካከራል።

**የስራ ማጎልበቻ ሒደት**

የስራ ማጎልበቻ ሒደት አራት ደረጃዎች አሉት:

**ሁኔታዊ ምዘናዎች (ወደ 1 ወር ገደማ)**

ሁኔታዊ ምዘናዎች (ወደ ስራ ቦታ መሄድና ስራዎችን "መለማመድ") የስራው አሰልጣኝ አንድ ግለሰብ አንድ የተወሰነ ስራን እንዴት መፈጸም እንደሚችል እንዲያይ ያስችለዋል። በምዘናው ወቅት የተሰበሰበ መረጃ የስራ ፍለጋው ከመጀመሩ በፊት ፍላጎት፣ የክህሎት ደረጃ፣ ተመራጭ አካባቢና ሌሎች ጉዳዮችን ለመወሰን ያግዛል። ሁኔታዊ ምዘና የሚፈልገው ወይም የሚያስፈልገው ሁሉም ሰው አይደለም።

**የስራ ማጎልበቻ (2-6 ወራት)**

ይህ ምዕራፍ ተጨባጭ የስራ ፍለጋና ለስራ ቃለ መጠይቅ መሰናዶችን ይጨምራል: ትስስር መፍጠር፣ የስራ ዕድሎችን ማፈላለግ፣ የግልና የስራ ታሪክን መጻፍ ወይም ማዘመን፣ የማመልከቻ ደብዳቤ ማዘጋጀት፣ የስራ ቅጥር ማመልከቻዎችን አሞላልና ቃለ መጠይቅን መለማመድ።

**ምደባ እና ስልጠና**

ተገቢ የሆነ ስራ ሲገኝ፣ አገልግሎት ሰጪው በቃለ መጠይቁ በመቀጠል ማናቸውንም ተፈላጊ መስተንግዶ ለመወሰን ያግዛል። አንዴ ስራውን ከጀመሩ፣ ስፔሻሊስትዎ የስራ አሰልጣኝዎ በመሆን ለስራው እንዲሰለጥኑ በማገዝ የእርስዎን ስኬታማነት ለማረጋገጥ ስለሚያስፈልጉ ስትራቴጂዎች ከእርስዎ፣ ከአሰሪው እና ከቤተሰብዎ ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

በውድድር ላይ የተመሰረተ የስራ ቅጥር ስልጠና የተወሰነ የጊዜ ሰሌዳ ያለው ነው፤ ራስዎን ችለው መንቀሳቀስ ምቾት እስከሚሰጥዎ ድረስ

በጣም በቅርበት አብሮ የመስራትን የመጀመሪያ ምዕራፍ ያልፋሉ። በስራው ላይ የሚወሰድ የጣልቃ ገብነት እርምጃ መጠን የሚወሰነው በግለሰቡ ፍላጎት ላይ ነው። ግለሰቡ ያለ ድጋፍ መንቀሳቀስ ሲችልና ነገሮችም በጥሩ ሁኔታ መሄድ ሲጀምሩ የስራ ላይ ስልጠናው እየቀነሰ ይሄዳል።

ግለሰቡ ከስራ አሰልጣኙ የሚደረግለት እርምጃ ቀንሶም በስራው ላይ ከተረጋጋ፣ ቡድኑ ስለ ቀጣይ እርምጃዎች ይወያያል። የጉዞ ስልጠና ከአገልግሎት አቅራቢው ጋር የሚደረግ ውል አካል ሊሆን ይችላል። ስልጠና በምደባ ላይ ስኬታማ ለመሆን ወደሚያስፈልጉ የውጭ ማህበራዊ ተቋማት ማስተላለፍንም ሊጨምር ይችላል።

**ወላጆች ሊያግዙ የሚችሉባቸው መንገዶች**

- ✓ የልጅዎን ፀጉር ማስተካከል፣ በአግባቡ ማልበስና ሰዓት ማክበርን በመጠቀም ከስራ ቦታ የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማጠናከር
- ✓ ቤት ውስጥ ከልጅዎ ከሚያዩትና ከሚሰሙት በመነሳት ስለ ስራ ልምድ ለአማካሪዎች ግብረ መልስ መስጠት
- ✓ ልጅዎ በስራው ላይ ያለው አፈጻጸም ምን እንደሚመስል ከስራ ቅጥር ስፔሻሊስትና ከአሰሪው ግብረ-መልስ ይጠይቁ
- ✓ ትራንስፖርትና ልዩ መስተንግዶዎችን የመሳሰሉ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ እገዛ ለመስጠት ዝግጁ ይሁኑ
- ✓ ለልጅዎ ኃላፊነቶችን በመጨመር ለምሳሌም በቤት አካባቢ ላሉ ስራዎች ተጠያቂ እንዲሆን በማድረግ ይደግፉት። ለመጀመር ያህል በጣም ትንሽ የሚባል ተግባር/ኃላፊነት የሌለ ሲሆን ይህንኑ ስራም ማዳበር ይቻላል።

***ጉዳይዎን መዝጋት***ባጠቃላይ፣ ቢያንስ ለ 90 ቀናት ያህል ስራውን በተረጋጋ ሁኔታ ሲሰሩ ከቆዩ፣ እርስዎና አማካሪዎ የ DARS ጉዳይዎን ትዘጋላችሁ። ጉዳይዎ ከመዘጋቱ በፊት፣ አማካሪዎ ስራው ለእርስዎ ትክክለኛ መሆኑንና አሰሪዎም ደስተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ በቅርበት ይሰራል።

ብቁነትዎ ካበቃ፣ የሚሰጡ አገልግሎቶች ለእርስዎ ስራ የማያስገኙ ከሆኑ፣ ወይም ኃላፊነትዎን ካልተወጡም DARS ጉዳይዎን ሊዘጋው ይችላል።

ጉዳይዎ ከተዘጋ በኋላ ተጨማሪ የ DARS አገልግሎት እንደሚያስፈልግዎ ካሰቡ፣ ጉዳይዎን እንደገና ለማስከፈት ወይም ከውስን ፍላጎቶችዎ ጋር አግባብነት ላላቸው አገልግሎቶች በድጋሚ የማመልከት አማራጮችን በተመለከተ መወያየት ይችላሉ። አገልግሎቶችዎን ካቀረበውና ለማቅረብም ከ DARS ጋር ለሰራው ESO ማመልከትም ይችላሉ።

# ቅጥያ 11፡ ከማህበረሰብ አገልግሎቶች ቦርድ (CSB) እና የስራ ቅጥር አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች (ESO) ጋር መስራት

ለ DARS የሚደረገው የገንዘብ ድጋፍ አንዴ ካቆመ፣ በስራ ቅጥር አገልግሎት ድርጅቶች በኩል ዘላቂ ድጋፍን ለማስቀጠል የሚያስፈልገው የገንዘብ ድጋፍ በ Developmental Disabilities Medicaid Waiver፣ በአካባቢው የማህበረሰብ አገልግሎቶች ቦርድ (CSB) ወይም በቤተሰቡ የግል ክፍያ ሊሸፈን ይችላል።

ቨርጂኒያ ውስጥ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ቦርዶች "የኬዝ አስተዳደር" አገልግሎቶች ወይም "የድጋፍ ቅንጅት" ለማግኘት ብቁ መሆንና በዘላቂነት የሚያቀርቡ "የአካባቢ መንግስታዊ ተቋማት" ናቸው። CSBs የዕድገት አካል ጉዳት (የአእምሮ አካል ጉዳትን ጨምሮ) እንዳለባቸው በምርመራ ለተረጋገጠባቸው ግለሰቦች ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፎችን ያስተባብራሉ።

CSB አስተባባሪዎች ግለሰቦችና ቤተሰቦች የሚያስፈልጋቸውን አገልግሎትና ግብዓት እንዲለዩና ትስስር እንዲፈጥሩ ይደግፋል። አገልግሎቶችን ያቀናጃሉ፣ ይከታተላሉ፣ የቴክኒክ እገዛ ይሰጣሉ፣ ለግለሰቡም ይሟገታሉ። ከግለሰባዊ አገልግሎቶችና ድጋፎች መካከል የሕክምና፣ የትምህርት፣ የስራ ቅጥር/የሙያ፣ የቤት፣ የፋይናንስ፣ የትራንስፖርት፣ የመዝናኛ፣ የሕግና የችግር አፈታት ክህሎት ማጎልበቻ አገልግሎቶች ይገኙበታል።

አስተባባሪዎች የዕድገት አካል ጉዳት ላለባቸው ግለሰቦች የቤት ውስጥና የማህበረሰብ አቀፍ Medicaid Waivers ብቁነታቸውን እንዲወስኑ ድጋፍ ያደርጋል። በአካባቢዎ ከ CSB እና ከ Medicaid Waiver የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማግኘት እንዴት ማመልከት እንዳለብዎት መረጃ ለማግኘት፣ ገጽ 23ን ይመልከቱ።

CSB የስራ ቅጥር አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን በማስተባበር የስራ ቅጥር ወይም ትርጉም ያለው የእንክብካቤ ድጋፍ ይሰጣል። የ CSB የስራ ቅጥርና የእንክብካቤ አገልግሎቶች የዕድገት አካል ጉዳት፣ ከባድ የአእምሮ ሕመም እና/ወይም የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነት ለተገኘባቸው ሰዎች የተለያየ ደረጃ ያላቸው የስራ ቅጥርና የእንክብካቤ ድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ።

የተለያዩ የአገልግሎት አቅራቢዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ (ዝርዝሩ ገጽ 50 ላይ ይጀምራል) ለእርስዎ በጣም ስኬታማ የሚሆነውን መምረጥ ይፈልጉ ይሆናል። ድረ ገጻቸውን በመጎብኘት ይጀምሩና ቀጠሮ ያስይዙ።

### ማስታወሻዎች

- የሚከተሉት ጥያቄዎች እርስዎ ከስራ ቅጥር አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጋር በሚገናኙበት ጊዜ እርስዎን ለማገዝ የሚያስችሉ አጠቃላይ መመሪያዎች ናቸው። ዝግጅት ሲያደርጉ፣ ከልጅዎ የተለየ ፍላጎት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን ማሰብ ይጀምራሉ። ማንኛውም ጥያቄ ቢኖርዎት ከመጠየቅ አያመንቱ!

- ከ ESO ጋር ስብሰባ ከማድረግዎ በፊት፣ ከእርስዎ ጋር ግንኙነት ስላላቸው የገንዘብ ምንጮች (Community Service Boards፣ Department of Aging and Rehabilitative Services፣ Medicaid Waiver፣ Self-Directed Services) ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖርዎት ይመከራል። ለእርስዎ ዝግጁ የሆኑ የድጋፍ አማራጮች የትኞቹ እንደሆኑ ይወቁ።

- ለ ESOs ቃለ መጠይቅ ማድረግ ሲጀምሩ፣ ከዚህ በፊት አስበዋቸው የማያውቁ ጥያቄዎች በሒደት ይነሳሉ። ይህ ጥሩ ነገር ነው! የተወሰነ የአገልግሎት ንጽጽርን ለማጠናቀቅ ሁለተኛ ቃለ መጠይቅ ማድረግ አስፈላጊነቱ ከተሰማዎት፣ ዳግም ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ተጨማሪ ጊዜ ይውሰዱ።

- ችሎታዎን፣ ክህሎትዎን፣ ፍላጎትዎንና ግብዎን ያጋሩ።

- ውሳኔዎን ሲወስኑ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያስቡ፡ አገልግሎት አቅራቢዎ ለጥያቄዎችዎ መልስ የሰጠው እንዴት ነበር? በአክብሮት አስተናግደዎታል? ሰራተኞቹን ወደዋቸዋል? ራሳቸውን ያቀረቡት ፕሮፌሽናል በሆነ መንገድ ነበር?

---

**የሚጠየቁ ጥያቄዎች ምሳሌዎች**
**የስራ ቅጥር አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች**

- ድርጅታችሁ የስራ ጥቆማዎችን ለሕዝብ የሚያዘጋጀው እንዴት ነው?
- ሰዎችን በየትኞቹ ድርጅቶች ውስጥ መድባችኋል፣ በምን ዓይነት ስራዎች ላይ?
- በስራ ማጎልበቻ እና ስልጠና ላይ ለቤተሰቡ የሚሰጡት ግብረ መልስ ምን ዓይነት ነው?
- የስራ አዘጋጁ የስራ ላይ ስልጠናም ይሰጣል ወይስ ይህን የሚሰራ ሌላ ግለሰብ (ማለትም፡ የስራ አሰልጣኝ፣ የተፈጥሮ ድጋፍ መዋቅር፣ ተባባሪ ሰራተኛ፣ አሰልጣኝ፣ ወዘተ…) ይቀጠራል?
- የቅጥር ቦታን ከግለሰብ ጋር በሚያዛምዱበት ወቅት ታሳቢ የሚያደርጓቸውን አንዳንድ ጉዳዮች ይግለጹ።
- ለአዲስና የወደፊት ቀጣሪ ያለዎት የገበያ ስትራቴጂ ምንድን ነው?
- ድርጅታችሁ ድጋፍ በሚደረግለት የስራ ቅጥር ውስጥ አገልግሎት የሚሰጣቸው ሰራተኞች ብዛት ስንት ነው?
- ከግለሰቡ ጋር ራስዎን ይበልጥ ለማስታዋወቅ ምን ዓይነት ተግባራት ያከናውናሉ?
- ወደ ስራ ቦታና ከስራ ቦታ የጉዞ ስልጠና ትሰጣላችሁ?
- ምን ዓይነት ወጪዎች ይወጣሉ፣ የሚከፍለውስ ማነው? ምን ዓይነት የገንዘብ ድጋፍ ምንጮችን ትቀበላላችሁ?
- ተግባቦታችን ምን ይመስላል?
- ድርጅትዎ የሚሰጣቸው ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶች ወይም ስልጠናዎች ምንድን ናቸው? ማህበራዊ ክህሎቶች፣ ራስን ችሎ የመኖር ክህሎቶች፣ የተግባቦት ክህሎቶች ስልጠና? የበጎ ፈቃደኝነት ልምዶች? የማህበረሰብ ቅንጅት አገልግሎቶች?
- ስራ ካገኘሁ በኋላ ተጨማሪ እገዛ ቢያስፈልገኝ ምን ታደርጋላችሁ?
- ስራ እየፈለግኩ ባለሁበት ጊዜ የምታቀርቡት ማንኛውም አገልግሎት አለ? ለምሳሌ፣ የመግባቢያ ክህሎቶች መመሪያ፣ ትርጉም ያለው የማህበረሰብ እና/ወይም የበጎ ፈቃደኝነት ተሞክሮዎች? አዎ ካሉ፣ ሊገልጿቸው ይችላሉ? አገልግሎቶች በማህረሰቡ ውስጥ የሚቀርቡት በምን ያህል ጊዜ ነው?

---

**Employment First** ሃገር አቀፍ ንቅናቄ ሲሆን መሰረት ያደረገው ዓላማም ከፍተኛ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች ጨምሮ ሁሉም ሰዎች በውድድር ላይ ለተመሰረተና ማህበረሰብ አቀፍ ለሆነ የስራ ቅጥር ብቁ ናቸው የሚል ነው። Employment First የስርዓት ለውጦች ጥረቶች ማዕቀፍ ነው። ጅማሮው ተጠባቂ ሁኔታዎችን ከፍ ማድረግ፣ የተሻሉ አሰራሮችን መተግበርና ፖሊሲዎችን ከክፍያ መመለሻ መዋቅሮች ጋር በማጣጣም ለሁሉም ሰው ውድድር ያለበትና የተቀናጀ የስራ ዕድል መፍጠርን ያበረታታል።

በፌብሩዋሪ 2012 ላይ፣ የቨርጂኒያ ሴኔት የጋራ ውሳኔ ቁ. 127 በማሳለፍ በ Commonwealth ውስጥ የመደበኛ ቅጥር የመጀመሪያ ፖሊሲን አወጣ። በአጠቃላዩ የሰራተኛ ሐይል መካከል የስራ ቅጥር ወጪያቸው በመንግስት ከሚሸፈኑ ስርዓቶች እገዛ ለሚያገኙ አካል ጉዳተኛ የቨርጂኒያ ነዋሪዎች ተቀዳሚውና የተሻለ አማራጭ ነው።

**የስራ ቅጥርና የገንዘብ ድጋፍ ምንጮች ሞዴሎች**
በአሁኑ ጊዜ፣ ለአካል ጉዳተኞች የሚሰጡ የስራ ቅጥርና የቀን የእንክብካቤ አገልግሎቶች ከታች በተገለጹት የተለያዩ ሞዴሎች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ገጽ 51 ላይ ያለው ሰንጠረዥ ለተለያዩ የስራ ቅጥር ድርጅቶች ጥቅም ላይ የዋሉ የአገልግሎት ሞዴሎችን ዓይነትና የገንዘብ ምንጮቻቸውን ያሳያል። ይሁን እንጂ፣ በ Employment First ሕግ መሰረት ምንጊዜም የመጀመሪያ አማራጭ መሆን ያለበት አካል ጉዳተኞችን በተቀናጀ ማዕቀፍ ውስጥ በማህበረሰብ *ውድድር ያለበት የስራ ቅጥር በአነስተኛ ወይም ከፍተኛ ደመወዝ* መመደብ ነው።

**የተደገፈ የስራ ቅጥር በሁለት ሞዴሎች ውስጥ ይወድቃል:**

***ግለሰባዊ የሚደገፍ የስራ ቅጥር*** ማለት ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜም የስራ አሰልጣኝ ለግለሰቡ አንድ ለአንድ የሚሰጠው ድጋፍ ነው፤ ድጋፍ የሚሰጠው ግለሰብም አብዛኛውን ጊዜ በስራ ቦታ ላይ ራሱን ችሎ የሚያሳልፍ ነው።

**የቡድን የሚደገፍ የስራ ቅጥር** ማለት ቁጥራቸው ስምንት ወይም ከዚያ በታች ለሆኑ አካል ጉዳተኞች በሰራተኞች የሚሰጥ ተከታታይ ድጋፍ ሲሆን ሰራተኞቹም ከሃገር ውስጥ ኩባንያ ጋር ኮንትራት ያላቸው ወይም በማህበረሰቡ የተለያዩ ቦታዎች ተንቀሳቅሰው የሚሰሩ ሰራተኞች ናቸው።

** በ Northern Virginia አካባቢ የሚገኙ በርካታ የስራ ቅጥር አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ከፌዴራል መንግስት ጋር የ AbilityOne ኮንትራቶች አላቸው። ለተጨማሪ መረጃ፣ ይህን ይጎብኙ: www.abilityone.gov። የ AbilityOne ፕሮግራም ለዓይነ ስውራን ወይም ሌሎች ከባድ አካል ጉዳቶች ላለባቸው ሰዎች የስራ ቅጥርና የስልጠና ዕድሎችን በመፍጠር ይበልጥ ምርታማና ራሱን የቻለ ሕይወት እንዲመሩ ያስችላቸዋል። ይህን የሚያደርግበት ተቀዳሚ መንገድ መንግስታዊ ድርጅቶች የመረጡ ምርቶችና አገልግሎቶችን እንዲህ ዓይነት ግለሰቦችን ከሚቀጥሩ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች እንዲገዙ በማድረግ ነው።

## የስራ ፍለጋ እና የስልጠና ግብዓቶች

### Workforce Innovation and Opportunity Act (WIOA)

ይህ በሰራተኛ ሚኒስቴር ስፖንሰር የሚደረግ የፌዴራል የስራ ስልጠና ፕሮግራም ነው። WIOA One Stop Centers ኔትወርክ በመጠቀም አሰሪዎችና ስራ ፈላጊዎች ነጻ የስራ ቅጥርና የስልጠና አገልግሎቶች ተደራሽነትን እንዲያገኙ ያደርጋል። WIOA ሰራተኞች የስራ ዘመናቸውን ለማስተዳደር እንዲችሉና አሰሪዎችም የሰለጠኑ ሰራተኞችን እንዲያገኙ የሚያግዙ መሳሪያዎችን ያቀርባል። ተቀዳሚው ግብ የስራ ቅጥር፣ ስራን ይዞ የመቆየት ዕድል፣ ገቢዎችና የሙያ ክህሎቶችን በሁሉም ቀጣሪዎችና አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ በስራ ፈላጊዎች ዘንድ መጨመር ነው። በአካባቢዎ የሚገኝ One Stop Center ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ: http://www.elevatevirginia.org/career-seekers/one-stop-centers/

**የፌርፋክስ ካውንቲ One Stop የክህሎት ምንጭ ማዕከላት**
በ Northern Virginia ውስጥ የሚገኙ ስራ ፈላጊዎችና አሰሪዎች ሁሉን አቀፍ የሆነ የስራ ቅጥርና የስልጠና አገልግሎቶች ስርዓት ያላቸው ሲሆን ሐብቶች የሚቀርቡትና የሚቀናጁት በ one-stop የስራ ቅጥር የመረጃ ማዕከላት፣ ወይም በአካባቢው አጠራር SkillSource Centers በሚባሉት በኩል ነው። አገልግሎቶች ከክፍያ ነጻ የሚቀርቡ ሲሆን እነዚህንም ያካትታሉ፡ ግለ ታሪክ የመጻፍና ለቃለ መጠይቅ መዘጋጃ ወርክሾፖች፣ የስራ ዘመን ስልጠና፣ መሰረታዊ የስራ ቅጥር ምዘናዎች፣ ለስራ ፍለጋ የሚሆኑ ኮምፒዩተሮች፣ ስልኮች፣ ኮፒ ማሽኖችና ኢንተርኔት የማግኘት ዕድል፣ የስራ ጥቆማ ድጋፍና ቀጣይነት ያለው የደንበኞች ድጋፍ።
www.fairfaxcounty.gov/dfs/ss/employtraining.htm

ፌርፋክስ: (703) 324-7280
አናንዳሌ: (703) 533-5400
አሌክሳንድሪያ: (703) 704-6286
ሬስተን: (703) 787-4974
ስለእነዚህ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይመልከቱ: http://www.myskillsource.org

SkillSource ወደ Work Program የሚያስገባ ትኬት ሲሆን ይህ ፕሮግራምም የማሕበራዊ ዋስትና ጥቅማ ጥቅሞችን ለሚያገኙ አካል ጉዳተኞች ስራ እንዲያገኙ የሚያግዝ ነው። ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል ሁሉን አቀፍ ምዘናዎች፣ የግለሰባዊ የስራ ቅጥር ዕቅዶች ዝግጅት፣ የምክር አገልግሎት፣ የስራ ዘመን ዕቅድ አወጣጥና ከስራ ጋር የተያያዙ የስልጠና ዕድሎችን ተደራሽ ማድረግ ይገኙበታል። (703) 752-1606 ወይም MyTicket@myskillsource.org

**Hire Autism**
www.hireautism.org
በ Organization for Autism Research (OAR) የተመሰረተ ነው። ይህ ድረ ገጽ በኦቲዝም ስፔክትረም ውስጥ ላሉ ግለሰቦች የስራ ሰሌዳ፣ ለአካባቢያዊ የስራ ዕድሎች ቀጥተኛ ተደራሽነት መፍጠር፣ ፕሮፋይል ማደራጀና ለስራ ቦታ አጋዥ የሆኑ ግብዓቶችን ያቀርባል።

## የእንክብካቤ ድጋፍ አገልግሎቶች

እነዚህ አገልግሎቶች ትርጉም ያለው የእንክብካቤ ተግባራትን የሚያቀርብ ሲሆን ክፍያ የሚያስገኝ የስራ ቅጥርን አያካትትም። ተግባራቱ የሚቀርቡት በአነስተኛ ቡድን ወይም አንድ ለአንድ በሆነ አቀማመጥ ነው።
ትኩረት የሚደረገው አካል ጉዳተኞች በአብዛኛው ጉዳት አልባዎች በሚሳተፉባቸው የማህበረሰብ ተግባራት ውስጥ የሚኖራቸውን ተሳትፎ መደገፍ ላይ ነው። በዚህ ውስጥ ከሚካተቱ ተግባራት መካከል እንደ መዝናኛ፣ ማህበራዊ ክህሎቶችን ማሻሻል፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚተገበር የዕለታዊ ኑሮ ተግባራትና የበጎ ፈቃድ ስራ ልምድ የመሳሰሉ አጠቃላይ የማህበረሰብ ቅንጅት ተግባራት ይገኙበታል። ይህ አማራጭ በዕለት ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ ያለው የዕለታዊ ኑሮ ድጋፍ ፍላጎቶች ላላቸውና የሙያ ክህሎቶችን ለመደገፍ ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች ያገለግላል።

ግለሰቡ ስራ ለመስራት ካልፈለገ፣ Day Support Services በቅድሚያ በ DARS በኩል ሳያልፉ በ waiver ወይም በ CSB አማካይነት ሊተገበሩ ይችላሉ። የዕለታዊ እንክብካቤ ድጋፍ አገልግሎቶች ከስራ ቅጥር ጋር የተያያዘ ባለመሆኑ ከ DARS የገንዘብ ድጋፍ አያገኝም። የስራ ቅጥርና የእንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ዝርዝር በቀጣዮቹ ገጾች ላይ ከሚገኘው ቻርት ይመልከቱ።

**የስራ ቅጥርና የዕለት ድጋፍ አገልግሎቶች ሰጪ ድርጅቶች**

| **አገልግሎት ሰጪ** | **ድረ ገጽ** | **የሚሰጡ አገልግሎቶች** | **የገንዘብ ምንጭ** |
|---|---|---|---|
| The Arc Greater Prince William/INSIGHT<br>13505 Hillendale Drive<br>Woodbridge, VA 22193<br>(703) 670-4800 | www.arcgpw.org | የተደገፈ የስራ ቅጥር<br>የዕለት ድጋፍ አገልግሎቶች | Waiver<br>CSB<br>DARS |
| Best Buddies Capital Region<br>131 East Broad Street, Suite 205<br>Falls Church, VA 22046<br>(703)533-9420 | www.bestbuddies.org./capitalregion | ግለሰባዊ የሚደገፍ የስራ ቅጥር | DARS<br>CSB<br>የግል ከፋይ |
| Career Support Systems<br>3801 Westerre Parkway, Suite C<br>Richmond, VA 23233<br>517-354-8458<br>*** ዋና መ/ቤቱ Richmond ውስጥ ቢሆንም፣ በመላው Northern VA ውስጥ የስራ ቅጥር ስፔሻሊስቶች አሉት* | www.careersupport.net | ግለሰባዊ የሚደገፍ የስራ ቅጥር<br>የቡድን የሚደገፍ የስራ ቅጥር<br>ራስን ችሎ የመኖር ክህሎቶች ስልጠና | DARS<br>Waiver |
| Chimes, Inc.<br>3951 Pender Drive, #120<br>Fairfax, VA 22030<br>(703) 267-6558 | www.chimes.org | የዕለት ድጋፍ አገልግሎቶች | Waiver<br>CSB<br>DARS<br>የግል ከፋዮች |
| The Choice Group<br>4807 Radford Ave. #106<br>Richmond, VA 23230<br>(804)278-9151<br>*** ዋና መ/ቤቱ Richmond ውስጥ ቢሆንም፣ በመላው Northern VA ውስጥ የስራ ቅጥር ስፔሻሊስቶች አሉት* | www.thechoicegroup.com | ግለሰባዊ የሚደገፍ የስራ ቅጥር | Waiver<br>DARS<br>CSB<br>የግል ከፋዮች |
| Community Visions, LLC<br>3460 Commission Court,<br>Suite 101<br>Woodbridge, VA 22192<br><br>Charming Concepts<br>Workhouse Arts Center<br>9601 Ox Road<br>Lorton, VA 22079 | www.comvsllc.net | ቅድመ ሙያ አገልግሎቶች<br>የእንክብካቤ አገልግሎቶች | Waiver<br>CSB<br>DARS<br>የግል ከፋዮች |
| Didlake, Inc.<br>8641 Breeden Ave.<br>Manassas, VA 20110<br>(703) 361-4195 | www.didlake.org | የሚደገፍ የስራ ቅጥር<br>የእንክብካቤ አገልግሎቶች | Waiver<br>CSB<br>DARS<br>የግል ከፋዮች |

**የስራ ቅጥርና የጎልማሶች እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች**

| **አገልግሎት አቅራቢ** | **ድረ ገጽ** | **የሚሰጡ አገልግሎቶች** | **የገንዘብ ምንጮች** |
|---|---|---|---|
| Every Citizen Has Opportunities (ECHO)<br>71 Lawson Road, SE<br>Leesburg, VA 20177<br>(703) 779-2100 | www.echoworks.org | የሚደገፍ የስራ ቅጥር<br>የጎልማሶች እንክብካቤ አገልግሎት | Waiver<br>CSB<br>DARS<br>የግል ከፋዮች |
| (JSSA) Jewish Social Service Agency<br>3025 Hamaker Ct, Suite 450<br>Fairfax, VA 22030<br>(703)204-9100 | https://www.jssa.org/get-help/specialized-employment/ | የሚደገፍ የስራ ቅጥር<br>የስራ ዘመን ምዘና | የግል ከፋዮች |
| Job Discovery, Inc.<br>10345 Democracy Lane<br>Fairfax, VA 22030<br>(703) 385-0041 | www.jobdiscovery.org | የሚደገፍ የስራ ቅጥር<br>የጎልማሶች እንክብካቤ አገልግሎት | Waiver<br>CSB<br>DARS<br>የግል ከፋዮች |
| Melwood<br>750 South 23rd Street<br>Arlington, VA 22202<br>(703) 521-4441 | www.melwood.org | የሚደገፍ የስራ ቅጥር<br>የጎልማሶች እንክብካቤ አገልግሎቶች<br>የስራ ዘመን ዝግጁነት | Waiver<br>CSB<br>DARS<br>የግል ከፋዮች |
| MVLE, Inc.<br>7420 Fullerton Road Suite 110<br>Springfield, VA 22153<br>(703) 569-3900 | www.mvle.org | የሚደገፍ የስራ ቅጥር<br>የጎልማሶች እንክብካቤ አገልግሎቶች | Waiver<br>CSB<br>DARS |
| Outstanding Possibilities Revealed<br>3022 Javier Road, Suite 130<br>Fairfax, VA 22031<br>(202)888-6533 | www.oprservices.org | የሚደገፍ የስራ ቅጥር | DARS<br>የግል ከፋዮች |
| ServiceSource, Inc.<br>10467 White Granite Drive<br>Oakton, VA 22124<br>(703)461-6000 | www.servicesource.org | የሚደገፍ የስራ ቅጥር<br>የጎልማሶች እንክብካቤ አገልግሎቶች<br>የአጋዥ ቴክኖሎጂ ማጣሪያ<br>የስራ ዘመን ማዕከል | Waiver<br>CSB<br>DARS<br>የግል ከፋዮች |
| Saint Coletta of Greater Washington<br>207 S. Peyton Street<br>Alexandria, VA 22314<br>571-438-6940 | www.stcoletta.org | የሚደገፍ የስራ ቅጥር<br>የጎልማሶች እንክብካቤ አገልግሎቶች<br>የኑሮ ክህሎቶች ስልጠና | Waiver<br>CSB<br>DARS<br>የግል ከፋዮች |
| St. John's Community Services, Inc.<br>7611 Little River Turnpike #404,<br>Annandale, VA 22003<br>(703) 914-2755 | www.sjcs.org | የሚደገፍ የስራ ቅጥር<br>የጎልማሶች እንክብካቤ አገልግሎቶች<br>የስነ ጥበብ አማራጮች | Waiver<br>CSB<br>DARS<br>የግል ከፋዮች |
| Work Opportunities Unlimited<br>11002 Veirs Mill Road, Wheaton, MD<br>(202)615-4467 ** *ዋና ማ/ቤቱ ሜሪላንድ (MD) ውስጥ ቢሆንም፣ በመላው Northern VA ውስጥ የስራ ቅጥር ስፔሻሊስቶች አሉት* | www.workopportunities.net | የሚደገፍ የስራ ቅጥር<br>የኑሮ ክህሎት ስልጠና | Waiver<br>DARS<br>CSB<br>የግል ከፋዮች |

## የልማዳዊ የስራ ቅጥርና የዕለት አገልግሎቶች አማራጮች

**በፌርፋክስ ካውንቲ ውስጥ ያሉ የራስ መር አገልግሎቶች**
የራስ መር (SD) አገልግሎቶች የአእምሮ አካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የልማዳዊ የድጋፍ ሞዴል አማራጭ ነው። በመጨረሻም የአገልግሎት ፍላጎቶች የመወሰን (ከግለሰቡ የ Community Services Board የድጋፍ አስተባባሪ እና ከተለያየ መስክ ከተውጣጣ ቡድን በሚገኝ ግብዓት)፣ የአገልግሎት የጊዜ መርሃ ግብርን የመለየትና ቀጥተኛ አገልግሎት አቅራቢዎችን የመመልመል፣ የመቅጠር፣ የማሰልጠን፣ የመቆጣጠር፣ የመክፈልና የመገምገም ኃላፊነቱ የግለሰቡ/ቤተሰቡ ነው። የ SD አገልግሎቶች:

- ግለሰባዊ የአገልግሎት አማራጮችና ዕቅዶችን ማሳደግና ማስፋት
- ለግለሰብ/ለቤተሰብ የሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ የበለጠ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ
- የአገልግሎቶችን ጊዜ አወጣጥና አቀባበል በተመለከተ የላቀ ተለዋዋጭነት እንዲኖር ማድረግ እና
- ከግለሰቡ ቤት አቅራቢያ ባለ ማህበረሰብ ውስጥ ሊሰጥ ይችላል።

የ SD አገልግሎቶች የ CSB የአገልግሎት ብቁነት መስፈርቶችን ለሚያሟሉና የዕለት ድጋፍ ወይም የስራ ቅጥር አገልግሎቶች የገንዘብ ድጋፍ በአሁኑ ጊዜ ለሚያገኙ ወይም እነዲቀበሉ ለተፈቀደላቸው የአእምሮ አካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ይቀርባሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ ከ Joel Friedman በስልክ ቁጥር (703)324-4433 ወይም joel.friedman@fairfaxcounty.gov ጋር ይነጋገሩ።

**SPARC Solutions (Specially Adapted Resource Clubs)**
ማህበረሰብ አቀፍ ትርጉም ያለው ቀን አጋጣሚዎችን ይፈጥራል። የክለብ ሃውስ ሞዴል የቀን ፕሮግራም ሲሆን ዕድሜያቸው ከ22 ዓመት በላይ የሆኑ አካል ጉዳተኛ ጎልማሶችን በሕይወት ክህሎቶች ማጎልበት፣ የስራ ፈጠራ ፕሮጀክቶችና እንደ ሙዚቃ እና የጥበብ ቴራፒዎችን በመሳሰሉ የማበልጸጊያ ተግባራት ድጋፍ ይሰጣል። ክለቦች በ Reston፣ McLean፣ Arlington፣ እና Fairfax ውስጥ ይገኛሉ። የክፍያው መጠን በወር $250-$750 የሚደርስ ሲሆን ይህም በሳምንት ውስጥ በነበረው የቆይታ መጠን ላይ የተመሰረተ ነው።

**SPARC Works**
ግለሰባዊ የስራ ቅጥር ስልጠናን ይሰጣል።

**SPARC C.A.N. (Continuing Education Advocacy Navigating the community)**
ለአንድ ዓመት በሳምንት 5 ቀን የሚሰጥና ራሳቸውን ችለው ለመኖርና ስራ ለመፈለግ ለሚፈልጉ ሰዎች የክህሎት ማስጠናት ድጋፍ የሚሰጥ ስርዓተ ትምህርት ነው።

እነዚህን ሁሉ ፕሮግራሞች በተመለከተ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ: www.sparcsolutions.org or contact Donna Goldbranson (703)338-6185 donna@sparcsolutions.org

**Adults with Disabilities Day Program (ADDP)**
ይህ ፕሮግራም በ McLean Bible Church ለ2ኛ ደረጃ ምሩቃን የተመቻቸ ሲሆን አገልግሎቱን የሚሰጡበት ቦታ Tyson እና Prince William ነው፣ የሚያተኩረውም በመንፈሳዊ መረጃ፣ ማንበብና መጻፍ፣ የሙያ ስልጠና፣ የግል እንክብካቤና ራስን መቻል፣ መዝናኛ፣ ማሕበራዊ ክህሎቶች፣ የጉዞ ስልጠና እና የማህበረሰብ ዳሰሳ እና ለራስ መሟገት ላይ ነው። በሳምንት ውስጥ በተመዘገቡባቸው ቀናት መሰረት የሚከፈል ወርሐዊ ክፍያ አለ። ፕሮግራሙ በሳምንት አምስት ቀን ከሰኞ እስከ አርብ ከ10am-3pm አገልግሎት ይሰጣል። ለተጨማሪ መረጃ፣ https://www.mcleanbible.org/connect/adults-disabilities-day-program-addp-mbc-tysons-prince-william?field_campus_tid=1

## ፈጠራ የተሞላባቸው የስራ ቅጥር ሞዴሎች

**Cameron's Coffee & Chocolates**
በ2013 ስራውን የጀመረው Every1 Can Work ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን Cameron's Coffee & Chocolates በተባለው የንግድ ድርጅቱ ውስጥ አካል ጉዳተኛ ሰራተኞችን ይቀጥራል። ሰራተኞች አሰልጣኝ መድቦላቸው ስለ ኪችን እና የኑሮ ክህሎቶች ይማራሉ።
www.every1canwork.com
9639 Fairfax Blvd., Fairfax, VA (703)278-2627

**Wildflour Bakery Chef-In-Training Program**
ስራውን በ2016 የጀመረ ሲሆን፣ ከ Fairfax-Falls Church CSB Employment and Day Services ጋር በመተባበርም ለ 26 ወራት የሚቆይ የምግብ ዝግጅት ክህሎትና የምግብ ደህንነት ስልጠና ይሰጣል። ለተጨማሪ መረጃ፣ Alberto Sangiorgio በ Wildflour Catering (703)263-1951 ያነጋግሩ።
https://wildflourcaterers.com/about-us/becoming-a-chef-2/

**Arlington Weaves**
ArlingtonWeaves, Etc የዕድገት አካል ጉዳት ያለባቸው ጎልማሶችን ቴክኒካዊና ማህበራዊ ክህሎቶችን በማስተማርና ራሳቸውን የሚችሉበትን ሁኔታ እንዲያሻሽሉ በማገዝ ድጋፍ ይሰጣል። ፕሮግራሙን የሚያንቀሳቅሰው ServiceSource ሲሆን ይህ ድርጅት ከ Arlington County Department of Human Services ጋር የገባው ኮንትራት አለው። ለተጨማሪ መረጃ፣ የ Arlington DD Services በስልክ ቁጥር 703-228-1700 ያነጋግሩ።

ስለ ስራ ቅጥር ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ቀጣዩን የ Arc of Northern Virginia የ Transition POINTS መምሪያ ያንብቡ: Entering the World of Work
https://thearcofnova.org/programs/transition/entering-world-work/

## የራስዎን የንግድ ስራ ለመጀመር ይፈልጋሉ?

ድረ ገጹ ከልማዳዊው የስራ ቅጥር ውጭ ለሚፈልጉ ሰዎች ሃሳቦችና ተጨማሪ የመረጃ ግብዓቶችን ይዘረዝራል
https://www.commercialcapitaltraining.com/business-resources/business-ideas/business-ideas-people-disabilities/

ገበያው ባለፉት ጥቂት አመታት ውስጥ ብዝሃነቱን ለማስፋት ችሎ ነበር። አካል ጉዳተኞች ሌሎችን ለማገዝ፣ ሕይወትን ይበልጥ ምቹ ለማድረግ፣ ወይም አንድ አስደሳችና አርኪ ነገርን እየሰሩ እያለ ከፍተኛ ገቢ የሚያመነጭ አዲስ አቅጣጫን ለመፍጠር በማሰብ አዳዲስ ቴከኖሎጂን እየተቀበሉና የንግድ ስራዎችን እየከፈቱ ነው። ፈቃድን ተከራይቶ ከመስራት እስከ ጀማሪ ድርጅቶች ድረስ፣ አካል ጉዳተኞች በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ቁጥራቸው እያደገ የመጣ የንግድ ስራ ፈጣሪዎችን ቀላል የማይባል ድርሻ ይይዛሉ። የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማየትና ለአካል ጉዳተኞች ዝግጁ የሆኑ አንዳንድ ምርጥ የንግድ ስራ ዕድሎች ለማየት ድረ ገጹን ይጎብኙ።

# ቅጥያ 12፡ ዘና ማለት

***መንግስታዊ የቴራፒ ነክ መዝናኛ ድርጅቶች***
*ሶስቱም አካባቢዎች ለአካል ጉዳተኞች የመዝናኛና ዘና የማለት ዕድሎችን የሚፈጥሩ ቴራፒ ነክ የመዝናኛ ቢሮዎች አላቸው። ለወጣት ጎልማሶች ከሚቀርቡ አገልግሎቶች መካከል ከሁኔታ ጋር የተዋደዱ የክፍል ትምህርቶች፣ ማህበራዊ ክበባትና የበጋ ካምፖች ይገኙበታል። እርስዎ ለአካባቢው አዲስ ከሆኑ፣ ሰራተኞች የልጅዎን ፍላጎቶች እንዲረዱ ለማስቻል ምዘና እንዲደረግልዎ መጠየቅ ይችላሉ።*

**City of Alexandria**
Alexandria Recreation, Parks & Cultural Activities, Therapeutic
https://www.alexandriava.gov/recreation/info/default.aspx?id=45758
703-746-5422

**Arlington County**
Department of Parks and Recreation
Therapeutic Recreation Office
https://parks.arlingtonva.us/therapeutic-recreation/
703-228-4740

**Fairfax County**
Fairfax Therapeutic Recreation Services
www.fairfaxcounty.gov/ncs/trs
703-324-5532

*በተጨማሪም፣ የ FCPS የወላጆች መረጃ ማዕከልን ይመልከቱ*
Adapted Sports and Recreation
http://www2.fcps.edu/dss/osp/prc/documents/AdaptedSportsRecreationGuide2016.pdf

***የግል አገልግሎት አቅራቢዎች***
**Adaptive Learn-to-Skate** Kettler Iceplex Adaptive Learning I and II *ዘወትር ቅዳሜ ማለዳ ይሰጣል። በስልክ ቁጥር* 571-224-0555 *ይደውሉ፣* LTS@kettlercapitalsiceplex.com*፣ ወይም ይህን ይጎብኙ፡* http://kettlercapitals.pointstreaksites.com.

**Adaptive Martial Arts** (4-18) Jhoon Rhee Tae Kwon Do *ከጀማሪ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ስልጠና የሚሰጥ ሲሆን ይህም የእጅና እግር አጠቃቀም ክህሎት፣ በቅንጅት የማሰራት ችሎታ፣ ትኩረትና ራስን መቆጣጠርን የሚያሻሽል ነው። ለ* Anna Rome *በስልክ ቁጥር* 703-532-7433 *በመደወል፣ ይህን በመጎብኘት* www.adaptivetkd.com*፣ ወይም ኢሜይል በመላክ* adaptivetkd@tkdlifeskills.com *ተጨማሪ መረጃ ያግኙ።*

**ArtStream** *ለአካል ጉዳተኛ ልጆችና ጎልማሶች የድራማና የውዝዋዜ ትምህርት የሚሰጥ ነው። በ* Silver Spring፣ MD፣ *እና* Arlington፣ VA *ትምህርቱ ይሰጣል።* http://www.art-stream.org *ወይም በ*301-565-4567 *ይደውሉ*

**Capernaum**፡ Young Life *የተባለው ከሌሎች ጋር ሕብረትን የሚፈጥር የክርስቲያን ወጣቶች ድርጅት የአውትሪች ተልዕኮ የሆነው* Capernaum *ዕድሜያቸው ከ*14-22 *ዓመት ለሆናቸውና አካላዊና አእምሯዊ አካል ጉዳት ላለባቸው ታዳጊ ወጣቶች የበካ ካምፕና በወር ሁለት ጊዜ ማህበራዊ ስብሰባዎችን ያዘጋጃል።* Arlington & McLean: caleb.younglife@gmail.com
Central Fairfax: wonkamas@gmail.com
Northwest Fairfax: younglifemike@gmail.com

**Cool Aspies Club of Northern Virginia** Asperger's Syndrome *እና* HF autism *ላለባቸው ወጣት ጎልማሶች ማህበራዊ ክበብ በኢሜይል ይላኩ* alexaspies@gmail.com *ወይም* Facebook *ላይ ይጎብኙ*
http://www.facebook.com/pages/Cool-Aspies/329777750424551

**Easter Seals of Northern Virginia** Arlington *ውስጥ በሚገኘው* Walter Reed Community Center *ቢያንስ በሳምንት ለ*2 *ቀን የሚዘጋጅ የመዝናኛ ቀን ፕሮግራም (ዕድሜያቸው ከ*18 *ዓመት በላይ ለሆናቸው ጎልማሶች ብቻ)።* 703-228-0964

**Expressive Therapeutic Movement**። *ዕድሜያቸው ከ*13 *ዓመት በላይ ለሆኑና አእምሯዊ አካል ጉዳት ላለባቸው ልጆች የሚሰጡ ትምህርቶች። ዮጋ፣ የአተነፋፈስ ልምምዶች፣ ስልታዊ ሙዚቃ፣ እና የሰውነት አካልን በተመለከተ ግንዛቤ መፍጠር ጥንካሬን፣ ከሁኔታ ጋር መለዋወጥን፣ መረጋጋትን፣ የእጅና እግር ጣምራ እንቅስቃሴና ራስን ማብቃትን ለማሳደግ ያገለግላሉ።* Springfield & Herndon, 703-218-0751 etm.movements@gmail.com

**Jewish Social Service Agency (JSSA)** *ለወጣት ጎልማሶች ወርክሾፖችና ቡድኖችን ያቀርባል።*
https://www.jssa.org/service/individuals-with-special-needs/

**Jewish Community Center of Northern Virginia (JCCNV)** *ቡድኖችና ማህበራዊ ክበባትን ያቀርባል።*
http://www.jccnv.org/specialneeds/special-needs/

**Lifechanging Fitness** (*በሁሉም ዕድሜ ላይ ለሚገኙ*) *ለአካል ጉዳተኞች በቡድንና በተናጣል የሚሰጡ የአካል ብቃት ትምህርቶች። ፕሮግራሙ ስብ ለማቃጠል፣ ለጥንካሬና የስፖርት ክህሎቶችንም ለመማር ሊያግዝ ይችላል። ድረ ገጻቸውን ይጎብኙ* www.lifechangingfitness.org *ወይም ለ* Ricardo Cunningham *በስልክ ቁጥር* 703-909-7971 *ይደውሉ።*

**Little League Baseball/Challenger League**፡
*ዕድሜ* 5-22 *ዓመት። ይህ በበጎ ፈቃደኞች የሚመራ ፕሮግራም ኳስ ለመጫወት ዕድል ይፈጥራል። ተጫዋቾች ከ*1 *የዋና ቡድን ተጨዋቾች ጋር*

ይጣመሩና እርሱም እንደ ቡድን አጋር ይሆናል። ወቅቱ በፀደይና በበልግ ነው። 703-351-5111 ወይም ይህን ይጎብኙ: www.arlingtonlittleleague.org

**Parents of Autistic Children (POAC)**
አሁን ያሉትን የስፖርትና የመዝናኛ ዕድሎችን ዝርዝር የያዘ ነው። https://poac-nova.org/wp-content/uploads/2018/02/Adapted-sports-and-rec-list-2018.pdf

**Special Olympics**። ዕድሜያቸው ከ 8 ዓመት
በላይ ለሆነና አእምሯዊ አካል ጉዳት ላለባቸው ልጆች በተለያዩ የኦሎምፒክ ዓይነት ስፖርቶች እንዲሰለጥኑና እንዲወዳደሩ ዕድል ይሰጣል። የ Northern VA Special Olympics በስልክ ቁጥር 703-359-4301 ያነጋግሩ ወይም ይህን ይጎብኙ: www.novasova.org/contact.html

**Springfield Challenger Baseball**
ልዩ ፍላጎት ላላቸውና ዕድሜያቸው ከ4-18 ለሆኑ ልጆች፣ እስካሁን በት/ቤቶች ተመዝግበው ለሚገኙ እስከ 22 ዓመት ድረስ ላሉ ወጣቶችና ለጎልማሶች የቤዝቦል ሶስት ዲቪዚዮኖችን ያቀርባል። www.springfieldchllenger.org

**TOPSoccer** ዕድሜ 4-19 ዓመት። ይህ በበጎ ፈቃደኞች የሚመራ የክህሎት ማሳደጊያ ፕሮግራም ነው። ወቅቱ በልግ፣ ክረምትና ፀደይ ነው። Alexandria ውስጥ Bill Dwyer ጋር ይነጋገሩ፣ wmdwyerprop@aol.com፣ 703-684-5425 ወይም http://www.alexandria-soccer.com/tops.htm። Arlington ውስጥ፣
ይህን ይጎብኙ: www.arlingtonsoccer.com/clubs/[g1] topsoccer። ወይም Joe Lerner በስልክ ቁጥር 703-522-5866 (የቤት)፤ 703-395-7379 (ተንቀሳቃሽ ስልክ) ያነጋግሩ።

በ Burke፣ Chantilly፣ McLean እና Reston የሚገኘውን TOPSoccer ለማየት የ TOPSoccer ድረ ገጽን ይጎብኙ http://www.vysa.com/programs/34617/34707.html

**የአጭር ጊዜ ፋታ ማግኛ እንክብካቤ**
አልፎ አልፎ ለሚሰጥና ለአጭር ጊዜ የፋታ ማግኛ እንክብካቤ:
**Jill's House**
www.jillshouse.org
9011 Leesburg Pike, Vienna, VA 22182
703-639-5660
በ Greater Washington DC አካባቢ ለሚገኙ አካል ጉዳተኛ ልጆች (ዕድሜያቸው ከ6 እስከ 17 ዓመት ለሆነ) ፋታ ማግኛ እንክብካቤ ይሰጣል።

**Camp Baker**
http://www.richmondarc.org/services/developmental-services/camp-baker-services/
3600 Saunders Avenue, Richmond, VA 23227
የግንኙነት አድራሻ (804) 748-4789
ወይም CampBaker@RichmondARC.org
ከ 6 ዓመት ጀምሮ እስከ ጉልምስና ዕድሜ ድረስ የፋታ ማግኛ እንክብካቤና የበጋ
ካምፕ አገልግሎቶች ይሰጣል።

**Hartwood Foundation**
https://www.hartwoodfoundation.com/programs/
የግንኙነት አድራሻ info@hartwoodfoundation.com 703-273-0939
3702 Pender Dr. Suite 410
Fairfax, VA 22303
የአእምሮ አካል ጉዳት ላለባቸው ልጆችና ጎልማሶች ፋታ ማግኛ የእንክብካቤ አገልግሎቶችን ይሰጣል።

**Summer Camps**
የአካባቢው የቴራፒ መዝናኛ ኤጄንሲዎች ለአካል ጉዳተኛ ወጣቶች የበጋ ፕሮግራሞችን ያቀርባሉ። በተጨማሪም፣ የሚከተሉትን አገልግሎት ሰጪዎች ይመልከቱ፡

**Parent Educational Advocacy Training Center (PEATC)**
የአካልና የዕድገት አካል ጉዳት ላለባቸው ግለሰቦች Virginia ውስጥ የሚቀርቡ የበጋ ካምፖች/ፕሮግራሞች ዝርዝር
**http://www.peatc.org/peatc.cgim?template=news_and_events.template**

**Jewish Community Center Camp JCC**
http://www.jccgw.org/camp-youth-teens/camp-jcc/

**Summit Camp**
www.summitcamp.com
ትኩረት የመስጠትና የማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ችግር ላለባቸው አፍላ ታዳጊዎችና ወጣት ጎልማሶች የሚቀርቡ ከቤት ውጭ ያሉ የመቆያ፣ የጉዞና የቅዳሜና እሁድን ማሳለፊያ ካምፖች

**Young Life Capernaum Camp**
ዕድሜያቸው እስከ 23 ዓመት ለሆናቸው ልጆች፣ አፍላ ወጣቶችና ወጣት ጎልማሶች በ Rockbridge in Goshen፣ VA ውስጥ የሚዘጋጅ የአምስት ቀን ካምፕ።

## ቅጥያ 13፡ ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስ

አካል ጉዳተኞች ከጉዞ ስልጠና
እና በዋሽንግተን አካባቢ በዝቅተኛ ዋጋ ከሚደረግ የአውቶብስና የምድር ውስጥ ባቡር ጉዞ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። የታክሲ ኩባንያዎችም ለአካል ጉዳተኞች የዋጋ ቅናሽና ልዩ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ።

***መንጃ ፈቃድ ያልሆነ የመታወቂያ ካርድ***
ለተማሪዎች፣ ለአካል ጉዳተኞች ወይም ለአረጋውያን የትራንስፖርት ዋጋ ቅናሽ የሚሰጡ በርካታ ፕሮግራሞች የዕድሜ ማስረጃ እና/ወይም የፎቶ መታወቂያ የሚጠይቁ በመሆኑ፣ የመጀመሪያው ብልህ እርምጃ የሚሆነው መንጃ ፈቃድ ያልሆነ የመታወቂያ ካርድ ከ Virginia Department of Motor Vehicles (DMV) ማግኘት ነው። (ይህ የመታወቂያ ካርድ የአየር ጉዞ በሚያደርጉበት ወቅትም ፎቶ ያለበት መታወቂያ ካርድ ሆኖ ያገለግላል)።

የመታወቂያ ካርድ ለማግኘት የ Virginia ነዋሪ መሆን አለብዎት። እነዚህ ካርዶች የዕድሜ ገደብ የሌላቸው ሲሆን የተማሪ ፈቃድ ወይም የመንጃ ፈቃድ ለሌለው ጎልማሳ ወይም ልጅ የሚሰጡ ናቸው።

የጎልማሳ መታወቂያ ካርድ አገልግሎት ዘመኑ የሚያበቃው እርስዎ በተወለዱበት ወር መጨረሻ ላይ ነው፤ ዕድሜዎም በ 5 የሚካፈል መሆን አለበት፤ ለምሳሌ 20፣ 25፣ 30፣ ወዘተ… የልጅ መታወቂያ ካርድ አገልግሎቱ የሚያበቃው የልጁ 16ኛ ዓመት ልደት ላይ ነው።

አንድ ደንበኛ ወደ DMV ለሚደረግ ጉብኝት ዝግጅት ለማድረግ የሚያስፈልጉት መረጃዎች በሙሉ ከ DMV ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል http://dmv.state.va.us/webdoc/citizen/legal_presqa.asp ወይም ለኤጀንሲው ከክፍያ ነጻ ስልክ ቁጥር at 1-866-DMV-LINE መደወል ይቻላል።

***የጉዞ ስልጠና***
ራስን የመቻል ሒደት ዋነኛ አካል አንድ ሰው የሕዝብ ትራንስፖርት ተጠቅሞ ወደ ስራና ማህበራዊ ጉዳዮች መንቀሳቀስ መቻሉ ነው። The ENDependence Center of Northern Virginia በ Washington አካባቢ አውቶብስና የምድር ውስጥ ባቡር መንገዶች ላይ ለአካል ጉዳተኞች ***ነጻ*** የጉዞ ስልጠና ይሰጣል። www.ecnv.org 2300 Clarendon Blvd., Arlington, VA. በስልክ ቁጥር (703) 525-3268 ይደውሉ።

***የሜትሮ የአካል ጉዳተኝነት መታወቂያ ካርድ***
በ Washington አካባቢ የሚገኙ ሁሉም የስልጣን አካላት ዝቅተኛ የትራንስፖርት ታሪፍ የሚሰጡ ቢሆንም፣ በቅድሚያ ግን ነጻ የሜትሮ የአካል ጉዳተኝነት መታወቂያ ካርድ ማግኘት አለብዎት። የማመልከቻ ቅጽ መሙላትና የአካል ጉዳትዎ በጤና እንክብካቤ ባለሙያ መረጋገጥ ያስፈልገዋል። በስልክ ቁጥር 202-962-2700 ይደውሉ ወይም የማመልከቻ ቅጹን ከዚህ ያውርዱ፡ http://www.wmata.com/accessibility/doc/Reduced_Fare_Application.pdf
የሜትሮ የአካል ጉዳተኝነት መታወቂያ ካርድን መጠቀም የሚቻለው በዲስትሪክቱ ውስጥ ባሉ የሜትሮ አውቶብሶች ላይ እና Arlington ውስጥ ደግሞ ART ላይ ነው። CUE፣ Fairfax Connector፣ RideOn፣ TheBus፣ VRE እና MARC ይቀበሉታል።

***የዋጋ ቅናሽ ያለው ታሪፍ ካርድ/የአውቶብስ መግቢያ እና/ወይም SmarTrip ካርድ***
የታሪፍ ቅናሽ ለመጠቀም አንዱ አማራጭ ዋጋው ዝቅተኛ የሆነ የአውቶብስ መግቢያ ወይም farecard (ሜትሮ) ነው። እነዚህ ካርዶች የሚሸጡት በ Giant እና Safeway መደብሮች፣ በሜትሮ የሽያጭ ቢሮዎችና የትራንዚት መደብሮች ነው። የሜትሮ አካል ጉዳተኝነት ካርድዎንና ፎቶ ያለበት የመታወቂያ ካርድዎን ማሳየት ይኖርብዎታል።

የሜትሮ አካል ጉዳተኝነት ካርድዎን ተጠቅመው ለዝቅተኛ ታሪፍ የተመሰጠረውን SmarTrip ካርድ ይግዙ።
SmarTrip ካርዶችን ኦንላይን ለመግዛት ወደ www.MetroOpensDoors.com ገብተው "Fares" የሚለው ስር ጠቅ ያድርጉ። (የተመዘገበ የሜትሮ የአካል ጉዳተኝነት መታወቂያ ካርድ ሊኖርዎትና ዋና ዋና ክሬዲት ካርድ ሊጠቀሙ ይገባል)፤ በሜትሮ የሽያጭ ቢሮዎች፤ እና የትራንዚት መደብሮች (ዝርዝሩን በዚህ ቅጥያ መጨረሻ ላይ ይመልከቱ)። በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም የሕዝብ የትራንዚት አገልግሎት SmarTrip ይጠቀማል፤ *ይህ ግን* The Bus፣ OmniRide፣ OmniLink፣ MARC እና VRE አይጨምርም።

የ SmarTrip ካርድዎን ማስመዝገብዎ በጣም የሚመከር ነው። ካርድዎ ከጠፋብዎት፣ $5 ከፍለው ምትክ ማግኘት የሚችሉ ሲሆን ይህም ክፍያ ካርዱ በጠፋበት ወቅት የነበረውን ዋጋ የሚጨምር ነው።

የ SmarTrip ካርድዎን በማንኛውም የሜትሮ ጣቢያ፣ በ farecard ማሽኖች ወይም Metrobus ላይ መሙላት ይችላሉ።

***የሕዝብ ትራንስፖርት መጠቀም***
አገልግሎት ስለሚሰጡ የጉዞ መስመሮች መረጃ ለማግኘት ጥሩ መነሻ ቦታ የሚሆነው CommuterPage.com ሲሆን ወደ Virginia እና Maryland የአውቶብስና የባቡር አገልግሎቶች የሚያመራ ማስፈንጠሪያም አለው። ይህን ይጎብኙ፡ www.comuterpage.com

አሌክሳንደሪያ ውስጥ፣ ይህን ይጎብኙ፡ www.dashbus.com
አርሊንግተን ውስጥ፣ ይህን ይጎብኙ፡ www.arlingtontransit.com
ፌር ፋክስ ውስጥ፣ ይህን ይጎብኙ፡ www.fairfaxcounty.gov/connector/
ፌርፋክስ ከተማ ውስጥ፣ ይህን ይጎብኙ፡ www.cuebus.org

***የአካል ጉዳተኞች ማስታወቂያ ሰሌዳ/የሰሌዳ ቁጥር***
Virginia ውስጥ የአካል ጉዳተኞች የመኪና ማቆሚያ ሰሌዳ ወይም የተሸከርካሪ ሰሌዳ ለማግኘት MED-10 ቅጽ መሙላት አለብዎ። ቅጹን ከ Department of Motor Vehicles (DMV) መውሰድ ይችላሉ ወይም ከቀጣዩ ድረ ገጻቸው ማግኘት ይችላሉ http://dmv.state.va.us። ቅጹ መሞላት ያለበት በሐኪም ነው።
የተሞላውን ቅጽ ለ DMV ይመልሱ።
የማስታወቂያ ሰሌዳ ወይም የተሸከርካሪ ሰሌዳ ወይም ሁለቱንም ማግኘት ይችላሉ። የማስታወቂያ ሰሌዳን እርስዎ ወደሚነዱት ወይም ወደተሳፈሩበት የትኛውም ተሽከርካሪ ማዛወር ስለሚችሉ እንደሁኔታው መቀያየር ያስችልዎታል።
ክፍያ ከፍለው የማስታወቂያ ሰሌዳ ወይም የተሸከርካሪ ሰሌዳን እዚያው መቀበል ይችላሉ። በመልእክት አድራሻ በኩል ማድረግ ቢችሉም ሒደቱ

ግን ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል።

**Paratransit አማራጮች**

MetroAccess ክልላዊ የሆነ ተሳፋሪዎች ጉዞን የሚጋሩበት የቤት ለቤት አገልግሎት ሲሆን በ Americans with Disabilities Act ድንጋጌዎች መሰረት በ Washington Metropolitan Area Transit Authority (WMATA) የተመሰረተ ነው። MetroAccess አገልግሎት የሚሰጠው በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ወደ አውቶብስ ፌርማታ ወይም ወደ ባቡር ጣቢያ መመላለስ ለማይችሉ ሰዎች ነው።

አንድ ሰው ለ MetroAccess አገልግሎት ብቁ ለመሆን ከሚከተሉት ሁኔታዎች መካከል አንዱን ማሟላት አለበት፡

(1) በ ADA በተገለጸው መሰረት አካል ጉዳት ያለበት **እና** በአካል ጉዳቱ ምክንያትም ቋሚ ጉዞ ያለውን የትራንስፖርት አማራጭ (Metrobus እና Metrorail) ለመጠቀም የማይችል፤

ወይም (2) የሕዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪ ለመጠቀም መወጣጫ ወይም ዊልቼር ሊፍት መጠቀም ካለበትና ተደራሽ የሆነው የሕዝብ ትራንዚት ተሽከርካሪ ግን እርስዎ በሚጓዙበት ሰዓት፣ ቀንና የጉዞ መስመር ላይ አገልግሎት እየሰጠ ካልሆነ ነው። (እባክዎ ያስተውሉ፡ ሁሉም Metrobuses ለዊልቼር ተደራሽ ናቸው)፤

ወይም (3) በአካል ጉዳት ምክንያት ወደ እና ከአውቶብስ ፌርማታ ወይም የባቡር ጣቢያ መጓዝ የማይችሉ ከሆኑ።

የአካል ጉዳትዎን ዝርዝር ሁኔታዎች የሚገልጽና የ paratransit አገልግሎቶች ፍላጎትዎን የሚጠቅስ የማመልከቻ ቅጽ በጤና እንክብካቤ ባለሙያ ተሞልቶ መረጋገጥ አለበት። የፊት ለፊት ቃለ መጠይቅና ተግባራዊ ምዘናም ያስፈልጋል። ይህ ሒደት እስከ ሶስት ወራት ድረስ ሊወስድ ይችላል።

ማመልከቻውን በሚያቀርቡበት ወቅት ከግላዊ እንክብካቤ ረዳት ጋር ለመጓዝ መመዝገብ ይችላሉ። የግላዊ እንክብካቤ ረዳት ከእርስዎ ጋር በ MetroAccess በሚጓዝበት ወቅት ክፍያ አይከፍልም። (301) 562-5360 (ድምፅ), (301) 588-7535 (TTY) www.wmata.com/metroaccess.

**STAR (Arlington County)**

STAR አካል ጉዳተኛ ሆነው ለ MetroAccess ብቁ ለሆኑ ሰዎች በ Arlington በቅድሚያ የተዘጋጀና አስቀድሞ የተያዘ የጉዞ አገልግሎት ነው። የ STAR ታሪፍና የዋጋ ቅናሽ ያላቸው የታክሲ ክፍያ ትኬቶችን በ Commuter Stores እና CommuterDirect.com ላይ ማግኘት ይችላሉ። መስፈርቱን የሚያሟሉ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች እነዚህን ውጤቶች ለማዘዝ መመዝገብ የሚችሉ ሲሆን ለዚህም ወደ Commuter Direct.com® በስልክ ቁጥር (703) 228-RIDE (7433), TDD (Virginia Relay Center - መስማት ለተሳናቸው ብቻ) (800) 828-1120 ይደውሉ።

በአሁኑ ጊዜ ለ MetroAccess በቁነታቸው የተረጋገጠ የአርሊንግተን ካውንቲ ነዋሪዎች ወዲያውኑ ለ STAR ብቁ ይሆናሉ። ራይድ የሚሰጠው የእግረኛ መንገዶች ጠርዝ ድረስ ነው። አሽከርካሪዎች በተሰጣቸው አድራሻ ፊት ለፊት የሚቆሙ ሲሆን መንገደኞች ወደ ተሽከርካሪው እንዲገቡና ከተሽከርካሪው እንዲወርዱ ያግዟቸዋል።

ስለ STAR ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት: (703) 892-8747 (Voice) STAR@arlingtontransit.com (E-mail)

***TaxiAccess (Fairfax County)***

TaxiAccess በ MetroAccess ለተመዘገቡ የፌር ፋክስ ካውንቲ ነዋሪዎች በድጎማ ክፍያ የታክሲ ካብ አገልግሎት የሚሰጥ ፕሮግራም ነው። አርሊንግተን ውስጥ እንዳለው STAR ሁሉ፣ የ TaxiAccess ተጠቃሚዎች የ taxicab ጉዞዎችን ለመጠቀም ከመደበኛው ዋጋ አንድ ሶስተኛ በሚሆን መጠን የኩፖን ደብተሮችን መግዛት ይችላሉ። እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ መረጃ ለማግኘት፣ ኩፖን ለማግኘትና ኩፖን የሚቀበሉ የፌር ፋክስ አካባቢ ኩባንያዎችን ለማግኘት ይህን ድረ ገጽ ይመልከቱ፡ http://www.fairfaxcounty.gov/ncs/taxiaccess.htm።

***Fastran (Fairfax)***

Fastran በሰብአዊ አገልግሎት ኤጀንሲ ፕሮግራሞች ውስጥ ለሚሳተፉ የፌር ፋክስ ካውንቲ እና የፌር ፋክስ እና የፎልስ ቸርች ከተማ ነዋሪዎች ልዩ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ይሰጣል። ሁሉም Fastran መንገደኞች አገልገሎቱን ከመጠቀማቸው በፊት በተሳታፊ ኤጀንሲ ማረጋገጫ ማግኘት አለባቸው። http://www.fairfaxcounty.gov/ncs/forms/darapprev5.pdf

***DOT***

DOT በአካል ጉዳታቸው ምክንያት መደበኛ የትራንዚት አውቶብሶች ወይም ባቡርን መጠቀም ለማይችሉ የአሌክሳንደሪያ ነዋሪዎችና ጎብኚዎች ልዩ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ የአሌክሳንደሪያ ከተማ ፕሮግራም ነው። ጉዞዎች የሚደረጉት በ taxicabs እና የዊልቼር ማስገቢያ ባላቸው ሚኒባሶች ነው።

የብቁነት ሒደቱ ከ Metro Access ጋር ተመሳሳይ ነው። ለተጨማሪ መረጃ ወይም ማመልከቻ ለመቀበል፣ እባክዎ የ Paratransit አስተባባሪን በስልክ ቁጥር (703) 746-4079 ያነጋግሩ። https://www.alexandriava.gov/tes/info/default.aspx?id=6538

***የማሽከርከር እምቅ ኢድልን መዳሰስ***

The Woodrow Wilson Workforce Center (WWRC) ሁሉን አቀፍ የማሽከርከር አገልግሎቶችን ይሰጣል።

የማሽከርከር አገልግሎቶች የሚተዳደሩትና የሚሰጡት Occupational Therapy (OT) Department ነው። በግዛት ደረጃ እውቅና የተሰጠው ፕሮግራም ብቃታቸው የተረጋገጠ የማሽከርከር መምህራን (CDI's) እና የአሽከርካሪ ተሐድሶ ስፔሻሊስቶችን (CDRS's) የያዘ ነው።

የሙያ ቴራፒስቶች የእይታ፣ የአመለካከት፣ ለይቶ የማወቅና የእጅና እግር አጠቃቀምን ክህሎቶች በመመዘን አንድ ግለሰብ የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት ያለውን አዋጭነት ይወስናሉ። የተማሪ ፈቃድ ወይም የመንጃ ፈቃድ መያዝ ይህን አገልግሎት ለማግኘት ቅድመ ሁኔታ አይደለም። ከግምገማው በኋላ፣

ዝርዝርና ግለሰባዊ ምክረ ሃሳቦችን የያዘ ሪፖርት ይዘጋጃል። ለተጨማሪ መረጃ፣ ይህን ይጎብኙ http://www.wwrc.virginia.gov/DrivingServices.htm

**Uber እና Lyft**

Uber እና Lyft በመተግበሪያ አማካይነት ለመንገደኞች አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ናቸው። ሁለቱም ድርጅቶች መስማትና ማየት ለተሳናቸው ሰዎች ተደራሽ ቴክኖሎጂን ያቀርባሉ። ስለ Uber ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ፡ https://accessibility.uber.com/። Lyft በ ABLE ሒሳብ አማካይነት ክፍያ እንዲፈጸም ያስችላል።

## ወጣት ጎልማሶችን ወደ ስራ ቦታ ለማሸጋገር የሚያበቃ ቴክኖሎጂ

**Empowering Employment,** The Arc of Northern Virginia እና ONEder የተባለ የቴክኖሎጂ አጋር በመተባበር በ ONEder ሶፍትዌር ፕላትፎርም ላይ ያዘጋጁት የስርዓተ ትምህርት መተግበሪያዎች ስብስብ ነው። The TravelMATE እና EmployMATE መተግበሪያዎች አእምሯዊ/የዕድገት አካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች በሕዝብ ትራንዚት፣ Uber/Lyft፣ ታክሲና አውሮፕላን ጉዞ ስለማድረግ ድጋፍ የሚሰጥ ሲሆን ለስራ ቅጥራቸውም ድጋፍን ይሰጣል። The Arc of Northern Virginia TravelMATE የተባለውን የመጀመሪያ ስርዓተ ትምህርት በ 2014 ቀርጾ ስራ ያስጀመረ ሲሆን ተጠቃሚው በቤትና በስራ ቦታ መካከል ያለ የሕዝብ ትራንዚት አማራጭን እንዴት ማሰስ እንደሚችል ደረጃ በደረጃ አሳታፊ መመሪያዎችን የሚሰጥ ነው። በ2016 EmployMate ስራ የጀመረ ሲሆን ይህ ደግሞ ግለሰቦች በስራ ቦታ ላይ ያላቸውን ተግባርና ተለዋዋጭ ሁኔታዎች እንዲያስሱ የሚያግዝ ነው። የ ONEder ሶፍትዌር የተለያዩ ተግባራዊ ፍላጎቶችን ለመደገፍ ባለው ችሎታ ከሌሎች የተለየ ነው። የእያንዳንዱን ተጠቃሚ ፕሮግራም ከቪዥዋል ስማርት ትዕይንቶችና ታሪኮች፣ ቪድዮ ሞዴሊንግ፣ መሰረተ ግሪድ ዓረፍተ ነገር መስሪያ የጂፒኤስ ቴክኖሎጂ፣ የስልጠና ዳታ መከታተያ እና የይዘት ላይብረሪን ጨምሮ ትምህርት ማጋራት ጋር በቀላሉ ያበጃል። በሌላ የትኛውም ቋንቋ (በጽሑፍና በድምፅ) ሊያገለግል የሚችል ሲሆን ከወጣተ ጎልማሶች ተጨባጭ የኑሮ ሁኔታ የተገኙ ምስሎችና ቪድዮዎችንም ይጠቀማል።

TravelMate እና EmployMate የአንድን ግለሰብ ውስን ፍላጎቶች በሚያሟላ መልኩ አንዴ ከተሞሉ፣ ግለሰቡ ሒደቶቹን በተደጋጋሚ ራሱ ወይም ከቤተሰቦቹና ጓደኞቹ ጋር ማየት ይችላል። ምናባዊ ታሪኮችን በቅጽበታዊ ቪድዮዎችና ፎቶዎች በማየት፣ የቤተሰብ አባላት በራሳቸው ጉዞ ስለሚያደርጉና ስለሚሰሩ ወጣት ልጆቻቸው የሚሰማቸውን የጭንቀትና የመረበሽ ስሜት በቀላሉ መቅረፍ ይችላሉ።

ይህ ባህርይ አእምሯዊ/የዕድገት አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በመደበኛነት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው የስራ ባልደረቦቻቸውን መጠየቅ ሳያስፈልጋቸው ወደ ስራቸው ደርሰው እነዲሰሩ ያስችላቸዋል። ስራቸውን የመስራት ችሎታቸውን ራሳቸው ሲቆጣጠሩ፣ በአቻዎቻቸው ላይ ጥገኛ ከመሆን ይልቅ እንደ ሰራተኞችና የስራ ባልደረቦች ሁሉ እኩል ናቸው። ስለዚህ ስርዓተ ትምህርት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ Kymberly DeLoatche በኢሜይል kdeloatche@thearcofnova.org ወይም Peter Leisen በኢሜይል pleisen@thearcofnova.org ያነጋግሩ።

## ቅጥያ 14፡ ለራስ መሟገት

በሽግግር ሒደቱ ውስጥ **የተማሪውን ተሳትፎ ያሳድጋል**። አካል ጉዳት ያለበትን ወጣት ጎልማሳ የራስ ውሳኔ ለመገንባት ዋነኛው መንገድ በ IEP ሒደቶች አማካይነት ነው። የተማሪውን IEP ተሳትፎ አስቀድመው ይጀምሩ። ልጅዎ የሚያስፈልገውንና የሚፈልገውን ነገር እንደዚሁም ህልሞቹን በማጋራት ረገድ ያግዙትና ድምፁም እንዲሰማ ያድርጉ!

- ተማሪው በሁሉም ስብሰባዎች ላይ እንዲሳተፍ ያድርጉ።
- የልጅዎን ችሎታዎች፣ ፍላጎቶችና ምርጫዎች በመገንዘብ ረገድ ያግዙ።
- ተማሪው ህልሙንና ተስፋውን እንዲገልጽ ያድርጉት።
- ተማሪው የውሳኔ አሰጣጥ ሒደቱ አካል እንዲሆን ያድርጉ።
- ቤት ውስጥ ሆነው የ IEP ስብሰባዎች ላይ መሳተፍንና መምራትን ይለማመዱ።
- ደህንነታቸው በተጠበቁ ሁኔታዎች ልጅዎ የተወሰነ ነጻነት እንዲኖረው ይፍቀዱለት። አዎ፣ ተማሪዎች ላይሳካላቸው ይችላል፤ ነገር ግን መጥፎ ነገርን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ሊያውቁ የሚገባው እርስዎ እገዛ መስጠት እየቻሉ ነው።
- ልጅዎ የተለያዩ እርምጃዎችና ስትራቴጂዎችን እንዲለማመድና እንዲሞክር ይፍቀዱለት። አንድ እርምጃ፣ ስትራቴጂ ወይም አቀራረብ ካልሰራ፣ ተስፋ ሳይቆርጡ ሌላ ይሞክሩ!
- ልጅዎ የእርስዎን ድጋፍ እያገኘ ከማህበረሰብ ኤጀንሲዎች ጋር ግንኙነት እንዲያደርግ ያበረታቱት።

### ለራስ መሟገት የሚያገለግሉ የመረጃ ምንጮች

**I'm Determined**
I'm Determined ፕሮጀክት የሚመራውና ወጪው የሚሸፈነው በ Virginia Department of Education ሲሆን የሚያተኩረውም ከ I'm Determined ባህርይ ጋር የተያያዙ ክህሎቶችን ለመለማመድ ቀጥተኛ መመሪያ፣ ሞዴሎችና አጋጣሚዎችን መፍጠር ላይ ያተኮረ ነው። የ I'm Determined ድረ ገጽ እነዚህን ክህሎቶች ወጣቶች እንዲማሩና ወላጆችም ለማስተማር እንዲያግዙ የሚረዱ መሳሪያዎችን ያቀርባል።
www.imdetermined.org

**It's My Choice**
By William T. Allen, PhD ከ Minnesota Governor's Council on Developmental Disabilities
www.Mn.gov/mnddc//extra/publications/choice/Its_My_Choice.pdf

**"Dude, Where's My Transition Plan?"**
A guide to promote student involvement in planning for life after high school.
http://www.tnstep.org/uploads/files/Final%20Dude%20Transition%20Book.pdf

**People First for Young Adults**
The Arc of Northern Virginia ዕድሜያቸው ከ 14-26 ለሚሆኑ አካል ጉዳተኛ ወጣቶች People First for Young Adults የተባለ የማህበራዊና የራስ ተሟጋች ቡድንን ያቀርባል። ቡድኑ ወር በገባ በሁለተኛው ማክሰኞ ቀን ይሰበሰባል። ለተጨማሪ መረጃ ይህን ይጎብኙ፡ www.thearcofnova.org።

**Autism Speaks**
https://www.autismspeaks.org/family-services/tool-kits/transition-tool-kit/self-advocacy

**PACERS (National Parent Center on Transition and Employment)**
http://www.pacer.org/transition/learning-center/independent-community-living/self-determination.asp

**Parent Center Hub**
http://www.parentcenterhub.org/repository/priority-selfadvocacy/

**Sound Out**
https://soundout.org/intro-to-student-voice/

# ቅጥያ 15፡ የመኖሪያ አማራጮችን መዳሰስ

አካል ጉዳት ላለበት ጎልማሳ የሚሆን ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ምቹና ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው መኖሪያ ቤት ማግኘት በአሁኑ ጊዜ ቤተሰቦች ከሚያጋጥሟቸው በጣም አስቸጋሪ ፈተናዎች መካከል አንዱ ነው። ይህ ክፍል Medicaid Waiver ላላቸውና ለሌላቸው ሰዎች ዝግጁ የሆኑ የመኖሪያ ቤት አማራጮችን ጠቅለል ባለ መንገድ የሚዘረዝር ነው። እዚህ ውስጥ የተደረደሩትን የመኖሪያ ቤት አማራጮችን ዝርዝር መግለጫ ለማየት *Finding a Home for Adults with Disabilities* በ the Arc of Northern Virginia ድረ ገጽ ላይ ማየት ይችላሉ፡ http://www.thearcofnova.org/programs/transition/transition-points። በተጨማሪም፣ የ Northern Virginia Housing and Supportive Services ድረ ገጽን ይጎብኙ፡ www.novahss.org.

**የቤትና የመኖሪያ አገልግሎቶች ሲነጻጸሩ**
በርካታ የአእምሮ ዕድገት አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በማህበረሰቡ ውስጥ መኖር ለመቻል የቤት እና የመኖሪያ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። የጎልማሳ ልጅዎን አማራጮች ለመገንዘብ በእነዚህ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት አስፈላጊ ነው።

**ቤት** ማለት አንድ ሰው የሚኖርበት አካላዊ ቦታ (ቤት፣ አፓርታማ፣ የኪራይ ክፍል)፣ ሸክላና ሞርታር **ወይም** በአካላዊ ቤት ውስጥ ለመቆየት የሚከፈል የኪራይ እገዛ ማለት ነው። (የቡድን ቤቶች በዚህ አገላለጽ መሰረት ቤቶች አይደሉም፤ ከታች ይመልከቱ)።

**የመኖሪያ አገልግቶች** ማለት በግለሰቦች ወይም በኤጀንሲ የተቀጠሩ ተንከባካቢ ሰራተኞች የሚሰጡት ድጋፍና ቁጥጥር ማለት ነው።

ይሁን እንጂ፣ እነ ቡድን ቤት ላሉ አንዳንድ የመኖሪያ አገልሎቶች፣ አካላዊ ቤትና የመኖሪያ አገልግሎቶች አንድ ላይ የተሳሰሩ ናቸው፤ *የቤት አገልግሎት እንደ መኖሪያ አገልግሎት ይቆጠራል (ሸክላዎችና ብሎኬትን ሳይጨምር)። የእነዚህ ፕሮግራሞች ወጪ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ፣ መክፈል የሚችሉት የMedicaid waivers ያላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው።* waiver እያለውም ቢሆን ግለሰቡ የመኖሪያ ክፍያ መክፈል ይኖርበታል።

ስለዚህ፣ ሶስቱ መሰረታዊ አማራጮች እነዚህ ናቸው፡

1. **Developmental Disabilities Waiver ላላቸው የ Community Living Waiver፣ Family and Individual Supports Waiver፣ እና the Building Independence Waiver፣** ጨምሮ የድጋፍ አገልግሎት ወጪ የሚሸፈነው በ Waiver ሲሆን ድጋፍ ሰጪ ቡድንዎ ተገቢውን አገልግሎት ለይቶ መስጠት አለበት። ይሁን እንጂ፣ የኪራይ ወጪው የተለየ ሆኖ በአካል ጉዳተኛው የሚከፈል ነው። ይህ አብዛኛውን ጊዜ የሚሸፈነው በማሕበራዊ ዋስትና ገቢ፣ በተገኘ ገቢና ምናልባትም በተጨማሪ የቤት ድጎማ ነው።
2. **Developmental Disabilities Waiver ለሌላቸው ሰዎች**፣ ለአካላዊ ቤት **እና** ለድጋፍ አገልግሎቶች (ግለሰቡ ካስፈለገው) ክፍያ የሚሸፈንበት መንገድ መፈለግ አለበት።
3. **ለ Waivers ብቁ ለሆኑ ሰዎች**፣ ይህ መምሪያ ከታተመበት ቀን አንስቶ ቨርጂኒያ የዕድገት መዘግየት አካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ቤት ውስጥ እንዲኖሩ ለማስቻል ከተዘረጋው "State Rental Assistance Program" የሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ ውስን መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል። ይህ ፕሮግራም የቤት ቫውቸር ወይም የኪራይ ድጎማ ሆኖ ይሰራል። እነዚህ አገልግሎቶች የሚቀርቡት Developmental Disability Waivers ላላቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለእነዚህ Waivers በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ላሉትም ጭምር ነው። በተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ ያሉ የተወሰኑ ሰዎች ይህን ገንዘብ ተጠቅመው በተፈጥሮ ስፖርት (ለምሳሌ ቤተሰበ ለእርዳታ የሚመጣበት እና/ወይም በግል የተቀጠረ አጋዥ በመመደብ Waiver እስከሚደርሳቸው ድረስ ይህን ውስን የቤት ዕድል ለማግኘት ይሞከራሉ። ስለዚህ ፕሮግራም የበለጠ ለማወቅ፣ Jeannie Cummins (j.cummins@dbhds.virginia.gov) ጋር ይነጋገሩ።

ዋጋው ተመጣጣኝ የሆነ ቤት ማግኘት ፈተና በመሆኑ፣ የቤት አማራጮችን ለማሳደግ በዝግጅት ላይ ያሉ በርካታ ዕቅዶች አሉ። ድጋሚ የተሻሻለው Developmental Disabilities Waivers የተለያዩ የመኖሪያ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ወይም የተሳሰሩ የተለያዩ አዳዲስ አማራጮችን ያቀርባሉ። ቤተሰቦች የቤት ወጪን እንዴት በግላቸው መሸፈን እንደሚችሉ ወይም ቀደም ሲል በባለቤትነት የያዙትን ቤት እንዴት ይዘው እንደሚቆዩ እያሰቡ ነው። አሁን ያሉትን አማራጮች በተመለከተና ለእርስዎ እንዴት ምቹ እንደሚያደርጓቸው ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የኢንተርኔት ገለጻ፣ ስላይዶችና ሌሎች ቤትን የሚመለከቱ መረጃዎችን የያዘውን ኦንላይን መሳሪያችንን ይጎብኙ። https://thearcofnova.org/programs/transition/finding-home-adults-disabilities/home-toolbox/housing-toolkit/

**1. ወጪያቸው በ by Medicaid Waiver የሚሸፈኑ የመኖሪያ አማራጮች፡** ወዳጅ ዘመድዎ Medicaid Waiver ካለው፣ በተለያዩ ማዕቀፎች ውስጥ እንዴት ሊኖር እንደሚችልና ድጋፍም እንዴት እንደሚያገኝ የተወሰኑ አማራጮች ያሉት ሲሆን ይህም የተለያዩ መኖሪያዎችን የሚያጠቃልል ወይም አብሮ የሚሰራ ሊሆን ይችላል። እነዚህ አማራጮች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። አዲስ በተሻሻለው Waivers መሰረት (ከሴፕቴምበር 1/2016 ጀምሮ) በአካል ጉዳተኛው ፍላጎትና ባለው Waiver ላይ ተመስርቶ የሚቀርቡ አማራጮች እንዳሉ ያስተውሉ። The Community Living Waiver ዓላማው እጅግ ከፍተኛና ውስብስብ ፍላጎት ያላቸውን ግለሰቦች ለመደገፍ ሲሆን፣ Family and Individual Supports Waiver ደግሞ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ለመደገፍና Building Independence Waiver ደግሞ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ ሆኖ ውስን የድጋፍ ፍላጎቶች ላላቸው ግለሰቦች የታሰበ ነው። ስለ Waivers ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የዚህን መምሪያ ገጽ 24 ይመልከቱ።

| **የአካል ጉዳት Waiver አገልግሎቶች** | **Community Living Waiver** | **Family & Individual Supports Waiver** | **Building Independence Waiver** |
|---|---|---|---|
| **በቡድን መኖሪያ ቤቶች**- 24/7 ሰራተኛ ያላቸውና ከ 3-7 የሚሆኑ አካል ጉዳተኞች የሚኖርባቸው ቤቶች። ቤቶቹ አብዛኛውን ጊዜ ሙሉ ጊዜ በፈረቃ የሚሰሩ ሰራተኞች አላቸው። | X | | |
| **የደባል ኑሮ**- ግለሰቡ ከጉዳት አልባ ግለሰብ ጋር የሚኖር ሲሆን ጉዳት አልባውም አብሮ ስለኖረ ለክፍሉ ኪራይን ለምግብ ወጪው ተመላሽ ይደረግለታል | X | X | X |
| **ራስን ችሎ መኖር**- ክህሎት መገንባትና ለበለጠ ኃላፊነት የማዘጋጀት ዓላማ ላይ ትኩረት አድርጎ በቤት ውስጥ የሚሰጡ ድጋፎች | | | X |
| **ስፖንሰር የተደረገ መኖሪያ** አካል ጉዳተኛው ሰው ክፍያ በሚከፈለው ተንከባካቢ ቤት ውስጥ ከተንከባካቢው ጋር የሚኖርበት አማራጭ | X | | |
| **በድጋፍ የታገዘ ኑሮ**- መኖሪያ ቤቱ በድጋፍ ሰጪው ባለቤትነት የተያዘ ሆኖ እስከ 24/7 የሚደርስ ድጋፍ ይሰጣል | X | X | |

https://thearcofnova.org/programs/transition/finding-home-adults-disabilities/home-toolbox/housing-toolkit/ በመጎብኘት እያንዳንዱ ሰው የራሱ ክፍል የማያገኝባቸውን የመኖሪያ አማራጮች በተመለከተ መረጃ የተሞላ ግዙፍ የኦንላይን መሳሪያ ማየት ይችላሉ። ድረ ገጹ በተጨማሪም የተለያዩ የድጋፍ ፍላጎቶች ያላቸውንና በተቀናጀ የቤት አማራጮች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ታሪክ ያሳያሉ።

የቤት አማራጮችን "ሁሉን አቀፍ ጉብኝቶች" ለማየት ይህን ይጎብኙ፡ http://www.youtube.com/user/VideosatTheArcofNoVA ፡፡

**የመኖሪያ (የሕዝብ) ፕሮግራም አማራጮች**
ቤትን የሚያቀርቡ አማራጮች ሲሆኑ የሚከተሉትን አገልግሎቶች ጨምሮ ለማግኘት Waiver፣ የግል ገንዘብ፣ ወይም ተፈጥሯዊ ድጋፎችን እንዲጠቀሙ ያስችልዎታል፡

**2. የመንግስት ቤት**
የመንግስት ቤት ማለት ወጪው በፌዴራል መንግስት የሚሸፈንና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች የሚቀርብ ቤት ነው። አብዛኛውን ጊዜ የቤቶቹ ባለቤት የአካባቢው የቤቶች ባለስልጣን (PHA) ሲሆን የገንዘብ ፍሰት የሚደረግለትም ከ Federal Department of Housing and Urban Development (HUD፣ ፌዴራል የቤቶችና የከተማ ልማት ሚኒስቴር) ነው። አንድ ግለሰብ የመንግስት ቤት ለማግኘት ብቁ የሚሆነው የመንግስት ቤቶች ባለስልጣን ያስቀመጣቸውን የዝቅተኛ ገቢ መስፈርቶች ሲያሟላ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ፣ ግለሰቡ በድጎማ ቤት ውስጥ ለመኖር ብቁ የሚሆነው በአካባቢው የመንግስት ቤቶች ባለስልጣን በተገነባና በሚመራ ቤት ውስጥ መኖር አለበት። አስፈላጊ ከሆነ፣ አብሮዎት ለሚኖር ረዳትዎ አንድ ተጨማሪ መኝታ ቤት እንዲሰጥዎ ማመልከት ይችላሉ።

የሚያሳዝነው ግን፣ የመንግስት ቤቶችን ለማግኘት ያለው የተጠባባቂዎች ዝርዝር በጣም ረዥም ነው። አሁን ባለው ሁኔታ፣ አሌክሳንደሪያ ወይም ፌርፋክስ (የመንግስት ቤቶችን የሚያስተዳድሩ ብቸኛ የ Northern Virginia አካባቢዎች) ውስጥ የተጠባባቂ ዝርዝር ላይ ለመካተት እንኳን አይቻልም።

**3. Housing Choice Vouchers**
Housing Choice Vouchers (HCVs) "Section 8 Vouchers" ተብለው ይጠሩ ነበር። ቫውቸር ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ግለሰቦችና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ዝቅ ባለ ዋጋ ከግለሰብ ባለቤቶች ቤት እንዲከራዩ ያስችላቸዋል። ተከራዩ ከገቢው ላይ 30% የሚሆነውን ለኪራይ ክፍያ የሚያውል ሲሆን ቫውቸሩ ደግሞ ፍትሐዊ የገበያ ኪራይ መጠን ድረስ ቀሪውን የኪራይ ወጪ ይደጉማል። ቫውቸር አንዴ ከተቀበሉ፣ ከአንድ ዓመት በኋላ ቫውቸሩን በሃገሪቱ ውስጥ ወደፈለጉበት ቦታ ይዘውት መሄድ ይችላሉ፣ አዲስ የሄዱበት አካባቢም ቫውቸሩን ተቀብሎ ሊያስተናግድዎ ፈቃደኛ መሆን ይኖርበታል። አስፈላጊ ከሆነ፣ አብሮዎት ለሚኖር ረዳትዎ አንድ ተጨማሪ መኝታ ቤት እንዲሰጥዎ ማመልከት ይችላሉ። የዚህ የአጠቃላይ ሕዝብ ፕሮግራም የተጠባባቂ ዝርዝሮች ረዥም ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ በአርሊንግተን፣ በአሌክሳንድሪያና በፌርፋክስ ውስጥ ለተጠባባቂ ዝርዝር ምዝገባ ቆሟል።

## 4. State Rental Assistance Program (SRAP)

ቨርጂኒያ የዕድገት መዘግየት አካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ቤት ውስጥ እንዲኖሩ ለማስቻል ከተዘረጋው "State Rental Assistance Program" የሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ ውስን ነው። ይህ ፕሮግራም የቤት ቫውቸር ወይም የኪራይ ድጎማ ሆኖ ይሰራል። <u>እነዚህ አገልግሎቶች የሚቀርቡት Developmental Disability Waivers ላላቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለእነዚህ Waivers በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ላሉትም ጭምር ነው</u>። በተጠባባቂ ዝርዝሩ ውስጥ ያሉ የተወሰኑ ሰዎች ይህን ገንዘብ ተጠቅመው በተፈጥሮ ስፖርት (ለምሳሌ ቤተሰብ ለእርዳታ የሚመጣበት እና/ወይም በግል የተቀጠረ ኢጋዥ በመመደብ Waiver እስከሚደርሳቸው ድረስ ይህን ውስን የቤት ዕድል ለማግኘት ይሞክራሉ። ስለዚህ ፕሮግራም የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ Jeannie Cummins በቀጣዩ አድራሻ ያነጋገሩ [j.cummins@dbhds.virginia.gov](mailto:j.cummins@dbhds.virginia.gov)።

እንደ መንግስት ቤቶች ሁሉ፣ አካል ጉዳተኞች በ Housing Choice Voucher የሚከራዩት ቤት ውስጥ ድጋፍ ለመቀበል Developmental Disability Waiver ወይም CCC Plus Waiver መጠቀም ይችላሉ። ይህ ሁኔታ ሲፈጠር፣ ግለሰቡ የአፓርታማው ተከራይ ይሆናል።

**ወጪን በግል የመሸፈን አማራጮች**

በርካታ አካል ጉዳተኞች ለ Medicaid Waiver <u>ብቁ አይደሉም፣ ሌሎች ደግሞ እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት ረዥም ወረፋ እየተጠባበቁ ነው፤</u> ቤተሰቦቻቸው ተገቢነት ያለው ቤት ብቻ ሳይሆን ለቤቱ ክፍያ የሚፈጽሙበትን መንገድም ማወቅ አለባቸው። ይሁን እንጂ፣ በቤተሰቦች የተዘጋጀ ቤት የግለሰቡን ፍላጎቶችና ምርጫዎች ይበልጥ የመቅረብ እድል ያለው ሲሆን አብረው የሚተከሉ የክትትልና የጥራት ማረጋገጫ ስርዓቶችም ይኖሩታል።

**1. Microboards**

የድጋፍ ሰጪዎች ክበብ ማለት አካል ጉዳተኛ ለሆነ ሰው የሚገዳቸውና ይህን ግለሰብ ለመርዳት ጊዜያቸውን በበጎ ፈቃደኝነት የሚያውሉ የቤተሰብና የጓደኞች ቡድን ነው። የድጋፍ ሰጪዎች ክበብ ራሱን እንደ ኮርፖሬት ተቋም ካደራጀ፣ አካል ጉዳተኛውን ወክሎ በንግድ ስራዎች ላይ መሰማራትና microboard መሆን ይችላል።

ይህን መደበኛ የሆነ microboard የሚል ስያሜ መያዙ ቦርዱ በ Virginia Housing Development Authority (VHDA) በኩል ወለዱ አነስተኛ የሆነ ብድር እንዲያገኝ ያስችለዋል፣ [www.vhda.com](http://www.vhda.com) ለ Bruce DeSimone በ 804-343-5656 [bruce.desimone@vhda.com](mailto:bruce.desimone@vhda.com) በማሳወቅ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

በተጨማሪም፣ microboards የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡

- የ waiver ድጋፎችን ማስተዳደር (ለምሳሌ፡ ሰራተኛ መቅጠርና ማሰልጠን)፤
- የንብረት አስተዳደርና ጥበቃ መስጠት፤
- የ waiver አገልግሎቶችን የሚሰጥ የግል አገልግሎት አቅራቢ መቅጠር፤
- ቀውስ በሚፈጠርበት ወቅት ችግር እንዲፈታ ማገዝ፤
- ወደ መረጃ ማዕከላት ማስተላለፍ እና/ወይም መረጃዎችን ማቀናጀት፤
- ተሰሚነት ያለው ቦርድ ሆኖ ማገልገል

Microboards ለረዥም ጊዜ ቆይታ እንዲኖራቸው የታሰቡ ናቸው። microboard ውስጠ ደንብ፣ የስብሰባ መርሃ ግብር፣ የመተካካት ዕቅድና የስልጣን ወሰኑን ያዘጋጃል። ለተጨማሪ መረጃ፣ Virginia Microboard Association በስልክ ቁጥር 757-460-1569፣ [http://virginiamicroboards.org/](http://virginiamicroboards.org/)፣ ወይም[VirginiaMicroboards@gmail.com](mailto:VirginiaMicroboards@gmail.com) ይጠይቁ።

**2. የጋራ አፓርታማዎች**

የጋራ አፓርታማ ማለት በቀላሉ ከአንድ ወይም ከብዙ ሰዎች ጋር የሚጋሩት የኪራይ አፓርታማ (ቤት፣ ኮንዶሚኒዬም ወይም ታውን ሆም) ማለት ነው። ጥቅሙም ወጪ መጋራትና ከሌላ ሰው ጋር አብሮ መሆን ነው።

በጋራ አፓርታማ ውስጥ፣ አንድ፣ የተወሰኑ ወይም የትኞቹም የቤተሰብ አባላት waiver እና/ወይም ተንከባካቢ ሰራተኛ ላይኖራቸው ይችላል። ይሁን እንጂ፣ waiver ካለዎት ሰራተኞች በቀን ለ 24 ሰዓት በቦታው እንዲኖሩ ለማድረግ የድጋፍ መስጫ ሰዓትን ማሸጋሸግ አይችሉም። እያንዳንዱ ተንከባካቢ ሰራተኛ ለአንድ አካል ጉዳተኛ በእንክብካቤ ዕቅዱ መሰረት እንክብካቤ መስጠት አለበት።

3. **ክፍል መከራየት**

በዚህ አቀማመጥ ውስጥ፣ ክፍሉን የሚከራየው ሰው የራሱ የግል መኝታ ቤት ሲኖረው፣ እንደ ኪችንና ሳሎን የመሳሰሉ ክፍሎችን የመጠቀም መብት አለው። ጥቅሙም ወጪ መጋራትና ከሌላ ሰው ጋር አብሮ መሆን ነው። ሌላኛው ጥቅሙ ደግሞ የቤቱ ባለቤት ወይም ተቀዳሚ አከራዩ ለቤቱ የዕለት ተዕለት ፍላጎት ሃላፊነት ያለበት መሆኑ ነው።

በድጋሚ፣ ክፍሉን የሚከራየው ሰው waiver እና/ወይም ተንከባካቢ ሰራተኛ ሊኖረው ይችላል፤ ነገር ግን ይህ ፍላጎትና ዕቅድ ስለመኖሩ በግልጽ ለቤት ባለቤቶች ወይም አከራዮች በማሳወቅ ሁሉም ሰው በዚህ ሁኔታ ምቾት የሚሰማው መሆኑን ሊያረጋግጡ ይገባል።

**4. Life Estates**

በ life estate ውስጥ፣ የቤቱ ባለቤት ለአካል ጉዳተኛው (ለምሳሌ ለእርስዎ ልጅ) "የዕድሜ ልክ ኪራይ" የሚሰጠው ሲሆን አካል ጉዳተኛውም ቀሪ ዘመኑን በዚያ ቤት ውስጥ የመኖር መብት ይኖረዋል ማለት ነው። የዕድሜ ልክ ተከራዩ ሲሞት፣ የቤቱ ባለቤትነት መብት ወደ ሌላ የቤተሰብ አባል፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ወይም ለሁለቱም ይተላለፋል።

ቤተሰቡ የሞርጌጅ ክፍያውን ቀደም ሲል ያጠናቀቀ ከሆነ ወይም መክፈል ያለበት ቀሪ የሞርጌጅ ክፍያ አነስተኛ ከሆነ፣ ይህ ጥሩ አማራጭ ሊሆን ይችላል። ቤተሰቡ ቤቱን ለጎልማሳ ልጃቸው ሊያስተላልፍ ይችላል። ቤቱ ለአካል ጉዳተኛው የተላለፈው ወላጆቹ በሕይወት እያሉ ከሆነ፣ ወላጆች አካል ጉዳተኛው እያለ በዚያው ቤት ውስጥ ለመቆየት ወይም ቤቱን ለቅቀው ለመውጣት ሊወስኑ ይችላሉ።

*በርካታ አገልግሎት አቅራቢዎች የዕድሜ ልክ ተከራዩ ሲሞት ቤቱ የማይተላለፍላቸው ከሆነ የዕድሜ ልክ ተከራዩን ድጋፎች ለማስተዳደር ዳተኛ እንደሚሆኑ ያስተውሉ።* የዕድሜ ልክ ተከራዩ ፍላጎቱ ወይም ምኞቱ በመቀየሩ ምክንያት በቤቱ ውስጥ ለመቆየት ካልቻለ፣ የእንክብካቤ ድጋፉን በተመለከተ ስምምነት ማድረግም ያስፈልጋችኋል።

### 5. የጋራ የቤት ግዥ

የተወሰኑ ቤተሰቦች ተሰባስበው አንድ ቤት ሊገዙ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ሶስት ቤተሰቦች ገንዘብ አዋጥተው ባለ ሶስት መኝታ ቤት ሊገዙ ይችላሉ። ከእያንዳንዱ ቤተሰብ አንድ አካል ጉዳተኛ በቤቱ ውስጥ ይኖርበታል።

ይህ ሞዴል ሊሰራ የሚችለው ቤተሰቦቹ ቤቱን በእጅ በእጅ ክፍያ የገዙት ከሆነ ነው።  ሞርጌጅ ካለው፣ ብድርና የባለቤትነት ሰነዶችን ለማግኘት ያስቸግራል፣ በተለይ ደግሞ አንዱ ቤተሰብ ቤቱን ለመለቀቅ ከፈለገ። ቤተሰቦቹ በቤቱ ላይ ያላቸውን ድርሻ ለመሸጥና ወጪን ለመጋራት የሚያስችሉ ደንቦችን ከጠበቆቻቸው ጋር ሆነው ማዘጋጀት አለባቸው።

ስለ ቤት ጉዳይ ጠለቅ ያለ መረጃ ለማግኘት፣ ቀጣዩን Transition POINTS መምሪያችንን ያውርዱ፡ ለአካል ጉዳተኛ ጎልማሶች ቤት መፈለግ
https://thearcofnova.org/programs/transition/finding-home-adults-disabilities/

### 6. የታክስ ክሬዲት ክፍሎች

አልሚዎች በአንድ ሕንጻ ውስጥ የተወሰኑ ክፍሎችን ለይተው እነዚህን ክፍሎች ለአካል ጉዳተኞች ለማከራየት ምርጫ ያቀርባሉ። የኪራይ ምርጫ ያላቸውን ክፍሎች የያዙ አንዳንድ የታክስ ክሬዲት የሚያገኙ ሕንጻዎች መሰረተ ፕሮጀክት የኪራይ ድጎማ የሚያገኙ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ እንደ Housing Choice Vouchers ወይም State Rental Assistance የመሳሰሉ የኪራይ ድጎማዎችን ይቀበላሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ የ DBHDS Housing Specialist, Jeannie Cummins በዚህ ያግኙ j.cummins@dbhds.virginia.gov እንደዚሁም ይህን ይጎብኙ፡ http://www.dbhds.virginia.gov/developmental-services/housing/housing-team

**ምስጋና**

“ቀጣይ ሕይወትን አስተማማኝ ማድረግ” ሊሳካ የቻለው ከሚከተሉት ግለሰቦች በተደረገ አስተዋጽኦ አማካይነት ነበር፡

Stephanie Sampson
ደራሲና አርታኢ
የ Transition POINTS ኮሚቴ ሰብሳቢ
The Arc of Northern Virginia
sampsonstephanie5@gmail.com

Diane Monnig
ተባባሪ አርታኢ
የሽግግር ኃላፊ
The Arc of Northern Virginia
dmonnig@thearcofnova.org

መምሪያው ከተለያዩ መንግስታዊ፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙና ከግል ድርጅቶች በተውጣጡ ባለሙያዎችና ወላጆች በየዓመቱ እየተገመገመ ወቅታዊ መረጃ እንዲካተትበት ይደረጋል።